# የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የስልጠና ማዕከል
## የረጅም ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና ፕሮግራም

# የቅድመ ሙግት፣ሙግትና የይግባኝ ሂደትን መምራት

2002 ዓ.ም

## ማውጫ


መግቢያ

**ክፍል አንድ**

**የጉዳዮች አመራር በጠቅላላው**

በፍትሃብሄር ስነስርአት አካሄድና አመራር መሰረታዊ መርሆች

በፍትሃብሄር ጉዳዮች ቀደም ብሎ የመግባት ዘዴ

ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ዘዴ

ውጤታማ የሆነ የቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴ

**ክፍል ሁለት**

**የቅድመ ሙግት አመራር**

ክስ ለመስማት መደረግ ስላለባቸው ቅድመ ዝግጅቶች

ክስን የመስማት ዘዴ

ጭብጥ የመመስረት ዘዴ

**ክፍል ሶስት**

**ሙግት አመራር**

ሰብሰብ ያለ የፍትሃብሄር ሙግት አሰማም ዘዴ

የሙግት ቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴዎች

የራሳቸውን ጉዳይ ይዘው የሚከራከሩ ተሟጋቾች ጉዳይን መምራት

የውስብስብ ጉዳዮች ሙግት አሰማም ዘዴ

**ክፍል አራት**

**ይግባኝ አመራር ዘዴ**

የይግባኝ ቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴ

ይግባኝን ለመስማት መደረግ ስላለባቸው ዝግጅቶች

የይግባኝ አሰማም ዘዴ

አባሪዎች

የስልጠና ማንዋል

## መግቢያ

አንድ ዳኛ የቀረበለትን ጉዳይ ፍሬነገሩን ከህጉ ጋር በማገናዘብ የመወሰን ስራ (adjudication) ብቻ ወይስ ጉዳዩን የመምራት (case management) ሃላፊነት አለበት የሚለው ጥያቄ ከቅርብ ጊዜ በተለይ ላለፉት አስርተ አመታት ከፍርድ ቤት ማሻሻያ ፕሮግራሞች ጋር ተያይዞ በአገራችን በመነሳት ላይ ያለ ጉዳይ ነው፡፡ የጉዳዮች ጫና በየጊዜው እየጨመረ መምጣት፣ ፍርድ ቤቶች በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚያሳድሩት ተፅእኖ እየጎላ መምጣት፣ ፍርድ ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች የህብረተሰቡን ትኩረት በማግኘታቸውና የመሳሰሉት ምክንያቶች ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት አገልግሎት ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሃዊ እንዲሆን አስገድደዋል፡፡

የቀረቡ ጉዳዮችን የመወሰንና የጉዳዮችን አካሄድ በአግባቡ የመመራት ተግባራት እርስ በርሳቸው የተያያዙ የዳኝነቱ ስራ ገፅታዎች መሆናቸው እየታመነበት መጥቷል፡፡ አንድ የፍትሃብሄር ጉዳይ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ካልተመራ በመጨረሻ ላይ የሚገኘው ውጤት ኢ-ፍትሃዊ የመሆን አዝማሚያው ከፍተኛ ነው፡፡ በፍትህ ስርአታችን እንዲሁም በሌሎች በርካታ አገሮች የመጨረሻ ውጤት ብቻ ሳይሆን ውጤቱን ለማግኘት የምንሄድበት መንገድና ስልት የውጤቱ አካል ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡ በመሆኑም ጉዳዮች በአግባቡ ሊመሩ ይገባል፡፡ ዳኞችም ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ፍትሃዊ የሆኑ የጉዳዮች አመራር ስልቶችን በመለየት ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ጉዳዮችን የመምራት ስርአት በውሱን ደረጃ በፍትሃብሄር ስነስርአት ህጋችን ውስጥ ቀደም ሲል ተቀርጾ እንዲካተት የተደረገ ሆኖም በልማዳዊ አሰራር ተግባራዊ ሳይደረግ የቀረ ነው፡፡ ባለፉት ጥቂት አመታት ልምዱን ወደጎን በመተው የስነስርአት ሕጎቻችን በሚደነግጉት መሰረት ለመፈጸም በተደረጉት ሙከራዎች አበረታች ውጤት ለማምጣት ተችሏል፡፡

በፍትህ አሰተዳደሩ ውስጥ የሚሳተፉት ሁሉም ባለድርሻዎች ስነስርአት ህጎችን ሊያከበሯቸውና ሊያስከብሯቸው ይገባል፡፡ በተለይም ዳኞች ሕጉን ማክበር ብቻ ሳይሆን ተከራካሪ ወገኖች እንዲያከብሯቸው የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ የክርክሩን መሪ ሁሉም

ተከራካሪ ወገኖች እንደፈለጉ የሚያሽከረክሩት ከሆነ ፍትህን በሚፈለገው ፍጥነት መስጠት አይቻልም።

በፍትሃብሄር ስነስርአት ህጉ ላይ የተቀመጡት ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው ፍርድ ቤቶች በጉዳዮች አካሄድ ላይ ሰፊ ክትትልና ቁጥጥር እንዲያደርጉ ስልጣኑ (express and inherent) አላቸው። በተለይ ውስብስብ ጉዳዮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ ፍርድ ቤቶች ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ከመደበኛው የተለየ የጉዳይ አሰማም ስልትን ሊከተሉ ይችላሉ።
ፍርድ ቤቶች ጉዳይ የሚሰማበትን ሁኔታ አቅደው በሚያስፈፅሙበት ጊዜ ለጉዳዩ ፈጣን፣ ወጭ ቆጣቢና ፍትሃዊ እልባት ለመስጠት መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለባቸው።
ዳኞች ጉዳዮች የሚመሩባቸውን ስልቶች ከጉዳዮቹ አይነትና በፍርድ ቤቶች ካለው ሃብት ጋር አጣጥመው ሊወስኑ ይገባል። የዳኛ ጊዜ ከሁሉም ሃብቶች በጣም ውዱ እንደመሆኑ መጠን ዳኞች ይህንን ጊዜ በብልጠትና ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊጠቀሙበት ይገባል።
የጊዜ እጥረት ወይም የስራ ጫና ዳኞች ጊዜያቸውን በጉዳዮች አመራር ላይ እንዳያውሉ ሊያስገድዳቸውና ሊያሳምናቸው ይችላል። ሆኖም ዳኛው ጉዳዩች በተጀመሩበት ወቅት ጊዜያቸውን ለአመራር ስራ መስዋት ማድረጋቸው ወደፊት ጉዳዩ በቀላሉና ቀደም ብሎ እንዲያልቅ የሚያደረገው፣ ጊዜ አባካኝ በሆኑ ስራዎች እንዳይጠመዱ የሚያደርግና በአመዛኙ አጭር ሙግት እንዲኖርና በጠቅላላው የዳኝነት ጊዜን ቁጠባ (economies of judicial time) የሚያሰፍን በመሆኑ ተመራጭ ነው።

## ሞጁሉን በተመለከተ

ይህ የስልጠና ሞጁል በተቻለ መጠን ዳኞች በራሳቸው እየተጠቀሙት እንዲማሩበት ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡ ሞጁሉ ጉዳዮችን መምራትን በተመለከተ አንዳንድ መሰረታዊ ነጥቦችን፣ በስነስርአት ህጉ የተቀመጡ ድንጋጌዎችን በአጭሩ የሚያነሳ ሲሆን ከዚህ ውጭ የፍትሃብሄር ጉዳዮች አመራር በዋነኝነት ክህሎት በመሆኑ ሰልጣኞች የአመራር ዘዴዎችን በተግባራዊ ልምምድ እንዲያዳብሯቸው ታስቧል፡፡

ሞጁሉ አራት ክፍሎች አሉት፡፡ ክፍል አንድ ስለ ጉዳዮች አመራር መሰረታዊ ፅንሰ ሃሳቦችን ከፍትሃብሄር ጉዳይ አካሄድ ጋር ያወያያል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ በጉዳዮች ቀደም ብሎ ስለመግባትና ጉዳዮችን ለያይቶ ስለመምራት በዋነኝነት ይታያል፡፡

አንድ የፍትሃብሄር ጉዳይ ለፍርድ ቤት በቀረበ ጊዜ ወደ ዋናው ጉዳይ ከመገባቱ በፊት ዳኞች ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውጤታማ የሆነ ሙግት እንዲኖርና ፍትሃዊ የሆነ መደምደሚያ ላይ ለመድረስ ቀደም ብለው መከናወን የሚገባቸው ወሳኝ ተግባራት ይኖራሉ፡፡ የሞጁሉ ክፍል ሁለት የቅድመ ሙግት አመራርን ይመለከታል፡፡ በዚህ ክፍል ክስ ለመስማት መደረግ ስላለባቸው ዝግጅቶች፣ ክስ የመስማት ዘዴንና ጭብጥ የመመስረት ዘዴን ይመለከታል፡፡

ክፍል ሶስት ሙግት የሚመራበትን ስልቶች ይመለከታል፡፡ በተለይ በፍርድ ቤቶቻችን እንደ ችግር የሚነሳው የተበታተነ የሙግት አሰማም መንገድ መከተላችን እንደሆነ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ክፍል ሰብሰብ ያለ የሙግት አሰማም ዘዴ ምን መምሰል እንዳለበት፣ የሙግት ቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴዎችን በተመለከተና የመሳሰሉት ላይ ያተኩራል፡፡

ክፍል አራት የሞጁሉ የመጨረሻ ክፍል ሲሆን በይግባኝ ጉዳዮች አመራር ዙሪያ ያተኩራል፡፡

# ክፍል አንድ

# የጉዳዮች አመራር በጠቅላላው

የክፍሉ ግቦች

ይህ ክፍል ከተጠናቀቀ በኃላ ሰልጣኞች

- ✓ የፍትሃብሔር ጉዳይ አመራር መርሆዎችን ይገልፃሉ፡፡
- ✓ የፍትሃብሔር ጉዳይ አመራር ቀልጣፋና ፍትሃዊ ለመሆን አስፈላጊ መሆኑን ይገለፃሉ፡፡
- ✓ በጉዳይ ቀደም ብሎ የመግባት ዘዴን ምንነት ይተነትናሉ፡፡
- ✓ በጉዳይ ቀደም ብሎ መግባትና መቆጣጠር ጠቀሚታውን ይዘረዝራሉ፡፡
- ✓ በጉዳይ ቀደም ብሎ ለመግባት ተገቢ የሆኑ ክህሎቶችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ጉዳዮችን ለያይቶ የመምረት ፅንሰ ኃሳብን ይገልፃሉ፡፡
- ✓ ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ዘዴን ይዘረዝረሉ፡፡
- ✓ በፍትሃብሔር ስነስርአት ህጉ ላይ የተቀመጡ የተለያዩ ጉዳይ ማስተናገጃ መንገዶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ✓ የፍትሃብሔር ሙግት ሂደቶችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ቀጠሮ አሰጣጥን በተመለከተ ውጤታማ የሆኑ ዘዴዎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ ለፍትሃብሔር ጉዳዮች አመራር ውጤታማነት አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ይለያሉ፡፡

## በፍትሃብሄር ጉዳይ አመራር መሰረታዊ መርሆች

የፍትሃብሄር አካሄድ አመራር በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፦

- ❖ ፍትሃዊ የሆነ እልባት ለጉዳዮች መስጠት
- ❖ ጉዳዮችን በተቀላጠፈ መንገድ ማስተናገድ
- ❖ የፍርድ ቤትን ሃብቶችን ከፍ ያለ ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል ሁኔታ መጠቀም
- ❖ ጉዳዮችን በዝቅተኛ ወጭና በአጭር ጊዜ ማስተናገድ
- ❖ ጉዳዮች ወደ ሙግት ደረጃ በሚያመሩበት ጊዜ አከራካሪ ጭብጦች በአግባቡ መለየታቸውን ማረጋገጥ፣
- ❖ ማስረጃዎች ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ መቅረባቸውን ማረጋገጥና
- ❖ ዳኛው ለውሳኔ የሚረዱት ሁኔታዎችን ሙሉና የተደራጀ (complete and orgnized) መሆናቸውን ማረጋገጥ።

እነዚህ መርሆዎች በመጨረሻ ግባቸው ትክክለኛ የሆነ ፍትህን ማስፈን ነው። ማናቸውም አይነት የጉዳዮች አመራር መርህም ሆነ ዘዴ ይህንን የመጨረሻ ግብ በማናቸውም ሌላ ግብ ለምሳሌ በፍጥነት፣ ወዘተ መተካት የለበትም።

ውጤታማ ለሆነ የጉዳዮች አመራር የሚከተሉት አስፈላጊ ናቸው፦

- ❖ ውጤታማ የሆነ የጉዳዮች አመራር በትብብር ላይ የተመሰረተ ነው። አብዛኛው ከፍትህ መስጠት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች ከፍርድ ቤቱ ቁጥጥር ውጭ ናቸው። በፍትሃብሄር ጉዳይ ቢያንስ ሁለት ተከራካሪዎች ያሉ ሲሆን ፍርድ ቤት ውጤታማ ስራ ለመስራት የነዚህን ወገኖች ትብብር ይፈልጋል። ፍርድ ቤት ከሂደቱ ተሳታፊዎች በህጉ በተቀመጠው መሰረት ስራቸውን እንዲሰሩ እንዲሁም ዝግጅት እንዲያደርጉ ይጠብቃል፣
- ❖ ውጤታማ የሆነ የጉዳይ አመራር የተጠቃሚውን ፋላጎት ሊያሟሏ የሚችል መሆን አለበት። የተጠቃሚው ፍላጎት ጉዳዮች በጥራትና ፍጥነት እንዲወሰኑ ሊሆን ይችላል።
- ❖ የፍርድ ቤት መሪዎች ቁርጠኝነትና ተነሳሽት

-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------
-----------------------------------------------------------------------------------------------

**የፍርድ ቤት ጉዳይ አመራር ሚና**

ንቁ የሆነ የጉዳይ አመራር የሚከተሉተን ይይዛል፡-

- ❖ ግራ ቀኙን የሚያከራክርውን ጭብጥ ቀደም ብሎ መለየት
- ❖ የምስክሮችን ፋላጎት ቀደም ብሎ መለየት
- ❖ የትኛው ተግባር፣ በማን፣ መቼና በምን አይነት ሁኔታ እንደሚሰራ ማረጋገጥ
- ❖ ለጉዳይ ሂደት የጊዜ ገደብ ማስቀመጥ
- ❖ ጉዳዮች በተቀመጠላቸው አቅጣጫ እየሄዱ ለመሆናቸው መከታተል
- ❖ ማስረጃዎች ግልፅ በሆነ መንገድና በአጭር ጊዜ ውስጥ መቅረባቸውን ማረጋገጥ
- ❖ የጉዳዮችን መዘግየት አለማበራታት
- ❖ በተቻለ መጠን ጎን ለጎን ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራትን ማከናወን
- ❖ ተሳታፊዎች በጉዳዮች አካሄድ ከፍርድ ቤቱ ጋር እንዲተባበሩ ማድረ

# በፍትሃብሄር ጉዳዮች ቀደም ብሎ መግባትና ቁጥጥር ማድረግ

**ከመጀመሪያውን በጉዳዮች ላይ ቁጥጥር የማድረግ የአመራር ዘዴን መዘርጋት**

የፍትሃብሄር ክስ በሚቀርብበት ጊዜ ቀደም ብሎ ከሙግት በፊት ያለውን ሂደት መቆጣጠር ጉዳዮ በፍርድ ቤት የሚያስቆጥረውን ጊዜ ለማሳጣር፣ የሙግቱን ወጭ ለመቆጠብና ፍትሃዊ የሆነ ውሳኔ ላይ ለመደረስ ወሳኝ ነው፡፡

ቀደም ብሎ በጉዳዮች ላይ ቁጥጥር ማድረግ ውጤታማ በሆነ መልኩ በስነስርአት ህጉ ላይ የተቀመጡትን ህጎች፣ ድንጋጌዎችና አካሄዶች እንዲሁም ለዳኛው የተሰጡ የጥንቃቄ ስልጣኖችን (discretionary powers) መጠቀምን ይጨምራል፡፡

በተለይ አንድ የፍትሃብሄር ጉዳይ ተከፍቶ ለዳኛ በቀረበ ጊዜ ዳኛው በስነሰርአት ህጉ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የቀረበው አቤቱታ ለክርክር ተገቢ በሆነ መልኩ መቅረቡን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ እንዲሁም ለቀረበው ክስ መልስ በቀረበ ጊዜ መልሱ የጉዳዩን ጭብጥ ሳይስት ተገቢ በሆነ መንገድ መቅረቡን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ ዳኞች ቀደም ብለው ጉዳይ ውስጥ በመግባት ወደፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን በመተበይ ክርክሮች ተስተካክለው እንዲቀርቡ በማድረግ ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መንገድ ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲሰጡ ሊያደርጋቸው ይችላል፡፡ በመሆኑም ጉዳዮች እንደቀረቡ ወደፊት በሰፊው ይታያሉ በሚል አስተሳሰብ ከማሳለፍ የቀረበውን ጉዳይ ከማለዳው በጥንቃቄ በመፈተሽ፣ ጉድለቶችን በማረም፣ ከባለጉዳዮች ጋር በህጉ አግባብ በመነጋገርና በመግባባት ጉዳዮች በቀላሉ እልባት እንዲያገኙ ትክክለኛውን አቅጣጫ ማስያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**በቡድን የመወያያ ጥያቄዎች 1**

1. አንድ የፍትሃብሄር ክስ ሲቀርብ መዝገቡ ተከፍቶ የቀረበለት ዳኛ የክሱን አቤቱታ ሳያነብ ለተከሰሰው ግለሰብ እንዲደርሰውና መልስ እንዲሰጥበት የሚደረግበት ተለምዶዋዊ አሰራር ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን በመዝገቦች ብዛት ምክንያት ክሶች ሳይነበቡ ለተከሳሽ የሚላኩበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ አሰራር ተገቢ ነውን ትላለህ? ለምን? ችግሩን እንዴት መቅረፍ ይቻላል?

2. ከዚህ ሞጁል ጋር የተያያዙ ትክክለኛ ለፍርድ ቤቱ የቀረቡ የክስ ማመልከቻዎች

ተያይዘዋል፡፡ ማመልከቻዎችን ተመልከትና ችግር ያለባቸውን ለይተህ አውጣ፡፡ ችግር አለባቸው የተባሉት ማመልከቻዎችን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ቀደም ብሎ ለይቶ ሳያወጣቸው ወደ ጉዳይ ውስጥ ቢገባ ኖሮ ምን የአካሄድ ችግር ይፈጠር ነበር ብለህ ትገምታለህ?

ዝርዝር ቴክኒኮች/ዘዴዎች

- አንድ ዳኛ አንድ የፍትሃብሔር ጉዳይ በመዝገብ ቤትና በሬጅስተራሩ በኩል አልፎ ሲቀርብለት የቀረበውን ክስ በጥንቃቀና በጥሞና ማንበብ አለበት፡፡ የቀረበው ክስ የፎርም፣ የግልፅነት ወይም የመንዛዛት ችግር ካለበት ተስተካክሎ እንዲቀርብ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ አብዛኛውን ግዜ ዳኞች እነዚህ ሁኔታዎችን ቀደም ብለው ባለማጣራታቸው፣ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን መልስ ከሰጠና ወደ ክርክሩ ከተገባ በኃላ ይስተዋሉና ጉዳዮች ከወራቶችና አመት በኃላ ወደ ኃላ የሚመለሱበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ ይህ የከራካሪዎቹን ግዜና ገንዘብ እንዲሁም የፍርድ ቤቱን ሃብት የሚያባክን ይሆናል፡፡

- የቀረበው ክስ የክስ ምክንያት ያለው መሆኑን ማጋገጥ አለበት፡፡ የቀረበው ጉዳይ የክስ ምክንያቱን በአግባቡ የማይገልፅ ከሆነ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ማድረግ አለበት፡፡ አንዳንድ የፍትሃብሄር ክሶች የክስ ምክንያት ሳይኖራቸው ወደ ሙግት ይገባና ቀድሞውን መብት የለም በሚል ከወራትና ዓመታት በሃላ ውሳኔ የሚሰጥበት ሁኔታዎች ያጋጥማሉ፡፡ ይህ የፍርድ ቤቱን ውድ ጊዜ፣ የተከራካሪዎችን ጊዜና ገንዘብ የሚያባክን ይሆናል፡፡

- ጉዳዮን ለማስተናገድ የፍሬነገርና የግዛት ስልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ጉዳዮን ለማስተናገድ ስልጣኑ ከሌለው ጉዳዩን ቀደም ብሎ ማሰናበት ይኖርበታል፡፡

- የቀረቡ አቤቱታዎችን (ክስና መልስ) በማንበብ የጉዳዩን ቀላልነት ወይም ውስብስብነት አስቀድሞ መተንበይ ይቻላል፡፡ ውስብስብ ጉዳዮች የዳኛውን ከፍተኛ ጊዜና ጉልበት የሚፈልጉ በመሆኑ የፍርድ ቤቱን ጊዜና ሀብት አስቀድሞ በማቀድ ውጤታማ ለመሆን መንቀሳቀስ ይቻላል፡፡
- የግራ ቀኙን አቤቱታ በቀረበ ጊዜ ወዲያውኑ በማንበብ ማስረጃዎች በአስቸኳይ እንዲሰበሰቡ ማድረግ ይገባል፡፡ በተለይ በተከራካሪ ወገኖች እጅ የማይገኙ ማስረጃዎች እንዲቀርቡ በተጠየቀ ጊዜ ወደ ሙግቱ ከተገባ በኃላ ማስረጃው እንዲቀርብ በሚደረግ ጉዳይ እንዳይጓተት ቀደም ብሎ ማስቀረብ ያስፈልጋል፡፡
- ቀደም ብሎ ጉዳዮችን መፈተሽ (early case screening)
  - ተከሳሽ ከፍርድ ቤት ግዛት ውጭ መሆኑን አለመሆኑን መለየት፡፡
  - ተከሳሹ የሚጠራበትን ወይም መጥሪያ ሊደረሰው የሚችልበትን መንገድ መለየት
  - የምስክሮችን ብዛት መለየት
  - ምስክሮች የሚመጡበትን ቦታ መለየት
  - የኤክስፐርት ምስክሮች መኖራቸውን መለየት
  - ጉዳዩ በማስረጃ ለማስረዳት ከባድ መሆን አለመሆኑን መለየት (ለምሳሌ የጉዳት ካሳ ጉዳዮችን ማስረዳት ከባድ ነው፡፡)
  - የሰነድ ማስረጃዎች መኖራቸውንና ብዛታቸውን መለየት
  - ሌሎች አይነት ማስረጃዎች ለምሳሌ ትይንተ ማስረጃዎች መኖራቸውን መለየት

**የተከራካሪዎች ጠበቆች ወይም ተከራካሪዎቹ ለጉዳዮች ቀደም ብለው ትኩረት እንዲሰጡት ማድረግ**

የፍትሃብሄር ሙግት ያለ ሁሉም ተሳታፊዎች ትጋት ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ የፍትሃብሄር ክርክሮችን ወደ ፍርድ ቤት የሚያመጡት ተሟጋቾች እንደመሆናቸው መጠን በዋነኝነት ለሂደቱ ሃላፊነቱን ሊወስዱ ይገባል፡፡ የሆነ ሆኖ የፍትሃብሄር ጉዳይ ያለ ተሟጋቾች

ተሳትፎ ጉቡን ስለማይመታ ፍርድ ቤቶች ተከራካሪዎችን የማትጋት ተግባር መፈፀም አለባቸው፡፡

በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎች፡-

- አቤቱታቸውን ግልፅና እጥር ምጥን ባለ መልኩ እንዲያቀርቡ ማድረግ አለበት
- እንዲቀርቡላቸው የጠየቋቸውም ማስረጃዎች ተከታትለው ማስቀረባቸውን መከታተል አለበት
- በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ባለው የተለመደ አሰራር አቤቱታዎች ለተቃራኒ ወገን ወይም ሌላ ፍርድ ቤቱ ለሚያዘው ወገን የሚያደርሱት ተከራካሪዎች በመሆኑ እነዚህን አቤቱታዎች በቂ በሆነ ጊዜ ማድረሳቸውን
- ፍርድ ቤቱ የሚሰጣቸውን ማናቸውም ትእዛዞች በጊዜ ገደቡና አጥጋቢ በሆነ ሁኔታ መፈፃማቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡
- ዳተኛ የሆነ ተከራካሪ ወገን በስነስርአት ህጉ በተቀመጠው መሰረት የቅጣት እርምጃዎችን ተግባራዊ ማድረግ (ለምሳሌ ኪሳ መቁረጥ)

## ቡድን መወያያ ጥያቄዎች 2

ከላይ በጉዳይ ቀደም ብሎ ለመግባት ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው ዘዴዎችና ስልቶች ተዘርዝረዋል፡፡

1. እነዚህን ስልቶች አንድ በአንድ ከተመለከትክ በኃላ ጠቃሚታቸው ላይ ተወያይ፡፡
2. ስልቶቹ ከስነስርአት ህጉ ጋር የሚሄዱ ናቸው ብለህ ታምናለህ? ለምን?
3. ፍርድ ቤቶች አሁን ካሉበት ነባራዊ ሁኔታ ስልቶቹን ተግባራዊ ከማድረግ የሚገድቡ ሁኔታዎች አሉን?

## ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት

ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት አንድ ፍርድ ቤት የቀረቡለትን የተለያዩ ጉዳዮች የሚያስፈልጋቸውን የዳኞችና የጠበቆች ትኩረት እንዲሁም ሊጓዙ የሚችሉበትን በቂ ጊዜ መሰረት በማድረግ ተለያይተው ሊታዩበት የሚችሉበት ስርአት የሚዘረጋበት ነው:: ይህ አሰራር ጉዳዩችን በፍርድ ቤት ስልጣን ለያይቶ ከማየት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት ከስልጣን ክፍፍል በላይ ረቀቅ ያለ ነው::

ፍርድ ቤት የሚመጡ ጉዳዮችን ስንመለከት ሁሉም አንድ አይነት አይደሉም:: አንዳንዶቹ ቀላል ሆነው የዳኛውን ጊዜ የማይሻሙ ይሆናሉ:: በሌላ በኩል የተወሰኑ ጉዳዮች ውስብስብ ጭብጥ የሚያስነሱ ብዛት ያላቸው ማስረጃዎች የሚሰማባቸው ይሆናሉ:: እንደዚህ አይነት ጉዳዮች የዳኛ ውን ልዩ ትኩረት፣ ቁጥጥርና ክትትል የሚሹ ይሆናሉ:: በመሆኑም ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ፅንሰ ሃሳብ ሁሉም ጉዳዮች በአንድ አይነት የጊዜ ገደብና መለኪያ እንዲሁም ሂደት መጓዝ የለባቸውም የሚል ነው:: የአንድ ፍርድ ቤት የስራ ፖሊሲ መጀመሪያ የመጣ ጉዳይ መጀመሪያ መስተናገድና መሰናበት አለበት የሚል ከሆነ አሰራሩ ወደ ስህተት ያመራዋል:: ጉዳዩች በተመሳሳይ ሁኔታ የሚስተናገዱ ከሆነ መዘግየት የሌለባቸው ጉዳዮች እንዲዘገዩ ይሆናል::

ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት ሁለት አላማዎች አሉት:: እነሱም:-

1. ጉዳዮች እንደ ባህሪያቸው በተቻለ መጠን በአጭር ጊዜ ውስጥና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ
2. የፍርድ ቤትን ጊዜና ሃብት (resource) እንደ ጉዳዮች ባህሪ ተግባራዊ ማድረግ ናቸው::

በመሆኑም ጉዳዮችን ለያይቶ ለመምራት የሚከተሉትን መቅረፅ ይፈልጋል:-

1. ጉዳዮች እንደ ባህሪያቸው በተለያየ የጊዜ ገደብና ሥነ ሥርአት አከሄድ የሚመሩባቸው የተለያዩ የጉዳዮች መስመሮች (multiple tracks or paths):
2. ጉዳዮች ፍርድ ቤት እንደቀረቡ በየትኛው መስመር መግባት እንዳለባቸው የሚወስንበት ስርአት:
3. ተከታታይ የሆነ በጉዳዮች ላይ ልዩ ስነስርአቱና የጊዜ ገደቡ የተሟላ ስለመሆኑ የክትትል ስርአት:
4. ጉዳዮች በሂደት ባህሪያቸው ሊለወጥ ስለሚችል ጉዳዮችን ለመመለያየት የተጠቀምንበት መመዘኛ ሲለወጥ አስፈላጊውን ማስተከከያ የማድረጊያ ስርአት።

ጉዳዮችን ለያይቶ ለመምራት ዋናው ተግባር ጉዳዮችን ለመለያየት የምንጠቀምባቸውን መመዘኛ ዎች መምረጥ ላይ ነው። ለዚህም የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ይቻላል። አንዳንድ በአሜሪካን አገር ያሉ ፍርድ ቤቶች የጉዳዮችን ከባድነት ማለትም ለምሳሌ ከባድ ወንጀል መሆኑ ወይም አለመሆኑን ግምት ውስጥ ሲያስገቡ ሌሎች የጉዳዮን የገንዘብ መጠን፣ የተከራካሪውን ወገን መከላከያ፣ የጉዳዩን የማስረጃ አይነት እንደ መመዘኛ ይወስዳሉ። አንዳንድ ፍርድ ቤቶች የጉዳዮቹን አይነት በመመልከት ሲከፋፍሉ ሌሎች ደግሞ የጉዳዩቹን አይነትና ከላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ግምት ውስጥ በማስገባት ጉዳዮችን በመለያየት ያስተናግዳሉ። ፍርድ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው መመዘኛዎች ብዛት ያላቸው ሲሆኑ ሁሉም መመዘኛዎች ጠቃሚነታቸው አጠያያቂ አይደለም። የኢትዮጵያ ፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ጉዳዮችን በአይነታቸው: በአስቸኳይነታቸውና በውስብስብነታቸው ለያይቶ የመምራት አሰራርን ይከተላል። በተለይ እያንዳንዳቸው ጉዳዮች ይፈጃሉ ተብሎ የተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ የተለያየ ነው።

ጉዳዩችን ለያይቶ በመምራት የሚከተሉት ጥቅሞች ይገኛሉ:-

1. ጉዳዮችን ለያይቶ በመምራት የፍርድ ቤትን የሰው ሃይል (ዳኞችንና ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችን) ያለ ብክነት በአግባቡ መጠቀም ያስችላል። ጉዳዮችን ቀደም ብሎ በመመልከት በአይነት መለየት ውስብስብ የሆኑ ጉዳዮችን ቀድሞ ለመለየትና ሳይዘገዩ

እልባት ለመስጠት ለመዘጋጀት ያስችላል። እንዲሁም የዳኛ ጊዜ ቀላል በሆኑ ጉዳዮች አላግባብ እንዳይጠፋ ያስችላል። ሆኖም እዚህጋ አንድ መታወቅ ያለበት ነጥብ ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት የፍርድ ቤትን የሰው ሃይል መጨመርን ከአማራጭነት ያስወጠዋል ማለት አይደለም። ሁለቱም አማራጮች ጎን ለጎን መስተናገድ ያለባቸው ናቸው።

2. ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት ጉዳዮች በተፋጠነ ሁኔታ እልባት እንዲገኙ ያደርግል። ጉዳዮችን በመለያየት ስርአት ለተለያዩት የጉዳይ መስመሮች የጊዜ ገደብ የሚበጅላቸው በመሆኑ ጉዳዮች በተመደበላቸው የጊዜ ገደብ የማለቃቸው እድል ከፍተኛ ነው።
3. ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት የፍርዶች ጥራት እንዲጨምር ያደርጋል። ስርአቱ ጉዳዮች ቀደም ብሎው እንዲታዩ የሚያስገድድ በመሆኑ ተከራከሪ ወገኖችም ሆኑ ዳኞች ቀደም ብለው ዝግጅት ያደርጋሉ። ተከራከሪ ወገኞች ቀደም ብለው በመዘጋጀት ክርክር እንዲያደርጉ ስለሚያስገድዳቸው የጉዳዩ ጭብጥ ነጥሮ እንዲወጣ ያደርጋል።
4. በፍትህ ስርአቱ ወሳኝ ሚና ካላቸው አካላት ለምሳሌ ከጠበቆች ማህበሮች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር ይረዳል። ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት ፍርድ ቤቱ በራሱ ብቻ ተነስቶ ተግባራዊ የሚያደርገው አይደለም። ሌሎች በፍትህ ስርአቱ በቀጥታ ተሳታፊ የሆኑ አካላት በሙሉ ስርአቱን ከማቀድ ጀምሮ እስከ አተገባበሩ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል። በተለይ ጉዳዮችን ለመለያየት የሚጠቅሙ መመዘኛዎች የመለየት ስራ በጋራ መስራት ያለበት ነው።
5. ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት የክርክር ወጭን ይቀንሳል። የክርክር ወጭ ስንል የፍርድ ቤትንም ሆነ የተከራከሪ ወገኞችንም ወጭ የሚጨምር ነው። በተለይ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት የጉዳዮችን እድሜ ያሳጥራል። የጉዳዮች እድሜ ባጠረ ቁጥር የተከራከሪ ወገኞች የተለያዩ ወጭዎች እንዲሁም የፍርድ ቤት ወጭ እንደሚቀንስ ግልፅ ነው።

6. ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት የፍርድ ቤት ሂደቶች ተገማችነትን የሚያሰፍን ስለሆነ ፍርድ ቤቶች በህብረተሰቡ ዘንድ ያላቸውን ተአማኒነት ከፍ ያደርጋል፡፡

ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ዘዴን በፍርድ ቤቶች ለማስተዋወቅ የሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ያስፈልጋሉ፡-

1. ጉዳዮችን የመምራት ሃላፊነትን ወውሰድ ያለበት ፍርድ ቤት ብቻ እንደሆነ መገንዘብ፡
2. የፍርድ ቤት ሃላፊዎች ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡ ጉዳዮች በሙሉ አንድ አይነት ባሕሪ የሌላቸው መሆኑንና በተለያየ አሰራር ሊመሩ የሚገባቸው መሆኑም መስማማት አለባቸው፡
3. በፍርድ ስራ ተሳታፊ የሆነ ወገኞች ጉዳዮች በየባህሪያቸው ተለያይተው ሊመሩ የሚገባ ለመሆኑ ሊያምኑበት ይገባል፡
4. በጉዳይ ዋና ዳኛ ወይም ሰብሳቢ ዳኛ የሚባለው የጉዳዮችን ሂደት በተመለከተ የመከታተል ሃላፊነትን ሊረከብ ይገባል
5. በአስተዳደር ስራ ልምድ ያለው ባለሙያ የጉዳዮችን የመለያየት ስራን ዝርዝር ተግባር እንዲያስተባብር ሃላፊነት ሊሰጠው ይገባል፡
6. ስርአቱን ለመደገፍ የመረጃ ዘዴን በተለይም የኮምፒውተር መረጃ ዘዴን ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡

ከላይ የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ስርአትን ለመዘርጋት ፕሮግራም መንደፍ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ስርአቱን ለማዘጋጀት የመጀመሪያ እርምጃ ስርአቱን ለማቀድ ተሳታፊ መሆን ያለባቸውን ተዋናይ መለየት ነው፡፡ በመሆኑም የሚከተሉት በዕቅዱ ተግባር ላይ ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል፡-

- የፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች
- የዞን ፍርድ ቤት ፕሬዝዳነቶች
- ሰብሳቢ ዳኞች

- ዋና ሬጅስተራሮች
- የፍርድ ቤት አስተዳዳሪዎች (አስተዳደርና ፋይናንስ ሃላፊዎች)

ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ስራ እቅድ ከመዘጋጀቱ በፊት በጉዳዮች ጫናና አሰራር ላይ መረጃ መሰብሰብ ይገባል፡፡ በመሆኑም፡-

- የቅርብ ጊዜ የመዝገቦች ብዛትና ትንበያ እንዲሁም የጉዳዮች አይነት፡
- በመታየት ላይ ያሉ መዝገቦች ብዛት፡ አይነትና እድሜ
- ቀጠሮ ተደጋግሞ የሚሰጥባቸው ምክንያቶችና የጉደዮች አይነት
- ጉዳዮች ከተከፈቱበት ጊዜ ጀምሮ የመጨረሻውን እልባት እስኪያገኙ የሚፈጀው ጊዜ የአሁኑና የአምስት አመት መረጃ፡
- ለጉዳዮች እልባት የሚሰጥበት የክርክር ደረጃ፡፡

እነዚህ መረጃዎች ጉዳዮች በምን መልኩ እየተስተናገዱ መሆኑን፡ ችግሩ የቱጋ እንደሆነ በተለይ የቀጠሮ አሰጣጥ ሂደት ለምን ሊደጋገም እንደቻለ ጠቅላላ ስእል የሚሰጡ ይሆናሉ፡፡ እነዚህ መረጃዎች በተጠናከረ መልኩ ሊተነተኑ የሚገባ ሲሆን በተለይ ለጉዳዮች እልባት የሚሰጥበትን ጊዜ ከሰላሳ ቀን በመጀመር በጊዜ ርዝምት በመቶኛ እንዲሁም ጉዳዮች እልባት ያገኙበትን መንገድ ለምሳሌ በእምነት፡ በአማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ ወይም በክርክር ሂደት መሆኑን ማስቀመጥ ይጠቅማል፡፡

በመሆኑም በቀጣይነት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡-

- ክርክር ሳይደረግባቸው እልባት ያገኙ ጉዳዮችና እልባት ያገኙበትን ምክንያት
- ረጅም ጊዜ የሚፈጁና የዳኞችንና የፍርድ ቤቱን ጊዜና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

የጉዳዮች እድሜ መረጃ ጉዳዮች በፍርድ ቤት እልባት ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ አመላካች ነው፡፡ እንዲሁም ከዚህ መረጃ የጉደዮች እድሜ ማጠር ወይም መርዘም ከየትኞቹ የፍርድ ቤት ተግባራት ጋር የተያያዙ መሆኑም መመልከት ይቻላል፡፡ ቀጠሮዎች ለምን ያህል

ጊዜ በተደጋጋሚ እንደሚሰጡ፡ የሚሰጡበትን ምክንያትና በምን አይነት ጉዳዮች ላይ እንደሚሰጡ መፈተሽ ያስፈልጋል። በተለይ ዳኞች ተጨባጭነት የሌላቸው ድርጊት መፈፀሚያ ቀጠሮዎችን ለምሳሌ በአንድ ቀን ውስጥ በበርካታ መዝገቦች ምስክሮችን ለመስማት ወይም ለተከሳሽ የተከላከይ ጠበቃ ሳይመደብለት ጉዳይ ለመስማት ቀጠሮ መስጠታቸው ሊፈተሽ ይገባል።

ከሞላ ጎደል ከላይ የተዘረዘሩትን መረጃ መሰረት አድርጎ ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት እቅድ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባዋል።

በመሆኑም ጉዳዮችን ለያይቶ ለመምራት በቅድሚያ ሊቀመጥ የሚገባው ጉዳዮችን ለመለያየት የምንጠቀምባቸውን መመዘናዎች ናቸው። በአሜሪከን አገር የሚገኙ አብዛኛው ፍርድ ቤቶች የፍጥነት መመዘኛን መሰረት በማድረግ ጉዳዮችን በሶስት መስመሮች ያስኬዳሉ። ሌሎች ፍርድ ቤቶች ፍጥነትንና ሎሎች ልዩ የሆኑ ጉዳዮችን ግምት ውስጥ በማስገባት አምስት ወይም ስድስት ጉዳይ ማስተናገጃ መስመሮችን ያስቀምጣሉ። የሆነ ሆኖ የጉዳዮች መስመሮች ብዛት ከፍርድ ቤቶች ጉዳዮች አይነት የሚወሰኑ ሲሆን በተለይ ቀደም ብለን በተመለከትነው በመረጃ አሰባሰብና ትንተና ውጤት ላይ የሚመሰረት ነው።

የጉዳዮች መስመርና ባህሪያቸውን ለመወሰን የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ያስፈልጋል፡-

- የትኞቹ ጉዳዮች ከሌሎች ፈጥነው እልባት ያገኛሉ? ለምሳሌ በእምነት የሚሰጡ ውሳኔዎች ፈጣኞች ከሆኑ እነዚህ ጉዳዮች ክርክር ካለባቸው ጉዳዮች ሊለዩና ከመደበኛ ጉዳዮች የተለየ የአመራር ስነ ስርአትና የጊዜ ገደብ ሊበጅላው ይገባል።
- የትኞቹ ጉዳዮች ናቸው ብዙ የፍርድ ቤቱንና የዳኞችን ጊዜ የሚፈልጉት? እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ሰፋ ያለ ጊዜ በሚሰጠው የጉዳዮች መስመር እንዲገቡ ይደረጋል።

▪ ልዩ ትኩረትና አመራርን የሚሹ ልዩ ጉዳዮች አሉን? ለምሳሌ የውጭ ቋንቋ ብቻ የሚናገርና የችሎት ሂደትን ለመከታተል የፍርድ ቤቱን የትርጉም አገልግሎት የሚፈልግ ተከሳሽ ያለበት የወንጀል ጉዳይ ልዩ ትኩረትን ይሻል።

በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች መሰረት በማድረግ የእያንዳንዱን የጉዳይ መስመር መመዘኛ ማስቀመጥ ይገባል። በመሆኑም ለምሳሌ ስንቅ የሌለው ቼክ የሰጠ ተከሳሽ ጉዳይ በተለይ ተከሳሹ የሚቀርብበት ማስረጃ ከሞላ ጎደል ቼኩ ብቻ ከሆነ ወይም የጉዳዩ የህግ ጥያቄ ውስብስብ ያልሆነና የማስረጃው ብዛት በጣም አነስተና የሆነ ጉዳይ በተፋጠነ የጉዳይ መስመር (expedited track) እንዲታይ ማድረግ ነው። ለምሳሌ እንደ ኮንስትራክሽን ያሉ ብዙ ክስና ብዛት ያለው ማስረጃ ያለበት ጉዳይ በውስብስብ የጉዳይ መስመር (complex track) ሊታይ ይገባዋል። የማስረጃው ብዛትና የጉዳዩ ውስብስብነት መጠነኛ የሆነ ጉዳይ በመደበኛ የጉዳይ መስመር (standard track) እንዲታይ ማድረግ ያስፈልጋል። በመሆኑም ጉዳዮች በፍርድ ቤት በሚጀመሩበት ጊዜ በተለያዩ መስመሮች ለማስገባት የጉዳዮቹን ባህሪ ለመወሰን መረጃ መሰብሰብ ያስፈልጋል። ይህም ጉዳዮች ለፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ በሚያቀርበው ፎርም ላይ ተከራካሪ ወገኖች መረጃ እንዲሰጡ ይደረጋል።

መመዘኛዎች ከተለዩና የጉዳዮች መስመሮች ከተወሰኑ በሃላ በእያንዳንዱ መስመር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው ስነስርአቶች ሊወሰኑ ይገባል። በመሆኑም ጉዳዮችን ሊያፋጥኑ የሚችሉ አሰራሮች መቀጠል ያለባቸው ሲሆን በዚያው ልክ ጉዳዮችን የሚያጓትቱ አሰራሮች ሊወገዱ ይገባል። እንዲሁም ጉዳዮን ሊያፋጥኑ የሚችሉ ሌሎች ስነ ስርአቶች መጨመር ከለባቸው እንዲጨመሩ መደረግ አለበት።

ባጠቃላይ ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ፕሮግራም ተነድፎ ተግባራዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን በአግባቡ ተግባራዊ ለመሆኑ ክትትል ይፈልጋል። በተለይ ከፍትህ ስርአቱ ተሳታፊዎች ጋር ቋሚ የሆነ ግንኙነትና ትብብር ይፈልጋል። በተለይ ተግባራዊ የተደረገው ፕሮግራም ጥሩና መጥፎ ጎኖች ሊመረመሩ ይገባል።

**የቡድን መወያያ ጥያቄዎች 3**

ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ዘዴን በፍርድ ቤት ተግባራዊ ለማድረግ በፍርድ ስራ የሚሰሩ በርካታ አካላትን ተሳትፎ ይፈልጋል፡፡ እንዲሁም ፕሮግራሙን ነድፎ ተግባራዊ ለማድረግ ሰፊ የጥናት ግዜን ይጠይቃል፡፡ በተለይ የፍርድ ቤት መሪዎችን ቁርጠኝነትና ተነሳሽትን ይፈልጋል፡፡ ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ዘዴን ጠቀሜታ ከላይ ለመመልከት ሞክረናል፡፡

- ❖ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ የሚያዘጋጀው ስርአት ሳይኖር ዳኛው ወይም አንድ ችሎት የሚቀርቡለትን ጉዳዮች ለያይቶ ለመምራት ይችላል ብለው ያምናሉን?
- ❖ በብዙ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አመታዊ እቅድ እንዲያዘጋጁ ይጠየቃሉ፡፡ በዚህ ሂደት የሚቀርቡላቸውን ጉዮች ለያይተው መምራት የሚችሉበትን እቅድ ማዘጋጀት ይችላሉን?

## የፍትሃብሄር ስነስርአት ህጉና ጉዳዮችን ለያይቶ መምራት

ከላይ የተመለከትነው ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ዘዴ በፍርድ ቤት ደረጃ እቅድ ተነድፎ ተግባራዊ የሚደረግበት ስርአት ነው፡፡ ይህ አሰራር ከፍርድ ቤቱ ከፍተኛ አመራር ወደ ታች የሚወርድ በመሆኑ ምናልባት በአፈፃፀም ረገድ ጊዜን ሊፈጅ የሚችል በመሆኑ አልያም ጭራሹኑ አሰራሩ ተግባራዊ ላይደረግ ስለሚችል ዳኞች የራሳቸውን ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ዘዴ ነድፈው ተግባራዊ ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው ጉዳዮች በአይነት፣ በውስብስብነት፣ በአስቸኳይነት ወዘተ ይለያያሉ፡፡ ይህንን ልዩነት መሰረት በማድረግ ጉዳደችን መምራት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ 30 ምስክሮች ያሉበት ጉዳይ እንደ መደበኛ ጉዳይ ታይቶ ከሌሎች መዝገቦች ጋር አብሮ ሊታይ

አይገባውም፡፡ ዳኞች ምስክሮችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ሰምተው ሊጨርሱ የሚችሉበትን ስልት ቀይሰው ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይ ከእንዲዚህ አይነት መዝገብ ጋር ሌሎች መዝገቦች ሊደረቡ እንደማይገባ ግልፅ ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ የቼክ ጉዳይ ከውርስ ጉዳይ ጋር በእኩል አሰራር መስተናገድ የለበትም፡፡ ለውርስ ጉዳይ የሚሰጠው ቀጠሮ ሊረዝም የሚችል ሲሆን ለቼክ ጉዳይ የሚሰጥ ቀጠሮ ማጠር ይገባዋል፡፡

በሌላ በኩል የፍትሃብሄር ስነስርአት ህጉ በዋነኝነት ጉዳዮች በሶስት መንገዶች ያስተናግዳል፡፡

**መደበኛ ስነስርት**

**ቅድመ ሙግት መስማት** (pre-trial stage)

1. የክስ አቤቱታ (ከሰነድና ከፅሑፍ ማስረጃ እንዲሁም ከማስረጃ ዝርዝር ጋር) ይቀርባል፡፡
2. ተከሳሹ የመከላከያ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ ይታዘዛል፡፡
3. የመከላከያ መልስ (ከሰነድና ከፅሑፍ ማስረጃ እንዲሁም ከማስረጃ ዝርዝር ጋር) ይቀርባል፡፡
4. የመከላከያ መልሱ ከቀረበ በኃላ የጽሑፍ ክርክሩ ያቆማል
5. የፅሑፍ ክርክሩ ካቆመ በኃላ ክሱን ለመስማት ይቀጠራል፡፡
6. በተቀጠረው ቀን በላጉዳዮች ራሳቸው ወይም ወኪሎቻቻው ይቀርባሉ፡፡
7. ባለጉዳዮች ከፅሑፍ አቤቱታቸው ጋር ያላቀረቡትን የፅሑፍ ማስረጃ ይዘው ይቀርባሉ፡፡
8. የጽሑፍ ማስረጃ ሁሉ በባለጉዳዮች ወይም በፍርድ ቤቱ ትፅዛዝ ተጠቃሎ ይገባል፡፡
9. ፍርድ ቤቱ ባለጉዳዮቹን ወይም ወኪሎቻቸውን ይመረምራል፡፡
10. የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከቀረበ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡
11. በተደረገው ምርመራ ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ካመነ ወዲያው ውሳኔ ይሰጣል፡፡
12. ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ካላመነ የክርክሩ ጭብጥ ይያዛል፡፡

**ሙግት መስማት** (trial stage)

13. ጭበጡ ከተመሠረተ በኃላ ክርክሩን መስማትና ማስረጃ መመርመር ይቀጥላል፡፡

14.ለሁለቱም ወገን ምስክሮች መጥሪያ ይላካል፡፡

15.የሁለቱም ወገን ምስክሮች  ተሟልተው ይቀርባሉ፡፡

16.ከሳሹ  (በተወሰኑ ሁኔታዎች ተከሳሹ) ሙግቱን ይከፍታል፡፡

17.ሙግቱን የጀመረው ወገን ምስክሮቹ የሚመስክሩለትን ነጥብ በአጭሩ ያስረዳል፡፡

18.ምስክሮች  እውነት ለመናገር ይምላሉ ወይም እውነት እንደሚናገሩ ያረጋግጣሉ፡፡

19. ሙግቱን የጀመረው ሰው ምስክሮቹን አንድ በአንድ  አቅርቦ ዋና ጥያቄ ይጠይቃል፡፡ ሌላው ወገን መስቀለኛ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ የጀመረው ወገን የማጣሪያ ጥያቄ ይጠይቃል፡፡ ፍርድ ቤቱ በማንኛውም ሰዓት አስፈላጊ የሆነ ጥያቄ ይጠይቃል፡፡

20.ሙግቱን የከፈተው ወገን ምስክሮቹን አሰምቶ ከጨረሰ በኃላ ሌላኛው ወገን ምስክሮቹ የሚያስረዱለትን የመከላከያ ነጥብ በአጭሩ አስረድቶ በተመሳሳይ ሁኔታ ምስክሮቹን ያሰማል፡፡

21.ማስረጃ የመስማቱ ሂደት ሲጠናቀቅ ግራ ቀኙ የመዝጊያ ቃላቸውን ይሰጣሉ፡፡

22.በመጨረሻም ፍርድ ቤቱ የፍርድ ውሳኔውን ይሰጣል፡፡

## አጭር ስነስርአት (summary Procedures)

1. ከፍ/ብ/ስ/ስ/ቁ/ 284 እስከ 292 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል፡፡
2. በዚህ ሥርዓት መሠረት ክስ ሊቀርብ የሚችለው በቁ. 284 ሥር በተዘረዘሩ ጉዳዮች ብቻ ነው፡፡
    - ምንጩ ግልፅ ውል፣ የሃዋላ ሰነድ፣ ቼክ፣ የተስፋ ሰነድ ወይም ቀላል ውል የሆነ ልኩ የታወቀ ገንዘብን የሚመለከት ክስ በሆነ ግዜ
3. ማመልከቻው በመኃላ ቃል ተደግፎ መቅረብ አለበት (284(ሐ))፡፡ የመኃላ ቃሉ ተከሳሹ ለነገሩ ምንም ዓይነት መከላከያ እንደሌለው ከሳሽ የሚያምን መሆኑን መግለፅ አለበት፡፡
4. ፍ/ቤቱ ማመልከቻውን ከተቀበለ በኃላ ለተከሳሹ መጥሪያ እንዲደርሰው ያዛል (ቁ. 285(1)) ፡፡

5. ተከሳሹ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ፍ/ቤቱን ጠይቆ ካላስፈቀደ በቀር መከላከያ ሊያቀርብ አይችልም (ቁ. 285(1))፡፡
6. ተከሳሹ ቀርቦ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ለፍ/ቤቱ ካላመለከተ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል(ቁ. 285(2))፡፡
7. ለመከላከል ፈቃድ እንዲሰጥ የሚቀርበው ማመልከቻ በቁ. 286 መሠረት በመኃላ ቃል ተደግፎ መቅረብ አለበት፡፡
8. ተከሳሹ ለመከላከል እንዲፈቀድለት ያቀረበው ማመልከቻ ተቀባይነት ካጣ ወዲያው ለከሳሹ ይፈረዳል (ቁ. 287)፡፡
9. ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ ግን ተከሳሹ መከላከያ እንዲያቀርብ ይፈቀድለታል፡፡ ክርክሩም የሚመራው ፍ/ቤቱ በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ወይም እንደመደበኛው ክስ በቀጥታ ሊሆን ይችላል(ቁ. 290 እና 291)፡፡
10. ፍርድ ከተሰጠ በኃላ ለተከሳሹ የተላከው መጥሪያ በአግባቡ ያልደረሰው ከሆነ ፍ/ቤቱ ፍርዱ ከመፈፀም እንዲቆይ በማድረግ ተከሳሹ ቀርቦ እንዲከላከልና ስለ ጉዳዩም አፈፃፀም ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ለመስጠት ይችላል(ቁ.292)፡፡

## የተፈጠነ ሥነ ሥርዓት (Accelerated Procedure)

1. ከፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 300 እስከ 314 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል፡፡
2. በመሠረቱ ይህ ሥርዓት የሚፈቀደው በቁ. 305 እና 307-314 በተዘረዘሩት ጉዳዮች ነው (ቁ. 300(11))፡፡
3. ሆኖም ግን ጉዳዩ በዚህ ሥርዓት መታየት የለበትም ብሎ ፍ/ቤቱ መከልከል የሚችል ሆኖ ከላይ በተጠቀሱት ቁጥሮች ከተደነገጉት ጉዳዮች ውጪም ቢሆኑ ሌሎች ጉዳዮች በዚህ ሥርዓት መታየት ይችላሉ (ቁ. 300 (1))፡፡
4. ማመልከቻው የሚቀርበው በቁ. 301 የተደነገገውን ሁኔታ አሟልቶና በመኃላ ቃል ተደግፎ መሆን አለበት፡፡
5. ማመልከቻው በቁ. 302 ሥር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ውድቅ ሊሆን ይችላል፡፡

6. ማመልከቻው ተቀባይነት ካገኘ ፍ/ቤቱ ውሳኔ የሚሰጠው በማመልከቻው ላይ በተገለፀው እና አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር ያቀረባቸውን ሰነዶችና የፅሑፍ ማስረጃዎች መሠረት በማድረግ ነው(ቁ. 303(2) እና 301(3))፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ የሆነ ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል (303 (3)) ፡፡
7. ሕጉ በሌላ አኳኃን እንዲፈፀም የሚያዝ ካልሆነ በቀር በዚህ ሥርዓት በሚሰጠው ፍርድ ላይ ይግባኝ ለማቅረብ አይቻልም (ከቁ. 309-311 ከተመለከተው በቀር) (ቁ. 306 (1))፡፡
8. ይግባኝ የሚፈቀድ ከሆነ ይግባኙ ፈርድ በተሰጠ በ15 ቀን ውስጥ መቅረብ አለበት (ቁ. 306 (2))፡፡

ከላይ ሶስቱን መሰረታዊ የፍትሃብሄር አካሄዶች የተመለከትን ሲሆን ዳኞች እነዚህን የፍትሃብሄር አካሄዶች በአግባቡ ሊጠቀሙባቸው ይገባል፡፡

**የቡድን መወያያ ጥያቄዎች 4**

1. የፍትሃብሄር ህጉ የሚያስቀምጣቸውን የጉዳይ አመራር መንገዶች (case tracks) አንድ በአንድ በማንሳት በመንገዶቹ መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ተወያዩበት፡፡
2. ዳኞች ጉዳዮች በአንዱ መንገድ እንዲመጡ የማስገደድ ስልጣን አላቸውን?
3. በተለምዶ አብዛኛው የፍትሃብሄር ጉዳዮች የሚቀርቡት በመደበኛ ስነስርአት ሲሆን ለዚህ ችግሩ ምንድነው ብለው ያምናሉ?

## ውጤታማ የሆነ የቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴ

የክስ መስማት፡ ሙግት ወይም ሌላ ማናቸውም ይፈፀማል የተባለ ድርጊት ወይም ሂደት ይሰማል ወይም ይፈፀማል በተባለበት ቀን ሊጀምር ወይም ሊፈፀም ይገባል፡፡ በተከራካሪ ወገኖችና በፍርድ ሂደቱ ተሳታፊ የሆነ ወገኖች ላይ አንድ ጉዳይ መሰማት ይጀመራል በተባለበት ቀን እንደሚሰማ እርግጠኛ ስሜት መፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የፍርድ ቤት ስራና ውጤታማነት በእጅጉን ከተከራካሪ ወገኖች የጉዳዮች ዝግጅት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዩ ይሰማል በተባለበት ቀን ጉዳዩ እንደማይሰማ እርግጠኛ ስሜት ካላቸው ፍርድ ቤት ተዘጋጅተው አይመጡም፡፡ ምስክሮቻቸውን ወይም ሌሎች ማስረጃዎቻቸውን ለማቅረብ ወጭና መጉላላት ስላለው እነዚህንም አያቀረቡም፡፡ በመሆኑም ጉዳዮች ይጓተታሉ፡፡

በተለይ ጥብቅና ታማኝ የሆነ ቀጠሮ ጉዳዮች በቅድሚያ በስምምነት እንዲያልቅ ያደርጋል፡፡ በአሜሪካን አገር በተደረገ ጥናት የፍርድ ቤቶች ጥብቅና ታማኝ ቀጠሮ ከጉዳዮች በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ከማግኘት ጋር ቀጥታ የተገናኘ መሆኑን ያሳያሉ፡፡

የጥብቅና ተአማኒነት ያለው ቀጠሮ ለማምጣት መደረግ ያለባቸው፡-

- የጉዳይ መስሚያ ቀን ከመወሰን በፊት ጉዳዮች በስምምነት እንዲያልቁ ማበረታታት
- ተፈፃሚ የሚሆን የአጀንዳ አያያዝ ዘዴን ማስተዋወቅ
- በቀጠሮ አሰጣጥ ላይ ጥብቅ የሆነ ፖሊሲ ማስቀመጥ
- ተጠባባቂ ዳኛ መመደብ

ጉዳዮች ወደ ክስ መሰማት ከመሄዳቸው በፊት በስምምነት እንዲያልቁ ማመቻቸት ለጉዳይ መስሚያ በቂ ጊዜን ይሰጣል፡፡ በተለይ ጉዳዮች ወደ ፍርድ ቤት እንደቀረቡ ዳኞች ጉዳዮች ወደ ሙግት መስማት ደረጃ ሳይደረሱ በስምምነት ወይም በሌላ አማራጭ የሙግት መፍቻ ዘዴ እልባት እንዲያገኙ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በመሆኑም አብዛኛው ጉዳዮች ከመጀመሪያውኑ

እልባት ያገኛሉ፡፡ በአሜሪካን አገር 96 በመቶ የሚሆኑ የወንጀል ጉዳዩችና 97 በመቶ የሚሆኑ የፍ/በሄር ጉዳዮች ወደ ክስ መሰማት ሳይሄዱ በስምምነት ወይም በሌላ የሙግት መፍቻ ዘዴዎች ያልቃሉ፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች 3-4 በመቶ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ነው ክርክሮችንና ሙግቶችን የሚያስተናግዱት፡፡ ይህም ፍርድ ቤቶች በጉዳዮች ስለ ማይጨናነቁ እእያንዳንዱን አከራካሪ ጉዳይ ዘና ብለው ለማስተናገድ ሰፊ ግዜ ይኖራቸዋል፡፡ ጉዳዮች ተደራርበው ስለማይቀጠሩ በአገራችን እንደተለመደው ሌላ ተለዋጭ ቀጠሮ ለመስጠት አይገደዱም፡፡ በመሆኑም ጉዳዮች ይሰማሉ ወይም ምስክሮች ይሰማሉ ወይም ማናቸውም ይፈፀማሉ የተባሉ ድርጊቶች በተመደበላቸው ወይም በተያዘላቸው ግዜ ይፈፀማሉ፡፡

ተፈፃሚ የሚሆን የአጀንዳ አያያዝ ዘዴ አንድ ችሎት በተወሰነ ጊዜ (በአንድ ቀን፡ በአንድ ሳምነት፡ ወዘተ) ምን ያህል ጉዳዮችን ሊቀጥር እእንደሚገባ የሚገልፅ ነው፡፡ የእለት፣ የሳምንት ወይም የወር አጀንዳ በቂ ወይም መጠነኛ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ከመጠን በላይ ማነስም ሆነ መብዛት የለበትም፡፡ የፍርድ ቤት አጀንዳ ከመጠን በላይ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ሁሉንም ጉዳዮች መስማት ስለማይችል የተወሰኑ ጉዳዬች ለሌላ ጊዜ መቅጠር ግድ ስለሚል የተከራካሪወዎችን እርግጠኛ ተስፋ የሚጎዳ ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አጅንዳዎች በጣም አነስተኛ በሆኑ ጊዜ በተለይ የአንድ መዝገብ ጉዳይ ለመስማት ቀጠሮ ተይዞ መስማት ባልተቻለ ጊዜ የዳኞች ጊዜ የሚባክን ይሆናል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቶች በአጀንዳ አያያዝ ላይ በሁለቱም ፅንፎች ያለውን ችግር በሚያስወግድ መልኩ ሊሰሩ ይገባል፡፡

ጥብቅና ተአማኒነት ያለው ቀጠሮ ለመፍጠር በቀጠሮ አሰጣጥ ላይ ጥብቅ የሆነ ፖሊሲ መከተል ያስፈልጋል፡፡ በጣም ልል የሆነ የቀጠሮ ፖሊስ ተከራካሪ ወገኖች ሳይዘጋጁ እንዲመጡ ያበረታታል፡፡

ተጠባባቂ ዳኛ መመደብ ጉዳዮች ለሌላ ጊዜ እንዳይቀጠሩ ወይም እንዳይተላለፉ ያደርጋል፡፡ የፍርድ ቤት ስራ ብዙ እርግጠኛ ለመሆን በማይቻሉ ክስተቶች የተሞላ ነው፡፡ ዳኞች ሊታመሙ

ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የቀጠሩትን መዝገብ ለማስተናገድ የማይችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከመዝገቦች ብዛትም ሁሉንም ጉዳዮች ማስተናገድ አይቻል ይሆናል፡፡ በእንደዚህ ሁኔታ ቀጠሮ መስጠት ጥብቅ በሆነ ቀጠሮ ላይ አሉታዊ ውጤት ስላለው ተጠባባቂ ዳኛ ይህንን ችግር ሊፈታ ይችላል፡፡

ዳኛ እንደማንኛውም መንግስት ሰራተኛ በቀን 8 ሰዓታት በሳምንት 5 ቀን ይሰራል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ የጉዳዮችና የባለጉዳዮች ፍሰት የማያቋርጥ በመሆኑ ዳኛ ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም መቻል አለበት፡፡ ዳኞች ጉዳዮችን በችሎት ከመዳኘነት በተጨማሪ

- የአመራር፣
- ባለጉዳዮችን የማስተናገድ፣
- ውሳኔ የመፃፍ፣
- ጉዳይ የማጣናት ወዘተ ተግባራት እንዲፈጽሙ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በመሆኑም ግዜያቸውን በአግባቡ ከፋፍለው ውጤታማ ስራ መስራት አለባቸው፡፡ ዳኞች የሳምንቱን ቀናት በሙሉ ችሎት በማስቻል ማሳለፍ የለባቸውም፡፡ ዳኞች በሳምንት ከሶስት ቀን በላይ ችሎት ባያስችሉ ይመረጣል፡፡ ከዚህ ውጭ ለመዝገብ ጥናት፣ ውሳኔ ለመፃፍ፣ አቤቱታዎችን ለማስተናገድ ጊዜ ሊመድቡ ይገባል፡፡ በተለይ በችሎት ላይ ክስ ብሎም ክርክር ለመስማት ከፍተኛ ዝግጅትን የሚፈልግ በመሆኑ ጊዜ ሊመደብ ይገባል፡፡

ከቀጠሮ ጋር በተያያዘ ፍርድ ቤቱ ለሚከተሉት ተግባራት ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡-

- በእያንዳንዱ ቀጠሮ ፍርድ ቤቱ አንድ አላማን ከግብ ለማድረስ ማለም አለበት
- አላስፈላጊ ቀጠሮዎች መወገድ አለባቸው

- ❖ ማናቸውም ቀጠሮ ግልፅ የሆነ ግብና ግቡን ለማሳካት የሚበቃ አጭር ጊዜ ሊኖረው ይገባል፡፡
- ❖ ጉዳዩ የሚቀጠር ከሆነ የጉዳዮ መሰማት የሚቀጥልበት ገልፅ አቅጣጫ መቀመጥ ይኖርበታል፡፡

**የቡድን መወያያ ጥያቄዎች 5**

1. ዳኞች ቀጠሮዎችን በዘፈቀደ ይሰጣሉ በሚል ይወቀሳሉ፡፡ ይህንን ይቀበሉታልን? ለምን?
2. ውጤታማ የሆነ የቀጠሮና አጀንዳ አያያዝ ዘዴ ምን አይነት ነው ብለው ያስባሉ?

# ክፍል ሁለት

# ቅድመ ሙግት

**የክፍሉ ግቦች**

ይህ ክፍል ከተጠናቀቀ በኃላ ሰልጣኞች

- ✓ የፍትሃብሄር ጉዳይ ቅድመ ሙግት ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- ✓ በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ክስ ለመስማት መደረግ ያለበትን ዝግጅት ይገልፃሉ፡፡
- ✓ የክስ መስማትን ምንነት ይገልፃሉ፡፡
- ✓ በክስ መስማት ሂደት መደረግ ያለባቸውን ስራዎች ይለያሉ፡፡
- ✓ ክስ ይሰማሉ፡፡
- ✓ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር ይሰማሉ፡፡
- ✓ ለመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ብይን ይሰጣሉ፡፡
- ✓ ጭብጥ ለመመስረት አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ይለያሉ፡፡
- ✓ የጭብጥ አመሰራረት ዘዴን ይለያሉ፡፡
- ✓ ጭብጥ ይመሰርታሉ፡፡

## መግቢያ

የቅድመ ሙግት ሂደት (pretrial stage) የመጀመሪያው የፍትሃብሄር ክርክር ሂደት ነው ሊባል ይችላል፡፡ በዚህ ግዜ ተከራካሪ ወገኖች አቤቱታና የሰነድ ማስረጃዎቻቸውን ይለዋወጣሉ፡፡ እንዲሁም ክስ መስማት በሚባለው ሂደት ፍርድ ቤቱ የተከራካሪዎች ምርመራ በማድረግ አቤቱታዎችን ያጣራል፣ ለመቃወሚያዎች መፍትሄ ይሰጣል እንዲሁም ጭብጥ ይመሰረታል፡፡ ግራ ቀኙ የሚከራከሩበት ነጥብ ከሌለም ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## ክስ ለመስማት መደረግ ስላለባቸው ቅድመ ዝግጅቶች

በፍትሃብሄር ክርክር ሂደት ክስ መስማት የመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ነው፡፡ የጉዳዩ የክርክር አቅጣጫ የሚወሰንበት በመሆኑ ወሳኝ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም ዳኞች በቀነ ቀጠሮ በቂ ዝግጅት አድርገው ጉዳዮን እንዲያስተናግዱ ይጠበቅባቸዋል፡፡

**<u>የፅሑፍ ክርክር የማቀባበል ሥራን ማጠናቀቅ</u>**

ሀ. ፅሑፍ የማቀባበል ሥራ የሚጠናቀቀው ከሳሹ ባቀረበው የክስ አቤቱታና የፅሑፍ ማስረጃ ላይ ተከሳሹ የመከላከያ መልሱንና የፅሑፍ ማስረጃውን ሲያቀርብ ነው፡፡

ለ. ተከሳሹ ባቀረበው የመከላከያ መልስ ላይ ከሳሹ የመልስ መልስ እንዲሰጥ ሊፈቀድለት አይገባምም፡፡

ሐ. ፅሑፍ የማቀባበሉ ሥራ ከተጠናቀቀ በኃላ በቁ. 241 እና በተከታዮቹ መሠረት

ተከራካሪዎቹን መመርመርና የክርክሩን ጭብጥ የመያዝ ሂደት ይቀጥላል፡፡

**ከፍትሃብሄር መርሃ ችሎት**

ክስ ከመሰማቱ በፊት ዳኞች የሚከተለውን ዝግጅት መፈፀም ይገባቸዋል፡-

- የግራ ቀኙን አቤቱታዎች በጥንቃቄ ማንበብ
- የሰነድ ማስረጃዎቹን በአግባቡ መፈተሽ
- አግባብነት ያላቸውን አግባብነት ከሌላቸው የሰነድ ማስረጃዎች መለየት
- ክሱም ሆነ መልሱ ጉድለት የሌለበት መሆኑን በድጋሚ ማረጋገጥ
- ሊቀርቡ የሚገባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ተጠቃለው መግባታቸውን ማረጋገጥ
- ግራ ቀኙ የሚያከራክራቸውን ነጥብ መለየት
- በግራ ቀኙ አቤቱታ ውስጥ ገልፅ ያልሆነውን መለየት፣ ለግራ ቀኙ የሚቀርብ የማብራሪያ ጥያቄ ማዘጋጀት
- ግራ ቀኙ ካቀረቧቸው የሰነድ ማስረጃዎች በግራ ቀኙ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን መለየት
- የግራ ቀኙን አቤቱታዎች በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ለማብራራት ማስታወሻ መያዝ
- ተከሳሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ እንደሆነ መለየት፣ መቃወሚያዎቹ ተቀባይነት ያላቸው እንደሆነ መፈተሽ

**የፅሑፍ ማስረጃ ስለሚቀርብበት ጊዜና ሁኔታ**

ሀ. የፅሑፍ ማስረጃዎች በሙሉ ክርክሩን መስማትና ምስክሮችን መመርመር

ከመጀመሩ በፊት ተጠቃለው መግባት አለባቸው፡፡

ለ. በመጀመሪያ ደረጃ ከሳሹ ከክስ ማመልከቻው ጋር ተከሳሹ ደግሞ ከመከላከያ መልሱ ጋር ይጠቅመናል የሚሉትንና በእጃቸው የሚገኙትን ወይም ሊያቀርቡ የሚችሉትን የጽሑፍ ማስረጃ በሙሉ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው (ቁ. 223(1)) (ለ) እና 234 (1)፡፡

ሐ. በሁለተኛ ደረጃ ተከራካሪ ወገኖች ለማቅረብ የሚችሉትንና ይጠቅማናል የሚሉትን ወይም ፍርድ ቤቱ እንዲቀርብ የጠየቀውንና አስቀድመው ፍርድ ቤት ያላቀረቡትን የፅሑፍ ማስረጃ ሁሉ በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ማቅረብ አለባቸው (ቁ. 137 (1)) ፡፡

መ. ማንኛውም አቤት ባይ ሰነዶችን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀነ ቀጠሮው በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ካላቀረበ በቀር ማስረጃዬ ከፍርድ ቤቱ መዝገብ ጋር ይያያዝልኝ ወይም ለማቅረብ ይፈቀድልኝ በማለት ለማመልከት አይችልም (137(3)፡፡

ሠ. መቅረብ የሚገባቸው ማስረጃዎች ከተከራካሪዎች ወገኖች ባንዳኛው ጉድለት ወይም በቂ ባልሆነ ምክንያት ሳይቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል (ቁ. 256(1))፡፡

ረ. ከላይ በ “መ” እና “ሠ” ሥር የተጠቀሱት አጠቃላይ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ከአቤቱታ ጋር ወይም በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ያልቀረበ የፅሁፍ ማስረጃ በሌላ ጊዜ ሊቀርብ የሚችልበት ልዩ ሁኔታዎች (exceptions) አሉ፡፡ እነዚህም፡-

1. ፍርድ ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም በተከራካሪዎች ወገኖች አመልካችነት በሌላ ፍ/ቤት ዘንድ የሚገኝ መዝገብ ወይም የጽሑፍ ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል (ቁ.148 (11))፡፡
2. ማስረጃዎቹ ሳይቀርቡ የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍርድ ቤቱ ከተረዳ ስለ ክርክሩ አወሳሰንና ማስረጃ ያለመቅረቡ ስላስከተለው ኪሳራ ተገቢ መስሎ የታየውን ትፅዛዝ በመስጠት ነገሩ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ይወስናል (ቁ. 256 (1)፡፡ (ማስረጃው እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል፡፡)

3. አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ከመያዙ በፊት በተከራካሪዎች ያልቀረበን የፅሑፍ ማስረጃ በትዕዛዝ አስቀርቦ መመርመር ይችላል (ቁ. 149 (1) )፡፡
4. ክርክሩ በሚሰማበት በማናቸውም ግዜ ፍርድ ቤቱ በተከራካሪዎቹ ያልቀረበ ነገር ግን ለክርክሩ ጠቃሚ የሆነ የፅሑፍ ማስረጃ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል (ቁ.164)፡፡
5. ምስክሮችን መስቀለኛ ጥያቄ ለመጠየቅ ወይም ምስክሩ ነገሩን ለማስታወስ እንዲችል የሚቀርብ የጽሑፍ ማስረጃ በመጀመሪያ በይቀርብም ክርክሩ በሚስማበት ጊዜ መቅረብ ይችላል (137 (4)) ፡፡

**ከፍትሃብሄር መርሃ ችሎት**

# ክስን የመስማት ዘዴ

የመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ክስ የሚሰማበት ቀን ነው፡፡ ዳኛው የግራ ቀኙን አቤቱታና ማስረጃዎች መርምሮ ጉድለት ያለበት ከሆነ ክሱን ከመስማቱ በፊት ጉድለቱ እንዲሟላ ማድረግ አለበት፡፡ ለምሳሌ በቀረበው ክስ ወይም መልስ ላይ መሰረታዊ ጉድለት ከተስተዋለ ክስ ከመሰማቱ በፊት አቤቱታዎቹ እንዲሻሻሉ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም የሰነድ ማስረጃዎች በዚህ ቀን ካልቀረቡ ያልቀረቡበትን ምክንያት በማጣራት በቂ ምክንያት ካለ ክሱ ከመስማት ማስተላለፍ ይኖርበታል፡፡

በዚህ ቀጠሮ የዳኛው ሚና ጎልቶ የሚወጣበት ነው፡፡ በተለምዶ የመጀመሪያው ቀን የቃል ክርክር ቀን ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ተከራካሪዎች ክርክርቸውን በአቤቱታቸው ላይ ያቀረቡትን ደግመው በማቅረብ የሚሟገቱበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ የክስ መስማት ቀን ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙን የሚመረምርበት እንጂ የቃል ክርክር የሚደረግበት አይደለም፡፡

ፍርድ ቤቱ ግራ ቀኙ መቅረባቸውን ካረጋገጠ በኃላ የግራ ቀኙን አቤቱታ በንባብ ማሰማት አለበት፡፡ ሆኖም የግራ ቀኙ አቤቱታዎች የተንዛዙ ሊሆኑ የሚችሉ በመሆናቸው በተለቻለ መጠን አጠር አድርጎ ለማብራራት ቢሞክር ይመረጣል፡፡

ፍርድ ቤቱ ተከሳሹን መሰረታዊ የሆኑትን ፍሬነገሮች የሚያምን ወይም የሚክድ መሆኑን መጠየቅ አለበት፡፡ ከዚ ውጭ በግራ ቀኙ አቤቱታዎች ውስጥ ግልፅ ያልሆኑ፣ አሻሚ የሆኑና ሌሎች ነጥቦች ላይ ማብራሪያ መጠየቅ አለበት፡፡ እንዲሁም ግራ ቀኙ አንዱ በሌላው አቤቱታ ላይ ግልፅ ያሆነ ነጥብ ወይም ሌሎች ማናቸውም እውነቱን ሊያወጡ የሚችሉ ጥያቄዎችን በፍርድ ቤቱ በኩል መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ፍርድ ቤቱም ጠያቂ መኖሩን ግራ ቀኙን በመጠየቅ ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ የክስ መስማቱ ሂደት፣ የሚቀርቡ ጥያቄዎችና መልሶች የአቤቱታው አካል ተደርገው የሚወሰዱ በመሆኑ በአግባቡ መመዝገብ አለባቸው፡፡

በክስ መስማቱ ሂደት ተከሳሹ የቀረበበትን ክስ ያመነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ፍርድ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም ግራ ቀኙን የሚያከራክራቸው ነጥብ ካለ ፍርድ ቤቱ ወደ ጭብጥ መመስረት መሄድ ይኖርበታል፡፡

<u>ተከራካሪዎቹን ስለመመርመር</u>

1. ባለጉዳዮቹ ሲቀርቡ ፍርድ ቤቱ ስለክርክሩ መነሻ እና ከክርክሩ ጋር አግባብነት ያላቸውን ጉዳዮች ከባለጉዳዮቹ በመሰለው ዘዴ የቃል ጥያቄ በማቅረብ ይመረምራቸዋል (ቁጥር 241) ፡፡
2. ከሳሹ ቀርቦ ተከሳሹ ቢቀርም ይህ ምርመራ በከሳሹ ላይ ብቻ መካሄድ አለበት፡፡
3. በዚህ ደረጃ ባለጉዳዮችን በመሰለው የሚመረምረው ፍርድ ቤቱ ነው እንጂ ባለጉዳዮቹ ሙግት አይጀምሩም (ቁጥር 241(2)) ፡፡ የባለጉዳዮች የቃል ሙግት የሚጀምረው በአንቀፅ 258 ነው፡፡ ሆኖም ክሱ በሚከፈትበት ጊዜም ቢሆን ከተከራካሪዎቹ ማንኛውም ወገን እንዲብራራለት የሚፈልገውን ጉዳይ ፍርድ ቤቱ እንዲጠይቅለት ለማመልከት ይችላል (241(2) )፡፡
4. ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ ወይንም በምርመራው ወቅት በሚሰጠው ቃል የተከሰሰበትን ነገር ሙሉ በሙሉ ወይንም በከፊል ያመነ እንደሆነ በታመነው መጠን ለከሳሹ ይፈረዳል (ቁጥር 242)፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ስላመነ ብቻ ለከሳሹ የሚወሰን ሳይሆን ተከሳሹ ቢያምንም ከሳሽ ያቀረበው ክስ ህጋዊ መሆኑንና ከሳሹ ያቀረበው

ዳኝነት በሕግ የሚገባው መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማጣራት አለበት፡፡

5. ክርክሩ በሚቀጥልበት ሂደት ውስጥ ተከሳሹ ያመነው ጉዳይ ካለም ቁጥር 242 ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፡፡ በቁጥር 241 የተደነገገው ምርመራም በክርክሩ ሂደት ሁሉ ሊቀጥል ይችላል (ቁጥር 243) ፡፡
6. ፍርድ ቤቱ ቅጣቱን ከመወሰኑ በፊት ባለጉዳዮን መምከርና በቁጥር 480 መሠረት አስፈላጊ የሆነውን እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡ የወንጀል ቅጣት የሚወሰነው በመጨረሻ ምርጫ መሆን አለበት፡፡
7. ተከራካሪ ወገኖቹ ወይም አንዱ ችሎቱ የሚካሄድበትን ቋንቋ የማያውቁ ከሆነ ፍርድ ቤቱ አስተርጓሚ መመደብ አለበት፡፡ አስተርጓሚው የመተርጐም ስራውን ከመጀመሩ በፊት  የመሐላ ወይም የማገጋገጫ ቃሉን መስጠት አለበት፡፡ የመኃላ ቃሉም በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት "በዚህ ፍርድ ቤት የቀረበውን ክርክር በእውነትና የችሎታዬን ያህል ልተረጉም እምላለሁ" የሚል መሆን አለበት፡፡ አስተርጓሚው እምላለሁ ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ እምላለሁ በማለት ፋንታ አረጋግጣለሁ ማለት ይችላል፡፡ መፅሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ እንዲምል ማስገደድ ተገቢ አይደለም፡፡
8. ክሱ የሚሰማው በግልፅ ችሎት መሆን አለበት፡፡ ሆኖም  የተከራካሪዎቹን የግል ህይወት፣ የሕዝብን ሞራልና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ጉዳዩን በዝግ ችሎት ማየት ይቻላል፡፡

**ከፍትሃብሄር መርሃ ችሎት**

# የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ በሰጠው መልስ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ማቅረቡን ማጣራት ይኖርበታል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ቀርቦ ከሆነ ከሳሽ መልስ እንዲሰጥበት እድል ይሰጠዋል፡፡ በተቻለ መጠን ፍርድ ቤቱ ለቀረበው መቃወሚያ ወዲያውኑ ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ሊሰጥ ይገባል፡፡

## በመጀመሪያ ደረጃ ክርክር ላይ የሚቀርቡ መቃወሚያዎች

1. ማስረጃ ተቀብሎ ከመመረመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ በፊት ፍርድ ቤቱ አስቀድሞ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ላቀረበው መቃወሚያ ውሳኔ መስጠት አለበት (ቁጥር 244(1)) ፡፡
2. መቃወሚያዎቹ ከአንድ በላይ ከሆኑ ሁሉም አንድ ላይ መቅረብ አለባቸው፡፡ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያሰናክሉ ካልሆኑ በቀር መጀመሪያ ያልቀረቡ መቃወሚያዎች በኃላ መቅረብ አይችሉም፡፡ (ቁጥር 244(3))
3. መቃወሚያ መቅረብ ያለበት ከመከላከያ መልስ ጋር ነው እንጂ መጀመሪያ መቃወሚያ ብቻ ቀርቦ ሙሉ መልስ በኃላ የሚቀርብበትን አሠራር ፍርድ ቤቱ መፍቀድ የለበትም፡፡ ስለዚህ ሙሉ መልስ ተሟልቶ ሳይቀርብ መቃወሚያው ብቻ የቀረበለት ፍርድ ቤት በቁጥር 338 መሠረት የመከላከያ መልሱን ሲመረምር እንዲህ አይነቱን ያልተሟላ መልስ አለመቀበል ወይም ተሰተካክሎ እንዲቀርብ ማዘዝ አለበት፡፡
4. ክሱ ትክክለኛውን ፎርም አልተከተለም የሚል ክርክር እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መቅረብ አይችልም (ቁጥር 24(4))፡፡ (ክሱ ፎርሙን መከተሉን የሚያጣራው ሪጅስትራር ስለሆነ ነው፡፡)
5. ፍርድ ቤቱ የቀረበውን መቃወሚያ እንዲሁም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ በቁጥር 245 መሠረት ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. የቀረበው መቃወሚያ ክሱ የተነሳበት ጉዳይ በይርጋ የታገደ መሆኑን፣ ወይም አስቀድም በፍርድ የተወሰነ መሆኑን፣ ወይም በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈጸመ መሆኑን፣ ወይም ለዕርቅ የተቀጠረ መሆኑን የሚገልፅ ከሆነና ይህም በማስረጃ ከተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ክሱን ዘግቶ ባለጉዳዮቹን ያሰናብታል (ቁጥር 245(2))፡፡
7. ከላይ በቁጥር 6 ስር ከተገለፀው ውጪ ያለ መቃወሚያ ሲቀርብና በማስረጃ ሲረጋገጥ ግን ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ዘግቶ ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
8. ከላይ በቁ. 7 ሥር በተጠቀሰው ሁኔታ መዝገቡ ሲዘጋ ካሳሽ ክሱን አሻሽሎ በዚያው

ወይም በሌላ ፌርድ ቤት ክሱን እንደገና ለማቅረብ ይችላል። ከላይ በቁጥር 6 ሥር በተጠቀሰው ሁኔታ ክሱ ሲዘጋ ግን ከሳሹ በዚያው ጉዳይ ሌላ ክስ ለማቅረብ አይችልም (ቁጥር 245 (3))።

9. መዝገቡ የተዘጋው ፍርድ ቤቱ ሥልጣን በማጣቱ ከሆነ ከሳሹ ከከፈለው የዳኝነት ገንዘብ ላይ በደንቡ መሠረት ከሚከፈለው ሂሣብ የቀረው ይመለስለታል (ቁጥር 245 (4)) ።

**የፍትሃብሄር መርሃ ችሎት**

የሙከራ ልምምድ

ከአባሪ 1-3 ያሉ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የክስ መስማት ልምምድ አድርጉ። የክስ መስማት ልምምዱ፡-

- ✓ የተከራካሪዎችን ምርመራ
- ✓ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ካለ ውሳኔን ይጨምራል።

## ጭብጥ የመመስረት ዘዴ

በፍትሃብሄር ሙግት ሂደት ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትን ጭብጥ መመስረት ወሳኝ ሂደት ነው። ጭብጥ ክርከሩ በምን መልኩ መመራት እንዳለበት እንዲሁም የትኞቹ ማስረጃዎች መቅረብ እንዳለባቸው የመወሰን ሃይል አለው። ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ጥቅም የሌለው ጭብጥ ቢመሰረት በጉዳዩ አካሄድ ላይ ከፍተኛ ችግር ሊፈጥር ይችላል። በመሆኑም በዚህ ሂደት ላይ ዳኞች ትክክለኛው ጭብጥ ለመመስረት ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ጭብጥ ግራ ቀኙን የሚያለያያቸው ህግ ወይም ፍሬነገር ነው።

ጭብጥን ለመመስረት የግራ ቀኙን አቤቱታ፣ በመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ ክሱ በሚሰማት ጊዜ በፍርድ ቤቱ ምርመራ ከተገኘው ውጤት እንዲሁም ከቀረቡት ማስረጃዎች በመነሳት ግራ ቀኙ የሚለያዩበትን ፍሬነገር ወይም ህግ መሰረት በማድረግ ሊመሰረት ይገባዋል፡፡

መሆኑም ጭብጥ ለመመስረት የሚከተሉትን ቴክኒኮች መከተል ያስፈልጋል፡-

1. ፌሬነገሩን ግልፅ አድርግ፡፡ ግራ የመጋባት ሁኔታን ሊፈጥሩ የሚችሉ ፍሬነገሮችን አስወግድ፡፡

   ❖ ግራ ቀኙ የሚስማሙባቸውን መሰረታዊ ፍሬነገሮች ለይተህ አውጣ-- ማን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ እንዴት. ለምሳሌ፡-

      ✓ ግንቦት 1 ቀን 2002 ዓ/ም ውል ተፈርሟል፡፡

      ✓ ስራው ሰኔ 5 ቀን 2001 ዓ/ም ተጠናቅቋል፡፡

      ✓ አበበ የሂሳብ ምርመራውን ሐምሌ 2 ቀን አጠናቋል፡፡

      ✓ አደጋው የደረሰው ጥቅምት 2 ቀን 1999 ዓ/ም ነው፡፡

      ✓ በአንድ ቤት ውስጥ መኖር የማይቻል መሆኑን ሁለታችሁም ትስማማላችሁ

   ❖ ግራ ቀኙ ያልተስማሙበትን ነጥሎ ማውጣት፡፡ ግራ ቀኙ ያልተስማሙበት ፍሬነገር፡-

      ✓ ወደፊት በማስረጃ የሚረጋገጥ ሊሆን ይችላል

      ✓ የአመለካከት ልዩነት ሊሆን ይችላል (ለምሳሌ የቤት ዋጋ ግምት)

2. ለጉዳዩ እልባት ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ጭብጡን መስርት፡፡ በአግባቡ የተመሰረተ ጭብጥ የተከራካሪዎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎች ፍርድ ቤቱ በመሰረተው ጭብጥ የሚስማሙ መሆኑን ሊጠይቅ ይገባል፡፡ የሆነ ሆኖ የመጨረሻውን ጭብጥ የመወሰን ስልጣን የፍርድ ቤቱ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡

በተገቢው ሁኔታ የተቀረፀ ጭብጥ በርካታ አማራጮችን የሚያስቀምጥ መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ፡-

1. በግራ ቀኙ መካከል ውል አለን?
2. ውል አለ ቢባል የተከሳሽ ሃላፊነት በውሉ ምንድነው?
3. ውል የለም ቢባል በግራ ቀኙ ያለው ግንኙነት ምንጩ ምንድንነው?
4. ግንኙነት የሚመነጨው ከውል ውጭ ሃላፊነት ከሆነ የተከሳሹ ሃላፊነት ምንድነው?
5. ወዘተ ተብሎ በአማራጭ ሊቀመጥ ይገባል፡፡

<u>የክርክሩን ጭብጥ መያዝ</u>

1. በቁጥር 241 መሠረት ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎቹን በቃል ከመረመረ በኃላ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተነስቶ እንደሆነም በመቃወሚያው ላይ አስፈላጊው ውሳኔ ከተሰጠ በኃላ ባለ ጉዳዮቹ የሚከራከሩበት ወይም የተለያዩበት ጭብጥ ይመሰረታል፡፡ (በቀረበው መቃወሚያ መሰረት ክሱ ወይም መዝገቡ ካልተዘጋ በቀር፡፡)
2. ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ወገን ያመነውን ወይም አለ ብሎ የሚከራከረውንና ከክርክሩ ጋር አግባብነት ያለውን የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ጉዳይ ሌላኛው ወገን ሲክድ ነው (ቁጥር 247(1) ፡፡

3. የሚመሠረተው ጭብጥ እንደነገሩ ሁኔታ የሕግ ብቻ፣ የፍሬ ነገር በቻ ወይም የሁለቱም ሊሆን ይችላል፡፡

4. በአንድ ክስ ላይ ከአንድ በላይ የሆነ የፍሬ ነገር ወይም የህግ ወይም የሁለቱንም ጭብጦችን መያዝ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል (ቁጥር 247(3)(4)) ፡

፡

5. የሕግና የፍሬ ነገር ጭብጦች አንድ ላይ ከተያዙ መጀመሪያ የሕግ ጉዳይ ላይ በተያዘው ጭብጥ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍርድ ቤቱ በሕግ ረገድ የተያዙትን ጭብጦች እስኪወስን ድረስ በፍሬ ነገር የተያዘውን ጭብጥ በቀጠሮ ሊያቆየው ይችላል (ቁጥር 247 (4)) ፡፡

6. የተያዘው ጭብጥ የሕግ ጉዳይ ብቻ ከሆነ (የፍሬ ነገር ክርክር ወይም ጭብጥ ከሌለ) ወዲያው አስፈላጊው ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

7. ጭብጥ የሚመሰረተው የግራ ቀኙ ማስረጃ ከመሰማቱ በፊት መሆን አለበት፡፡ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ከታየው ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ከመመስረቱ በፊት ምስክሮችንና የፅሁፍ ማስረጃዎችን አስቀርቦ መመርመር ይችላል (ቁጥር 249)፡፡ በተጨማሪም ፍርድ ቤቱ ፍርድ ከመስጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ መጀመሪያ ተይዘው የነበሩትን ጭብጦች ለማሻሻል፣ ለመቀየር ወይም ተሳስቶ ተቀብሎ የነበረውን ጭብጥ ለመሰረዝ ይችላል (ቁ. 251) ፡፡

8. በመሰረቱ ጭብጥ የሚይዘው ፍርድ ቤቱ ነው፡፡ ሆኖም ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ሲይዝ ጭብጡ ምን እንደሆነ ለባለጉዳዮቹ መግለፅና ሐሳባቸውን መስማት አለበት፡፡

9. በሌላ በኩልም ተከራካሪ ወገኖች እራሳቸው ጭብጡ ላይ በመስማማት ፍርድ ቤቱ ጭብጡን እንዲይዝላቸው ለማመልከት ይችላሉ (ቁጥር 251)፡፡ ፍርድ ቤቱም በቁጥር 253 መሠረት ጥያቄውን መርምሮ ጭብጡን በመቀበል በዚያው መሠረት ውሳኔ ለመስጠት ይችላል፡፡

10.ክሱ በሚሰማበት ቀን ተከሳሹ የመከላከያ መልሱን ሳያቀርብ ከቀረ ፍርድ ቤቱ የነገሩን ጭብጥ ለመያዝ አይገደድም (ቁጥር 246(2)) ፡፡ ሆኖም ግን ከሳሹ ካቀረበው ክስ እና የጽሑፍ ማስረጃ እንዲሁም በቁጥር 241 መሠረት በተደረገው የቃል ምርመራ ከተገኘው መረጃ በመነሳት አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍረድ ቤት መፍትሔ የሚሻውን ጭብጥ ለመያዝ ይችላል፡፡

11.የክርክሩ ጭበጥ የሚያዘው (ቁጥር 248)፤

ሀ. በክሱና በመከላከያው መልስ ውስጥ የተዘረዘሩትን ነገሮች፣

ለ. ተከራካሪዎቹ ያቀረቡትን የፅሑፍ ማስረጃ፣

ሐ. በቁጥር 241 መሠረት በተደረገው ምርመራ የተገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ (እንደሁኔታው ሦስቱንም ወይም ከሦስቱ ሁለቱን ወይም አንዱን መሠረት በማድረግ) ነው፡፡

12. ከላይ በቁጥር "11" ከተዘረዘሩት ውጪ ሌላ ማስረጃ መቅረቡ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ፍርድ ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ለመመሥረት አስፈላጊ የሆኑ ምስክሮችንና የፅሑፍ ማስረጃዎችን አስቀርቦ መመርመር ይችላል (ቁጥር 249) ፡፡

13.ክስ በቀረበበት ሀብት ግምት ላይ ክርክር ከተነሳ ፍርድ ቤቱ ጭብጥ ከመመሥረቱ በፊት የሀብቱን ግምት የሚያስታውቁ ምትክ ዳኞችን መሾም አለበት (ቁጥር 250) ፡፡

14.ተከራካሪዎቹን የሚያከራክራቸው ነጥብ አለመኖሩን ፍርድ ቤቱ ከተረዳው ማስረጃ መስማት አስፈላጊ ሳይሆን ወዲያው ተገቢውን ፍርድ መስጠት አለበት (ቁጥር 254)፡፡

15. ተከራካሪዎቹን የሚለያያቸው ነጥብ መኖሩ ከታወቀ ግን ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ከመሠረተ በኃላ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በመጀመሪያ ክርክር ላይ ያቀረቡት ማስረጃና (በተጨማሪም በቁጥር 249 መሠረት በፍረድ ቤት ትዕዛዝ የቀረበው ማስረጃ) ክርክር በቻ ፍትሐዊ ፍርድ ለመስጠት በቂ ከሆነ ወዲያው ፍርድ ይሰጣል (ቁጥር 255) ፡፡

**ከፍትሃብሄር መርሃ ችሎት**

የሙከራ ጥያቄ

<u>**ከሳሽ ያቀረበው ክስ**</u>

አቶ አድማሱ ጀመረና ወ/ሮ ዘውዲቱ ንጉሴ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/13 የቤት ቁጥሩ 157 በወ/ሮ ንጉሴ ዘውዲቱ ስም የተመዘገበ የጋራ ቤት ነበራቸው፡፡ አቶ አድማሱና ወ/ሮ ዘውዲቱ ንጉሴ ከአገር ተሰድደው ሲኖሩ አንደኛው ተከሳሽ አባት እናቴ ጠፍተዋል በማለት የወራሽነት ማስረጃ በማውጣት ከአዋጅ ውጭ የተወረሰው ቤት እንዲመለስላቸው በማስወሰን ቤቱን ይረከባሉ፡፡ ሆኖም የተሰጠው የወራሽነት ማስጃ ያለአግባብ ነው በማለት አቶ አድማሱ ባቀረቡት መቃወሚያ መሰረት ፍርድ ቤቱ የወራሽነት ማስረጃውን ሽሮታል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ወ/ሮ ዘውዲቱ ንጉሴ በመቀጠልም አቶ አድማሱ ጀመረ ከዚህ አለም በሞት በለመየታቸው ከሳሽና 1ኛ ተከሳሽ የወ/ሮ ዘውዲቱ ንጉሴ ያለኑዛዜ ወራሾች እንዲሁም የአቶ አድማሱ ጀመረ ኑዛዜ ወራሾች ናቸው፡፡ በመሆኑም ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12/13 የቤት ቁጥሩ 157 የሆነው ቤት የጋራ የውርስ ሀብት ነው፡፡ ይህን የውርስ ሀብት 1ኛ ተከሳሽ ከሁለተኛ ተከሳሽ ጋር ሚያዚያ 3 ቀን 1999 ዓ/ም በተደረገ የሽያጭ ውል አስተላልፏል፡ ፡ የጋራ የውርስ ሃብት ሳይከፋፈል ባለበት ሁኔታ የወራሾች ስምምነት ሙሉ በሙሉ ሳይገኝ ሊተላለፍ እንደማይችል በፍትሃብሄር ህግ ቁጥር 1060/1266 ላይ በግልፅ ሰፍሯል፡፡ በመሆኑም የሽያጭ ውሉ ሊፈርስ የሚገባው ስለሆነ ውሉ እንዲፈርስና ቤቱን ለከሳሽ እንዲያስረክቡ እንዲወሰንልኝ በአማራጭ ውሉ የማይፈርስበት ምክንያት ካለ

ተከሳሽ በሽያጭ የወሰደው ብር 2,500,000 (ሁለት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) በውርስ ሀብትነት እንደተለየ የሚቆጠር ስለሆነ በሞዴል 85 መሰረት እንዲያዝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ከሳስ ከክስ ማመልከቻቸው ጋር የወራሽነት ሰርቲፊኬት፣ የቤት ሽያጭ ውልና ሌሎች ሰነዶችን አያይዘው አቅርበዋል፡፡

<u>1ኛ ተከሳሽ የሰጠው መልስ</u>

1ኛ ተከሳሽ ለቀረበባቸው ክስ ሰኔ 13 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ የሰጡት መልስ ይዘት ባጭሩ፡-

- ሚች አባቴ አቶ አድማሱ ጀመረና ወ/ሮ ዘውዲቱ ንጉሴ የጋራ የሆነ ንብረት አልነበራቸውም፣ ክርክር የቀረበበት ቤትም እናቴ ወ/ሮ ዘውዲቱ ንጉሴ ከጋብቻ በፊት ያፈሩት የግል ቤታቸው ነው፡፡
- ሚች አባቴ አቶ አድማሱ ጀመረ ቤቱ የራሳቸው ስላልሆነ ቤቱን አውርሻለሁ ብለው ሊናዘዙ አይችሉም፡፡
- ከሳሽ ካቀረቡት ክስ ላይ አለኝ የሚሉት የወራሽነት መብት የወ/ሮ ዘውዲቱን የግል ንብረት ሊወርሱ እንደማይችሉ ተቃውሞ ቀርቦበት በፍርድ ቤት የታገደ በመሆኑ በንብረቱ ላይ ያቀረቡት ጥያቄ በሌላቸውና ባልተረጋገጠ መብት ላይ ጥያቄ በመሆኑ ጥያቄያቸው ውድቅ ነው፡፡
- ከሳሽ ክስ ያቀረቡበት ቤት የጋራ ነው የሚሉ ስለሆነ ሙሉ በሙሉ ለሳቸው እንዲሰጥ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም
- የወላጅ እናቴ የሆነውን ቤት ለማስለቀቅ ከ1985 ዓ/ም ጀምሮ ለ9 ዓመታት በራሴ ወጭና ከሰዎች ባገኘሁት ብድርና ድጋፍ በ1994 ዓ/ም ከመንግስት ተፈቅዶልኛል፡፡ በዚህ ጊዜ አንድም ድጋፍ ሳያደርጉልኝ ለ6 ዓመታት በይዞታ ስር አቆይቼ በ1999 ዓ/ም በህጋዊ መንገድ ለ2ኛ ተከሳሽ የሸጥኩ ስለሆነ ውሉ ይፈረስ ተብሎ የቀረበው ክስ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡
- ለከሳሽ በአማራጭ የሽያጩ ገንዘብ ብር 2.5 ሚሊዮን የሚሰጥበት ምክንያት የለም፣ በሞዴል 85 የሚያዝበት ምክንያትም የለም፡፡
- ከሳሽ የንብረት አጣሪነት ስልጣን በኑዛዜ ተሰጥቶኛል ሲሉ ያቀረቡት ኑዛዜው

ህገ-ወጥ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡

- ከሳሽ የውርስ ድርሻዩ ይሰጠኝ የሚሉ ከሆነ ንብረቱን ለመረከብ ወደ ብር 60,000 (ስድሳ ሺህ) ያወጣሁ ስለሆነ ይህ ሊታሰብልኝ የሚገባ ነው የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ከመልሳቸው ጋር አያይዘው ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ የለም፡፡

**<u>2ኛ ተከሳሽ የሰጠው መልስ</u>**

2ኛ ተከሳሽ ሰኔ 13 ቀን 2001 ዓ/ም በተፃፈ የሰጠው መልስ ይዘት ባጭሩ፡- ተከሳሹ 1ኛው ተከሳሽ በስማቸው የተመዘገበውን ቤት ለመሸጥ እንደሚፈልጉ በመግለፃቸው ቤቱ በስማቸው የተመዘገበ መሆኑ፣ እዳና እገዳ የሌለበት መሆኑ ተጣርቶ በሰነዶችና ማስረጃ ምዝገባ ፅ/ቤት ውሉ ተፈርሞ የቤቱ ባለቤትነት በስማችን የተመዘገበ በመሆኑ የቀረበብን ክስ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

2ኛ ተከሳሽ ከመልሱ ጋር የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዞ አቅርቧል፡፡

---

የግራ ቀኙን የፁሁፍ ክርክር ካነበብክ በኃላ ጭብጡን በዚህ ባዶ ቦታ ላይ አስፍርና ከዚህ በታች ጭብጥ ጋር የራስህን አነፃፅር፡፡

ጭብጥ

ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የሚከተሉትን ሁለት ጭብጦች ይዟል፡-

1. ከሳሽ ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ መብት አላቸውን?
2. ከሳሽ በቤቱ ላይ መብት አላቸው የሚባል ቢሆን 1ኛና 2ኛ ተከሳሾች ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ሊፈርስ ይገባዋልን?
3. ውሉ ሊፈርስ አይገባውም የሚባል ቢሆን የሽያጩ ገንዘብ ብር 2,500,000 (ሁለት ሚሊዩን አምስት መቶ ሺህ) ለከሳሽ ሊሰጣቸው ይገባልን?

የሙከራ ልምምድ

1. ከአባሪ 1-7 ላይ የተዘረዘሩትን ጉዳዮች በመመልከት ጭብጡን አውጡ፡፡
2. አባሪ 1ና 2 ላይ ፍርድ ቤት የሰጣቸው ውሳኔዎች የተያያዙ ሲሆን በውሳኔዎቹ ላይ ለአባሪዎቹ ጭብጥ ተመስርቷል፡፡ በጭብጦቹ ይስማማሉን?

# ክፍል 3

## ሙግቱን መስማት

### የክፍሉ ግቦች

ይህ ክፍል ከተጠናቀቀ በኃላ ሰልጣኞች

- ✓ ሰብሰብ ያለ የሙግት አሰማም ዘዴን ይለያሉ፡፡
- ✓ የሙግት መስማት ሂደትን ይገልፃሉ፡፡
- ✓ የመክፈቻና የመዝጊያ ንግግር አስፈላጊነት ይረዳሉ፡፡
- ✓ ሙግት ይመራሉ፡፡
- ✓ በራሳቸው የሚሟመገቱ ተከራካሪዎችን ልዩ ፍላጎት ይለያሉ፡፧
- ✓ የውስብስብ ጉዳዮችን አመራር ዘዴ ይለያሉ፡፡

## ሰብሰብ ያለ የፍትሃብሄር ሙግት አሰማም ዘዴ

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጉ ሰብሰብ ያለ (concentrated) የጉዳይ መስማት ሂደትን ይደነግጋል፡፡ በተለይ ምስክር መሰማት ከጀመረ መቋረጥ እንደሌለበትና ምስክር መሰማቱ በአንድ ቀን የማያልቅ ከሆነ በአዳሪ እየቀጠሩ መጨረስ እንደሚገባ ከቁ. 197(3) መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም ግራ ቀኙ የሰነድ ማስረጃ የሚያቀርቡ ቢሆን ከአቤቱታቸው ጋር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህግ ቁ. 223 በሚያዘው መሰረት መጀመሪያውኑ ካልቀረበ ወይም ጉዳዩ ለክስ መስማት ሲቀጠር ካልቀረበ በሃላ ላይ ሊቀርብ እንደማይችል ከቁ. 137 ድንጋጌዎች መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ወደ ክርክር መስማት ደረጃ ሲገባ ማስረጃዎች ሁሉ ተጠቃለው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህም

በተከራካሪ ወገኞች መካከል እንግዳ ማስረጃና ክርክር ሳይፈጠር ጉዳይን በአጭር ጊዜ ውስጥ እልባት ለመስጠት ያስችላል፡፡ በአንድ ክርክር ላይ የሚቀርቡ ማስረጃዎች በየጊዜው እየተለወጡና እየጨመሩ በመጡ ቁጥር ዋናውና ክርክር የቀረበበት ጭብጥ እየተዘነጋ ጉዳዩ እየተንዛዛ፣ ውስብስብና አቅጣጫ የጠፋው እየሆነ እንደሚመጣ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ጉዳይ በጊዜ እልባት እንዳያገኝ የሚያደረግ ነው፡፡

ሌላው ከማስረጃ መስማት ደረጃ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ማስረጃውን መጀመር ያለበት ማን ነው በሚለው ላይ ነው፡፡ በወ/መ/ሥ/ሥ/ ህግ መሰረት ምንጊዜም ማስረዳት መጀመር ያለበት ከሳሹ ዓቃቤ ህግ ሲሆን ይህ አካሄድ በፍ/ሥ/ሥ/ ህጉ ሁልጊዜ የሚሰራ አይሆንም፡፡ ለምሳሌ ተከሳሹ ከሳሹ ያቀረበውን ፍሬ ነገር አምኖ ሆኖም ከሳሹ ያላነሳቸውን አዲስ ፍሬ ነገሮችን አንስቶ የሚከራከር ቢሆን ማስረጃ ማሰማት ያለበት ተከሳሹ ይሆናል (ቁ. 259-261)፡፡ ፍርድ ቤቱ ማስረጃ ከሰማ በሃላ ፍርድ ወዲያውኑ ወይም በአጭር ጊዜ ውስጥ መስጠት አለበት (ቁ. 180)፡፡

በሌላ በኩል ከሳሽ በማስረጃ አቀራረብ ረገድ ሁል ጊዜ ጀማሪ እንዳልሆነ የስነ ስርአት ህጉ ግልፅ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ አንድ ከሳሽ በተከሳሽ መኪና ተገጭቼ ጉዳት ደርሶብኛልና ካሳ ይከፈለኝ ብሎ ክስ አቅርቦ ተከሳሹ ከሳሹ በመኪው የተገጨ መሆኑን አምኖ አደጋው የደረስው በከሳሹ ጥፋት መሆኑን ገልፆ ከተከራከረ በዚህ ጉዳይ ማስረጃ አቀራረብ ላይ መጀመር ያለበት ተከሳሹ ነው፡፡ ከሳሹ በተከሳሹ መኪና መገጨቱን ማስረዳት ነበረበት ሆኖም ተከሳሹ ያመነለት በመሆኑ ይህንን ነጥብ ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡ ሆኖም ተከሳሹ የከሳሹን ጥፋት ካስረዳ በሃላ ከሳሹ ጥፋት የሌለበት መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም የማስረዳት ሸክም በዚህ መልኩ የሚቀያየር ይሆናል፡፡ ጉዳዮን የማሳመን ሸክም ግን ምን ግዜም ቢሆን የከሳሹ ይሆናል፡፡

ሌላው ከሙግት መስማት ሂደት ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ምንም እንኳን የስነ ስርአት ህጋችን ሰብሰብ ያለ ሂደትን ያስቀመጠ ቢሆንም በተግባር የሙግቱ ሂደት የተበታተነ ነው፡፡ ማስረጃዎች የሚቀርቡት እየተንጠባጠቡ በተለያዩ ቀጠሮዎች ነው፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጉ ጥብቅ

የሆነ የቀጠሮ ፖሊሲን ይከተላል:: ይህንንም ከቁጥሮች 192-199 ካሉት መገንዘንብ ይቻላል:: በተለይ እነዚህን ድንጋጌዎች ዳኖችና ጠበቆች ይመለከቷቸዋል ለማለት ያስቸግራል:: ተከራካሪ ወገኖች ወይም ጠበቆች በመቅረታቸው ቀጠሮዎች ሲሰጡ ይታያሉ:: ሆኖም እንዲዚህ አይነት አሰራር በህጉ በግልፅ ተከልክሎ ይገኛል (ቁ. 197(4))::

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ህጉ ቁ. 194 (2) አንድ ተግባር እንዲፈፀም ጊዜ ተሰጥቶ በዛ ጊዜ ውስጥ ካልተፈፀመ ከባድ ምክንያት ካላጋጠመ በቀር ሌላ ጊዜ ሊሰጥ እንደማይችል ይደነግጋል:: ለምሳሌ ተከሳሹ መልሱን እንዲያቀርብ ጊዜ ተወስኖለት በዛ ጊዜ ውስጥ መልሱን ካላቀረበ ከባድ ምክንያት ካላቀረበ በቀር መልሱን እንዲያቀርብ ሊፈቀድለት አይገባም:: ሆኖም ዳኞች ብዙ ግዜ በቀጠሮና በጊዜ ውሳኔ ላይ ላላ ብለው ይታያሉ:: በተለይ የፍትሃብሄር ጉዳይ አካሄድ የሚወሰነው በግራ ቀኙ ክርክር ስለሆነ ግራ ቀኙ እስከተስማሙ ድረስ ፍርድ ቤቱ ጣልቃ መግባት የለበትም በተለይም ጥፋተኛው ወገን ለሌላኛው ተከራካሪ ወገን ኪሳራ እስከቆረጠ ድረስ ችግር የለም የሚል አመለካከት በዳኞች ዘንድ ይንፀባረቃል:: ይህ አሰራር ከዘመናዊ የጉዳዮች አመራር ዘዴ ጋር የሚጋጭ ነው:: በተለያዩ አገሮች ለጉዳዮች መንዛዛት አንዱ ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው ተከራካሪ ወገኖች ጉዳዮችን መምራታቸው ነው:: አሁን ያለው አስተሳሰብ ተከራካሪ ወገኖችን ተቆጣጥሮና አትግቶ አቅጣጫ ማስያዝ ያለበት ዳኛው ነው:: የጉዳይ መሪ መሆን ያለበት ዳኛው ነው:: በተለይ ተከራካሪ ወገኖች በአንድ ጉዳይ ላይ በተቃራኒው የሚሰሩ በመሆኑ (ማለትም አንዱ ለመርታት ሌላኛው ላለመረታት) ያለ ዳኛው መሪነት ጉዳዮች በተፈለገው ፍጥነትና ወደተፈለገው ግብ ይሄዳሉ ለማለት ያስቸግራል::

## የመክፈቻ ንግግር

የፍትሃብሄር ስነስርአት ህጉ ክሱን የመክፈት መብት ያለው ወገን የመክፈቻ ንግግር በማድረግ ማስረጃዎችን ማሰማት እንዳለበት ይደነግጋል። በተለይ ህጉ ግራ ቀኙ በህግና በፍሬነገር ረገድ

የሚመተማኑባቸውን ነጥቦች በማንሳት ክርክር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም በተለምዶ ይህ እምብዛም ሲፈፀም አይታይም፡፡

በሌሎች አገሮች፡-

- የመክፍቻ ንግግር በክርክሩ ሂደት ወሳኝ ምዕራፍ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡
- የመክፈቻ ንግግር የማስረጃ አቀራረብን ሂደት (road map) በግልፅ ያሳያል፡፡
- ምስክሮች ቀርበው ሲሰሙና ሌሎች ማስረጃዎች ሲመረመሩ ቀስ በቀስና እየተቆራረጠ በመሆኑ በአግባቡ የተደረገ የመክፈቻ ንግግር የማስረጃዎችን ትልቅ ስእል (bigger picture) ዳኛው እንዲመለከት ያደርገዋል፡፡
- በተደረጉ ጥናቶች ዳኞች ለማስረጃዎች ትርጉም የሚሰጡት የመክፈቻውን ንግግር መሰረት በማድረግ ነው፡፡
- የመክፈቻ ንግግር የተቃራኒውን ወገን ክርክር ሊያሽመደምድ ይቻላል፡፡

የመክፈቻ መያዝ ያለበት

1. ጉዳዩን ለፍርድ ቤቱና ለዳኛው ማስተዋወቅ
    - ✓ መክፈቻ ንግግር እንደ አንድ ፊልም ማስታወቂያ ወይም ፕሮቫ (preview) ሊቆጠር ይችላል
    - ✓ የጉዳዩን ታሪክ በአጭሩ (birds eye view) ማሳየት
    - ✓ በጉዳዩ ትኩረት ሊሰጥበት የሚገባውን (theme of the case) ማሳየት
2. ጠበቆች ከፍርድ ቤቱ ጋር መግባቢያ መፍጠር

- ✓ ፍርድ ቤቱ ከጉዳዩ ጋር እንዲለማመድ፣ ራሱን እንዲያስተዋውቅ ማድረግ
- ✓ ታማኝነት፣ አሳቢነት፣ አዋቂነት፣ ቅን ልቦናን ማሳየት፣ ወዘተ (ተንኮለኛነት፣ ለፍላፊነት፣ ተሳዳቢነት፣ ወዘተ በዳኛው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖን ሊያሳድር ይችላል
- ✓ መክፈቻ ንግግር መግቢያ፣ ዋና ክፍልና መደመምደሚያ ሊኖረው ይገባል፡፡

በመክፈቻ ንግግር የዳኛው ሚና፡-

- ✓ ከመክፈቻ ንግግር በቂ ጊዜ መመደብ፣ ይህንን ለተከራካሪዎች ቀደም ብሎ ማሳወቅ
- ✓ በተቻለ መጠን በንግግሩ ጣልቃ አለመግባበት
- ✓ የመክፈቻ ንግግሩ መመዘገቡን ማረጋገጥ

## የምስክሮች መሰማት

በሙግት መስማት ሂደት የምስክሮች ምርመራ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ በመሆኑም ዳኞችም ሆኑ ተከራከራካሪ ወገኖች አፈፃፀሙን በተመለከተ ልዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል፡፡ በተቻለ መጠን ዳኞች በሂደቱ ጣልቃ ላለመግባት መሞከር አለባቸው፡፡ በተለምዶ የምስክሮች ምርመራ ሙሉ በሙሉ በዳኞች የሚፈፀም ሲሆን ይህ ከስነስርአቱ ህጉ የወጣ በመሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተለይ ተከራካሪ ወገኖች በጠበቃ በተወከሉ ጊዜ የምስክሮችን ምርመራ ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ ለባለሙያዎች ማስተላፍና ዳኛው በጣም ውስን በሆኑ ሁኔታዎች የማብራሪያ ጥያቄ ሊጠይቅ ይገባል፡፡

የዳኛው ሃላፊነት፡-

- ✓ ለምስክሮች ስለ ፍርድ ሂደት ማብራሪያ መስጠት
- ✓ ምስክሮች ዘና እንዲሉ ማድረግ
- ✓ ምስክሩን የሚያስቆጡ ወይም የሚያበሳጩና የሚደጋገሙ ጥያቄዎችን ማስቆም

- ✓ በዋና ጥያቄ ጊዜ መሪ ጥያቄዎች
- ✓ ባለሙያ ላልሆኑ ምስክሮች የሚቀርቡ የአስተያየት ጥያቄዎች
- ✓ በዋናው ጥያቄ ጊዜ ባልተነሱ ጉዳዮች የሚቀርቡ መስቀለኛ ጥያቄዎች
- ✓ ማጣሪያ ጥያቄዎችን የመጠየቅ

## የክርክር ማቆሚያ ንግግር

የክርክር ማቆሚያ ንግግር የግራ ቀኙ ማስረጃዎች ከተሰሙ በሃላ ተከራካሪዎች ስለ ጉዳዩ በህግና በፍሬነገር ረገድ ያላቸውን አቋም በተመለከተ ማጠቃለያ ክርክር የሚያቀርቡበት ነው፡፡ ሰዎች በመጨረሻ የሰሙትን የማስታወስ ዝንባሌ ስላላቸው ይህ ሂደት ወሳኝ ነው፡፡ በክርክር ማቆሚያ ንግግር ላይ በመክፈቻ ንግግር ላይ የተቀመጡት መርሆችና ተግባራት ተግባራዊ መደረግ አለባቸው፡፡

<u>ክርክሩን ስለመስማት እና ምስክሮችን ስለመመርመር</u>

ይህ ደረጃ ዋናው የክስ መሰማት ሂደት የሚካሄድበት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ የሚፈፀሙ ዋና ዋና ተግባራት፡-

1. ተከራካሪዎቹ ሙግታቸውን ያሰማሉ፡፡ ምስክሮቻቸውንም አቅርበው ያሰማሉ፡፡
2. ተከራካሪዎቹ በዋናነት ፍ/ቤቱ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ምስክሮችን ይመረምራሉ፡፡

   ፍ/ቤቱም የምስክሮችን ቃል ይመዘግባል፡፡
3. በቀረበው ክስና ማስረጃ ላይ ተመስርቶ ፍ/ቤት ፍርድ ይሰጣል፡፡

<u>ስለምስክሮች</u>

1. ተከራካሪዎቹ ያቀረቡት የፅሑፍ ወይም የቃል ክርክርና ከአቤቱታዎቻቸው ጋር ወይም በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያቀረቡት የፅሑፍ ማስረጃ እንዲሁም ፍ/ቤቱ ጭብጡን ከመመስረቱ በፊት አስቀርቦ የመረመራቸው የሰውና የፅሑፍ ማስርጃዎች በክርክሩ ላይ

ውሳኔ ለመስጠት በቂ ካልሆኑ ፍ/ቤቱ በቁ. 223 መሠረት ተከራካሪዎቹ የዘረዘሯቸው ምስክሮች ቀረበው እንዲሰሙ ያዛል፡፡

2. ሁለቱም ወገኖች የምስክሮች ዝርዝር አቅርበው ከሆነ የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ቀን እንዲቀርቡ መታዘዝ አለበት፡፡
3. መቅረብ ያለባቸው ተከራካሪዎቹ በአቤቱታቸው ላይ የገለጿቸው ምስክሮች ሁሉ ሳይሆን በፅሑፍ ማስርጃ ያልተረጋገጡና በቁ. 241 መሠረት በተደረገው ምርመራ ተከራካሪዎቹ ያልተማመኑባቸውን የፍሬ ነገር ጭብጥ ለማስረዳት የሚችሉ ምስክሮች ብቻ ናቸው፡፡

4. አንደኛው ወገን የሌላውን ወገን ምስክር መስቀለኛ ጥያቄ በማቅረብ የመመርመር መብት ስላለው በመሠረቱ ምስክሮች በተቻለ መጠን በአካል ፍ/ቤት ቀርበው ቃላቸውን መስጠት አለባቸው (ቁ. 261(3)) ፡፡

5. ከላይ በቁ.4 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ በውስን ሁኔታዎች ፍ/ቤቱ ተገቢ መስሎ ሲታየው የፍርድ ቤት እንደራሴ ሆኖ በመወከል ማንኛውንም ማስረጃ የሚሰበስብ ወይም ምስክር የሚመረምር ምትክ ዳኛ መሰየም ይችላል (ቁ. 122-135)፡፡ እንዲሁም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) አስፈላጊውን ምርመራ አድርጎ የምርመራውን ውጤት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲያቀርብ ለማዘዝ ይችላል (ቁ. 136)፡፡

6. በተጨማሪም ውስን በሆኑ ሁኔታዎች ምስክሩ ፍ/ቤት ሳይቀርብ የመሐላ ቃል እንዲሰጥና ቃሉ በችሎት በንባብ እንዲሰማ ማድረግ ይችላል (ቁ. 203-206)፡፡

<u>**ለምስክሮች መጥሪያ መላክ**</u>

1. ከላይ በ(ለ) (5) እና (6) ሥር ከተመለከተው ውጪ ምስክር በአካል ፍ/ቤት ቀርቦ መመስከር አለበት፡፡
2. የመቅረባቸው አስፈላጊነት የታመነባቸው የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ላይ እንዲቀርቡ መጥሪያ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡ የመጥሪያው አላላክ ከቁ.111 እስከ 121 በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል፡፡

3. አመልካቹ ራሱ (መጥሪያ ሳይጠይቅ) ምስክሮቹን ለማቅረብ ይችላል (ቁ. 111)፡፡
4. መጥሪያ የሚጠይቀው ወገን መጥሪያውን ከመቀበሉ በፊት ፍ/ቤቱ በወሰነው ልክ ለምስክሮች ማጓጓዣና ሌላ የቀን ወጪ ወይም አበል የሚሆን ገንዘብ እንዲያስቀምጥ ይገደዳል፡፡ ይህን ግዴታ ካልፈፀመ የመጥሪያ ትዕዛዝ ሊሰጠው አይገባም (ቁ. 212 እና 213)፡፡
5. የምስክርነት ቃል እንዲሰጥ ወይም የፅሑፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ለሚጠራ ሰው በሚፃፈው የመጥሪያ ትዕዛዝ ላይ የተጠራበትን ምክንያት፣ የሚቀርብበትን ቀንና ሰዓት፣ ሥፍራው፣ የተጠራው ለምስክርነት ወይም የፅሑፍ ማስርጃ ለማቅረብ ወይም ስለ ሁለቱም ጉዳይ መሆኑ ተለይቶ መገለፅ አለበት (114)፡፡
6. የምስክርነት ቃል ለመስጠት ሳይሆን የፅሑፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ብቻ የታዘዘ ሰው ማስረጃው ለፍ/ቤቱ እንዲደርስ ካደረገ ራሱ ለመቅረብ አይገደድም (ቁ. 115)፡፡
7. ስለተከሳሽ መጥሪያ የተደነገጉት ድንጋጌዎች (ከቁ. 103-105 ከተደነገገው በቀር) ለምስክር በሚሰጥ መጥሪያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ (ቁ. 116)፡፡
8. መጥሪያው ሲላክ ተጠሪው በተወሰነው ቀነ ቀጠሮ ለመድረስ እንዲችል ለመጓጓዣና አስፈላጊውን መሰናዳት ለማድረግ በቂ ሆኖ በሚገመት ጊዜ ውስጥ ሊደርሰው እንዲችል መደረግ አለበት፡፡
9. መጥሪያው የተላከለት ሰው መጥሪያው ስላልደረሰው ሳይቀርብ የቀረ ወይም የፅሑፍ ማስረጃውን ሳያቀርብ ከቀረና ምስክሩ ወይም የፅሑፍ ማስረጃው መቅረቡ ጠቃሚ ከሆነ ባለ ጉዳዩ ተገቢውን ኪሣራ ከፍሎ ሌላ መጥሪያ እንዲደርሰው ይታዘዝለታል (118(2)(ሀ))፡፡
10. የተጠራው ሰው መጥሪያው ደርሶት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት ከሆነ ወይም እንዳይደርሰው ሆነ ብሎ ከተሰወረ ተጠሪው ተገዶ ወይም ታስሮ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ያዛል (ቁ. 118 (2) (ለ))፡፡ በተጨማሪም በወ/መ/ሕ/ቁ 442 መሠረት በወንጀል ሊቀጣው ይችላል (ቁ. 118 (3) እና 481)፡፡
11. ክርክሩን ለመስማት በተቀጠረው ቀን የሁለቱም ወገን ምስክሮች በአንድ ላይ ተሟልተው መቅረብ አለባቸው፡፡

**<u>የምስክሮች ተሟልተው አለመቅረብ</u>**

1. ከሁለቱም ወገን ምንም ምስክር ካልቀረበ ወይም ምስክሮች በከፊል ብቻ ከቀረቡ (መጥሪያውን እንዲያደርስ የታዘዘው ቁ. 95 (1) በሚያዘው መሠረት መጥሪያ ሰጪ ሳይሆን ባለጉዳዮቹ ራሳቸው እንዲያደርሱ በታዘዙ ጊዜና ክርክሩን የመጀመርና ማስረጃ በቅድሚያ የማሰማት መብት የከሳሹ በሆነበት ሁኔታ)፡-

1.1. የሁለቱም ወገን ምስክሮች ካልቀረቡ፤

ሀ. በሁለቱም ባለጉዳዮች ጥፋት ከሆነ መዝገቡ ላይ ባለው ማስረጃ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት ወይም ክሱን መዝጋት እንጂ ምስክሮቹ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መሰጠት የለበትም (ቁ. 196 እና 199)፡፡

ለ. የከሳሽ የቀሩት በከሳሹ ጥፋት ሆኖ የተከሳሹ የቀሩት ግን በጥፋቱ ሳይሆን ከዓቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የከሳሹን ምስክር ለመስማት ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም፡፡ ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት ወይም የከሳሹ ምስክሮች ባይሰሙም በተከሳሽ ምስክር መጣራት ያለባቸው ነጥቦች ካሉ የተከሳሽ ምስክሮችን ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት፡፡

ሐ. የከሳሹ ያልቀረቡት ከዐቅም በላይ በሆነ ችግር ሆኖ የተከሳሹ የቀሩት በተከሳሹ ጥፋት ከሆነ የከሳሹን ምስክሮች ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ መስጠት፡፡ የተከሳሹ ምስክሮች እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም፡፡

1.2. የከሳሽ ምስክር ምንም ሳይቀርቡ የተከሳሽ የተወሰነ ወይም በሙሉ ቢቀርቡ፤

ሀ. የከሳሽ ምስክር ያልቀረቡት ከዓቅሙ በላይ በሆነ ችግር ከሆነ ምስክሮቹ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠትና እንዲሁም የተከሳሹን ምስክሮች መመለስና በሚቀጥለው ቀነ ቀጠሮ እንዲቀርቡ ማዘዝ፡፡ በተከሳሹና በምስክሮቹ ላይ ለደረሰው መጉላላት በቂ ኪሣራ መወሰን፡፡

ለ. በከሳሹ ጥፋት ከሆነ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም፡፡ ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት፡፡ የከሳሹ ምስክር ባይሰሙም በተከሳሽ ምስክር መጣራት ያለባቸው ነጥቦች ካሉ የተከሳሽ ምስክሮችን ብቻ ሰምቶ አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት፡፡

1.3. የከሳሽ የተወሰኑ ብቻ ቀርበው የተከሳሽ በሙሉ ወይም በከፊል ቢቀርቡ

ሀ. ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የቀረቡትን የከሳሽ ምስክር መስማት፡፡ ያልቀረቡት መቅረባቸው የግድ አስፈላጊ ከሆነ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠት፡፡ የተከሳሽ ምስክሮች እንዲመለሱና በሚቀጥለው ቀነ-ቀጠሮ እንዲቀርቡ ማዘዝ፡፡ በተከሳሽና በከሣሹ ምስክሮች ላይ ለደረሰው መጉላላት ተገቢውን ኪሣራ መወሰን፡፡

ለ. በከሳሹ ጥፋት ከሆነ የቀረቡትን ምስክሮች ብቻ መስማት፡፡ የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም፡፡ የተሰሙት የከሳሽ ምስክሮች ብቻ እንደክሱ ካላስረዱ ክሱን መዝጋት ወይም አስፈላጊውን ውሳኔ መስጠት፡፡ የተሰሙት ብቻ ክሱን በማስረዳታቸው ወይም ባያስረዱም አንዳንድ ነጥቦችን ለማጣራት የተከሳሽን ምስክር መስማት አስፈላጊ

ከሆነ መስማት፡፡

1.4. የከሳሽ በሙሉ ቀርበው የተከሳሽ ምንም ካልቀረቡ፡-

ሀ) በተከሳሽ ጥፋት ከሆነ የከሳሽ ብቻ ተሰምተው አስፈላጊው ውሳኔ ይሰጣል፡ ፡ የተከሳሹን ምስክር ለመስማት ሌላ ቀጠሮ አይሰጥም፡፡

ለ) በተከሳሹ ጥፋት ሳይሆን ከዓቅም በላይ በሆነ ችግር ከሆነ የከሳሹን ሰምቶ የተከሳሹ እንዲቀርቡ ሌላ ቀጠሮ መስጠት፡፡ በከሳሹ ላይ ለደረሰው መጉላላት ተገቢውን ኪሣራ ተከሳሽ እንዲከፍል ማዘዝ፡፡

1.5. የከሳሽ በሙሉ ቀርበው የተከሳሽ በከፊል ብቻ ቢቀርቡ፡-

ሀ) በተከሳሹ ጥፋት ከሆነ የከሳሽ ከተሰሙ በኃላ እንደ ክሱ ካስረዱ የቀረቡትን የተከሳሽ ምስክር ብቻ መስማት፡፡ የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀነ ቀጠሮ አይሰጥም፡፡

ለ) ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ወይም ምክንያት ከሆነ የከሳሽ ምስክሮች ከተሰሙ በኃላ እንደ ክሱ አስረድተው ከሆነ የቀረቡትን የተከሳሽ ምስክሮች መስማት፡፡ የቀሩት የተከሳሽ ምስክሮች መቅረብ ለትክክለኛ ፍትህ አሰጣጥ አስፈላጊ መሆናቸው ከታመነበት የቀረቡትን ሰምቶ የቀሩት እንዲቀርቡ ሌላ ቀነ ቀጠሮ መስጠት፡፡ ቀጠሮ ከተሰጠ በከሳሹ ላይ ለደረሰው መጉላላት ተከሳሽ በቂ የሆነ ኪሣራ እንዲከፍል ማዘዝ፡፡

2. ከላይ በቁ. 1 የተመለከተው ሁኔታ ፍ/ቤቱ ለትክክለኛ ፍትህ የግድ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ያልቀረበው ምስክር እንደተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ ከማዘዝ አያግደውም፡፡
3. ምስክሩ የቀረው በባለጉዳዮች ጥፋት ሳይሆን መጥሪያ በትክክል ከደረሰው በኃላ በእምቢተኝነት የቀረ እንደሆነ በቁ. 118 (2) (ለ) የተደነገገው ተፈፃሚ ይሆናል፡፡
4. ምስክሮች ተሟልተው ከቀረቡ ወይም በከፊል ቢቀርቡም የቀረቡት እንዲሰሙ ፍ/ቤት የወሰነ እንደሆነ ምስክሮችን መመርመር ይቀጥላል፡፡
5. የቀረቡትን ምስክሮች በአንድ ቀን ሰምቶ መጨረስ ካልቻለ ፍ/ቤቱ ምስክሮቹን ሁሉ ሰምቶ እስኪጨርስ ድረስ በየዕለቱ አዳሪ የሚሆን ቀጠሮ እየሰጠ ሥራውን ማከናወን አለበት እንጂ

ረጅም ቀጠሮ መስጠት የለበትም (ቁ. 197 (3))።

***የተከራካሪዎቹ ሙግት መጀመርና ምስክሮችን መመርመር***

1. ***ስለ ክሱ መከፈትና ሙግትን የመጀመር መብት***

1.1. ክስን መክፈትና ሙግትን የመጀመር መብት የከሳሽ ነው። ነገር ግን ተከሳሹ ከሳሽ ያቀረበውን ክስ አምኖ ነገር ግን ሕግ ወይም ሌላ ፍሬ ነገር በመጥቀስ የቀረበብኝ ክስ ዋጋ የለውም ብሎ የሚከራከር ከሆነ ሙግቱን የሚጀምረው ተከሳሹ ይሆናል (258(1)) ።

1.2. ክሱን የሚጀምረው ወገን የመክፈቻ ቃሉን ከሰጠና ምስክሮቹ የሚመሰክሩለትን ነጥብ በአጭሩ ካስረዳ በኃላ የሚደግፈውን ማስርጃ አቅርቦ ያሰማል (259(1))።

1.3. ክሱን የሚጀምረው ወገን ማስረጃውን አሰምቶ ከጨረሰ በኃላ ሌላኛው ወገን የራሱን የመካላከያ መክፈቻ ቃል ካሰማና የመከላከያ ምስክሮቹ የሚመሰክሩለትን ነጥብ በአጭሩ ካስረዳ በኃላ የመከላከያ ምስክሩን አቅርቦ ያሰማል (ቁ. 259(2)) ።

2. ***የማስረጃ አቀራረብ***

2.1. ምስክር የምስክርነት ቃሉን ከመስጠቱ በፊት የመኃላ ቃል ወይም የሚሰጠው ቃል እውነተኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ ቃል መስጠት አለበት (261(1))።

2.2. የሚሰጠው የመኃላ ቃል በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት "በዚህ ፍርድ ቤት ፊት የምሰጠው ቃል እውነት፣በሙሉ እውነት፣ እውነት እንጂ ሌላ ምንም እንደማይሆን እምላለሁ።" የሚል መሆን አለበት። ምስክሩ "እምላለሁ" ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ "እምላለሁ" በማለት ፋንታ "አረጋግጣለሁ" ማለቱ በቂ ነው። ምስክሩ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ እንዲምል ማስገደድ አስፈላጊ አይደለም።

2.3. ስለራሱ ጉዳይ የምስክርነት ቃል መስጠት የሚፈልግ ተከራካሪ ወገን መመስከር ይችላል። የሚመሰክረውም እውነት እንደሚናገር ከማለ ወይም ካረጋገጠ በኃላ መሆን አለበት።

2.4. ምስክሩን ያቀረበው ወገን ለራሱ ምስክሮች ዋና ጥያቄ (examination-in-chief) በማቅረብ ይመረምራቸዋል፡፡ በዋና ጥያቄ ወቅት መሪ ጥያቄ አይፈቅድም፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱን በማስፈቀድ መሪ ጥያቄ መጠየቅ ይቻላል (ቁ. 263 (1) (2))፡፡

2.5. በዋና ጥያቄ ጊዜ የሚቀርበው ጥያቄ ጭብጡን የሚመለከትና ምስክሩ በቀጥታ ወይም በሌላ መንገድ በሚያውቀው ወይም ሊያውቀው በሚችለው ነገር ላይ ብቻ ነው (263(1)) ፡፡

2.6. ምስክሩን ያቀረበው ወገን ዋና ጥያቄ አቅርቦ ከጨረሰ በኃላ ተቃራኒው ወገን መስቀልኛ ጥያቄ በማቅረብ ምስክሩን ይመረምረዋል፡፡ በመስቀልኛ የሚቀርበው ጥያቄ ምስክሩ በዋና ጥያቄ የሰጠው የምስክርነት ቃል የተሳሳተበትን፣ ሀሰት ነው የሚባልበትን ወይም አጠራጣሪ መስሎ የተገመተበትን ነጥብ ፍ/ቤቱ እንዲረዳ ለማድረግ የሚቀርብ ነው፡፡ ስለዚህ በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት በዋና ጥያቄ ላይ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወደዚያ የማያመራ አዲስ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡ ሀኖም በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት ምስክሩን መምራት ይቻላል (ቁ. 263 (3)) ፡፡

2.7. የመስቀልኛ ጥያቄ ካለቀ በኃላ የመጀመሪያው ጠያቂ የማጣሪያ ጥያቄ ያቀርባል፡፡ በማጣሪያ ጥያቄ ወቅት በመስቀልኛ ጥያቄ ላይ ከተነሳው ነጥብ ጋር የማይገናኝ ወይም ወደዚያ የማያመራ አዲስ ጥያቄ መጠየቅ አይቻልም፡፡ ጥያቄው የሚጠየቀው ምስክሩ በመስቀልኛ ጥያቄ ወቅት የሰጠውን ቃል ለማብራራት ብቻ ነው (ቁ. 263 (4))፡፡

2.8.ምስክርን የመመርመር ሥራ በዋናነት የባለጉዳዮቹ ቢሆንም ስለ ጉዳዩ መብራራትና ስለክርክሩ አወሳሰን ጠቃሚ መስሎ የታየው እንደሆነ ፍ/ቤቱ በማናቸውም ጊዜ ምስክሩን ለመጠየቅ ይችላል (ቁ. 261(4)) ፡፡

2.9. በጥያቄ አቀራረብ ላይ መቃወሚያ ሲነሳ ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን ሳይቀበል ለጥያቄው መልስ እንዲሰጥበት ያዘዘ እንደሆነ መቃወሚያው የቀረበበትን ጥያቄ፣ የተሰጠውን መልስ፣ የተቃወመውን ሰው ስም፣ መቃወሚያው ውድቅ የሆነበት ውሳኔ በመዝገቡ ላይ ማስፈር አለበት (ቁ. 270)፡፡

2.10. አንድ ባለጉዳይ ያቀረበው ምስክር መልሶ በባለጉዳዩ ላይ ቢመሰክር ባለጉዳዩ ይህ ቃል እንዳይመዘገብ ምስክሩም ቃሉን መስጠት እንዲያቆም ፍ/ቤቱን መጠየቅ አይችልም፡፡ ጥያቄው ቢቀርብም ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ሳይቀበል የምስክሩን ቃል መመዝገብ አለበት፡፡ ባለጉዳዩ ጥያቄውን ቢያቀምም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ መስሎ ከታየው ምስክሩን

መመርመር መቀጠል ይችላል፡፡

2.11. የምስክሩ ቃል የተሰጠው በችሎቱ ቋንቋ ሳይሆን በሌላ ቋንቋ ከሆነ አስተርጓሚ ይመደባል፡፡ አስተርጓሚውም የመተርጐም ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የመኃላ ቃል ወይም በትክክል እንደሚተረጉም የሚያረጋግጥ ቃሉን መስጠት አለበት፡፡ የመኃላ ቃሉም በፍ/ሥ/ሥ/ሕጉ የፎርም ሠንጠረዥ ላይ በተገለፀው መሠረት "በዚህ ፍ/ቤት የሚሰጠኝን ማስርጃ በእውነትና የችሎታዬን ያህል ልተረጉም እምላለሁ፡፡" የሚል መሆን አለበት፡፡ አስተርጓሚው "እምላለሁ" ማለትን ኃይማኖቱ የማይፈቅድለት ከሆነ "እምላለሁ" በማለት ፋንታ "አረጋግጣለሁ" ማለት ይችላል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም ቁራን ይዞ እንዲምል ማስገደድ ተገቢ አይደለም፡፡

2.12. የተሰጠው የምስክርነት ቃል በቁ. 269 የተደነገገውን ፎርምና ይዘት ተከትሎ መመዝገብ ለለበት፡፡

## 3. <u>የፍ/ቤቱ ሥልጣን</u>

3.1. ምስክሮችን አቅርቦ ማሰማት በዋናነት የባለጉዳዮቹ ቢሆንም ለክርክሩ ጠቃሚ መስሎ ከታየው ተከራካሪዎቹ ካቀረቡት ምስክር በቀር ተጨማሪ ምስክር ጠርቶ መስማት ይችላል (ቁ. 264)፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ ተጨማሪ ምስክር መስማት ያለበት ለፍትህ አሰጣጥ የግድ አስፈላጊ ሲሆንና በውስን ሁኔታዎች ብቻ እንዲሁም ገለልተኝነቱን በማይነካ መልኩ መሆን አለበት፡፡

3.2. ለፍትህ አሰጣጥ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ክርክሩ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝበት ጊዜ ቀድሞ መስክረው የነበሩትን ምስክሮች ፍ/ቤቱ እንደገና አስጠርቶ ማናቸውንም ተገቢ መስሎ የታየውን ጥያቄ ሊጠይቃቸው ይችላል (ቁ. 266)፡፡

3.3. በቁ. 265 የተገለፀው ሁኔታ ሲያጋጥም ፍ/ቤቱ የምስክሩን ቃል ባስቸኳይ መቀበል ይችላል፡፡

3.4. ክርክሩ በማናቸውም ደረጃ በሚገኝበት ጊዜ ሁሉ ፍ/ቤቱ ክርክር የተነሳበትን ማናቸውንም ንብረት ወይም ማናቸውንም ነገር ሥፍራው ድረስ ሄዶ በማየት

ለመመርመር ይችላል(ቁ. 272)፡፡

4. <u>የምስክር ቃልን ለመስጠት ፈቃደኛ ስላለመሆንና ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል</u>

4.1. ማንኛውም በፍ/ቤት ችሎት የቀረበ ተከራካሪ ወገን ወይም ሌላ ሰው የምስክርነት ቃሉን እንዲሰጥ ወይም በእጁ የሚገኘውን ወይም በሥልጣኑ ሥር የሚገኘውን የፅሑፍ ማስረጃ እንዲያቀርብ ፍ/ቤቱ ሲያዘው በቂ ባልሆነ ወይም በሕግ በማይደገፍ ምክንያት ትዕዛዙን ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ወዲያውኑ ይፈርድበታል፡፡ ወይም ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢ መስሎ የታየውን ሌላ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

4.2. በዚህም መሠረት ፍ/ቤቱ በቁ. 480 በተጠቀሰው መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡

4.3. በተጨማሪም እምቢተኛውን በወ/መ/ሕ/ቁ. 442 መሠረት ወዲያው መቅጣት ይችላል (ቁ. 481)፡፡ ሆኖም ይህን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ምስክሩ ቃሉን ለመስጠት ያልፈለገበትን ምክንያት (ለምሣሌ ጥያቄውን ቢመልስ የወንጀል ክስ ሊያስከትልብኝ ይችላል ብሎ በመፍራት እንደሆነ) ማጣራትና ምስክሩ ቃሉን መስጠቱ አስፈላጊ መሆኑን፣ ቃሉን መስጠቱም ግዴታው መሆኑን፣ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለ ግን የወንጀል ቅጣት ሊወሰንበት እንደሚችል ማስርዳትና አስፈላጊውን ምክር ሁሉ መስጠት አለበት፡፡ ፍ/ቤቱ አስፈላጊውን ማጣሪያ ካደረገና ተገቢውን ምክር ከሰጠ በኃላ ምስክሩ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለና ሌላ አማራጭ የሌለ መስሎ ከታየው የወንጀል ቅጣቱን መወሰን ይችላል፡፡

4.4. ምስክሩ ሐሳቡን ቀይሮ የምስክርነት ቃሉን ለመስጠት ፈቃደኝነቱን ከገለፀና ቃሉን ከሰጠ ፍ/ቤቱ የወሰነበትን ቅጣት ሊያቀልለት ወይም ቅጣቱን ሙሉ በሙሉ አንስቶለት በተግሳፅ ብቻ ሊያልፈው ይችላል፡፡

4.5. ምስከሩ ግልፅ የሆነ የሐሰተኛ ምስክርነት ቃል ከሰጠ ቃሉን ያስተካክል እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተገቢውን ጥረት ካደረገና አስፈላጊውን ምክር ከሰጠው እንዲሁም በሐሰት መመስክር ወዲያው በወንጀል እንደሚያስቀጣው ካስረዳው በኃላ ምስክሩ በእምቢተኝነቱ ከቀጠለ በወ/መ/ሕ/ቁ.447 መሠረት ምስከሩን ወዲያው መቅጣት ይችላል (ቁ. 481)፡፡

4.6. ከላይ በቁ. (4.5.) በተገለፀው መሠረት ቅጣት የተወሰነበት ምስክር በራሱ ፈቃድ

ቃሉን ወዲያው ካነሳው ወይም ካስተካከለ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን ሲያቀልለት ወይም ቅጣቱን ሙሉ በሙሉ በማስቀረት በተግሳፅ ብቻ ሊያልፈው ይችላል (ወ/መ/ሕ/ቁ. 448)፡፡

4.7. የሐሰት ቃል የሰጠው ተከራካሪ ወገን ከሆነ በወ/መ/ሕ/ቁ. 446 መሠረት ወዲያው ቅጣት ሊበይንበት ይችላል፡፡ በዚህም ጊዜ ከላይ በቁ. (4.5.) እና (4.6.) የተመለከቱት ሁኔታዎች እና ጥንቃቄዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡፡

**<u>ከፍትሃብሄር መርሃ ችሎት</u>**

የተግባር ልምምድ

አባሪ 1-3 ያሉ ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የሙግት ልምምድ አድርግ፡፡ የመክፈቻ ንግግር፣ የምስክሮችን ቃልና አንዳንድ አስፈላጊ መስሎ የሚታያቸውን ሁኔታ ሰልጣኞች በራሳቸው እንዲፈጥሩ ይመከራል፡፡

# የሙግት ቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴዎች

ሙግቱን/ክርክሩን ለመስማት የሚሰጥ ቀጠሮ ከሌሎች ቀጠሮዎች በተለየ መታየት ያለበት ተግባር ነው፡፡ ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው የክስ መስማቱ ሂደት ከተጠናቀቀ በሃላ ጭብጥ ተመስርቶ ሙግቱ ይሰማል፡፡ የሙግት መስማቱ ሂደት ሰብሰብ ያለና አንዴ ከተጀመረ ሳይበጣጠስ ተሰምቶ መጠናቀቅ እንዳለበት የስነስርአት ህጉ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ በመሆኑም ሙግቱን ለመስማት የሚሰጥ ቀጠሮ ይህንን ግብ ሊመታ የሚችል መሆን አለበት፡፡

የቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴ ከሳይንስ ይልቅ አርት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ዳኞች ቀጠሮ በሚዙበት ጊዜ በርካታና ሊገመቱ የማይችሉ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ውሳኔ ላይ የሚደርሱ በመሆኑ አንድ ሙግት ይሰማል በተባለ ቀን ላይሰማ ስለሚችል የፍርድ ቤት ሃብት ሊባክን የሚችልበት አጋጣሚ በርካታ ነው፡፡

ለምሳሌ በአንድ ቀን ምን ያህል ጉዳይ ለክስ መስማት፣ ፍርድ ለማንበብ፣ ሙግት ለመስማት፣ ሌሎች ተግባራትን ለማከናወን መቀጠር እንዳለበት ዳኛው የፍርድ ቤቱንና የችሎቱን እውነታ ግምት ውስጥ በማስገባት መወሰን አለበት፡፡

## የራሳቸውን ጉዳይ ይዘው የሚከራከሩ ተሟጋቾች ጉዳይ መምራት

የራሳቸውን ጉዳይ ፍርድ ቤት ይዘው በመምጣት የሚከራከሩ ባለጉዳዮች በፍትሃብሄር ክርክር በአንዱ ሂደት ያለ ጠበቃ እገዛ ክርክር የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ተከራካሪዎቹ፡-

- አቤቱታቸውን በራሳቸው ፅፈው ለፍርድ ቤት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
- አቤቱታውን በባለሙያ አፅፈው የፍርድ ሂደቱን ግን በራሳቸው ሊከራከሩ ይችላሉ፡፡
- ወይም በፍርድ ሂደቱ በተወሰነ ደረጃ ላይ በባለሙያ በሌላ ደረጃ ደግሞ በራሳቸው ሊከራከሩ ይቻላሉ፡፡

በኢትዩጵያ ፍርድ ቤቶች ምን ያህሉ ራሳቸውን ወክለው ይከራከራሉ በሚለው ላይ የተሰራ ጥናት ባይኖርም በአገሪቱ ውስጥ የሚቀርቡ አብዛኛው ጉዳዮች በተከራካሪው በራሱ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የህግ እውቀትና ክህሎታቸው ውስን የሆነ ተከራካሪዎች ፍርድ ቤት በሚቀርቡበት ጊዜ ለፍርድ ቤቱ ከባድ ፈተናን ይደቅናሉ፡፡

ተከራካሪዎች በባለሙያ የማይታገዙባቸው በርካታ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን ጥቂቶቹ፡-

- የጥብቅና ስራ አለመስፋፋት
- ለጥብቅና የሚከፈል ገንዘብ ከተከራካሪው አቅም በላይ መሆን
- የህግ ድጋፍ የሚያደርጉ ድርጅቶች አለመኖር
- የህግ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ አለመሆን
- የባለሙያ ድጋፍ አስፈላጊ መሆኑን አለማወቅ
- ወዘተ

ባለጉዳዮች የራሳቸውን ጉዳይ ይዘው ሲመጡ ዳኞች የሚገጥማቸው ፈተና፡-

- የፍትሃብሄር ሙግት አካሄድ ግራ ቀኙ በሚያቀርቡት ክርክር (adversarial) ሲሆን ተከራካሪዎቹ ክርክራቸውን በራሳው ስለማያቀርቡ የፍርድ ቤቱ በራስ ተነሳሽነት የሚፈፅማቸው ተግባራት ከህጉ ጋር መጋጨት
- በአግባቡ አለመከራከር (የመክፈቻ ንግግር፣ ዋና ጥያቄ፣ መስቀለኛ ጥያቄ፣ ወዘተ)
- ፍርድ ቤቱ ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎች ተገቢነት ያላቸውን መልሶች አለመስጠት
- ቴክኒካል የሆኑ ሂደቶችን ባለመፈፀም ጉዳዮች በፍርድ ቤት ረጅም ጊዜ ማስቆጠር
- የክርክር አለመመጣጠን (በተለይ አንደኛው ተከራካሪ በጠበቃ የሚደገፍ ከሆነ)

ከላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶች በባለሙያ ያልታገዙ ባለጉዳዮች ሲቀርቡ ፍርድ ቤቶች ለእንደዚህ አይነት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የተከራካሪ ወገኖች ባሕሪ የተለያየ ቢሆንም የጉዳዮች ፍሬ ነገርና ህጉ ተገናዝቦ ተመሳሳይ የሆነ ውጤት መምጣት ይኖርበታል፡፡ ይህ አረፍተነገር በውስጡ የህግ የበላይነትን ፅንሰ ሃሳብ ያዘለ ነው፡፡

በራስ የሚከራከር ተከራካሪ ወገን ሲያጋጥም የሚከተሉትን መርሆች ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቃል፡-

- በራሱ የቀረበው ተከራካሪ የህግ ባለሙያ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ፣ የህግ ባለሙያ ይዞ መከራከር እንደሚችል ማሳወቅ
- ዝግጅት ማድረግ፡፡ ዳኛው ከፍተኛ ሚና ስለሚኖረው ጉዳዮን የሚሸፍነውን ህግ በስፋት በማጥናት ከፍተኛ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች በጠበቃ የሚታገዙ ቢሆን ህጉን በራሳቸው የክርክር መስመር ፈትሸው ተዘጋጅተው ስለሚቀርቡ ዳኛውን ያግዛሉ፡፡
- የፍርድ ሂደቱን በተመለከተ ገለፃ ማድረግ ለምሳሌ “በዚህ ጉዳይ ሁለቱንም ወገን መስማት እንደሚገባ፣ መጀመሪያ ከሳሽ ቀጥሎ ተከሳሽ እንደሚሰማ፣ በችሎት የሚደረግ ሂደት በሙሉ እንደሚመዘገብ፣ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ማስረጃውን በሚያሰማበት ጊዜ ማቋረጥ እንደማይገባ፣ ወዘተ”

- በመሰረታዊ የህግ ፅንሰ ሃሳቦች ላይ አጭር ገለፃ መስጠት ለምሳሌ የማስረዳት ሸክም የማን እንደሆነ፣ ወዘተ
- ጠቅለል ባለ መልኩ ምን አይነት ማስረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚችሉ ማብራሪያ መስጠት፣ ወዘተ
- ሂደቱን የህግ ባለሙያ ያልሆነ ሰው ሊገባው በሚችል መልኩ መምራት
- ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ጥያቄዎችን መጠየቅ

## የውስብስብ ጉዳዮች ሙግት አሰማም ዘዴ

በክፍል አንድ ለመመልከት እንደሞከርነው ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች አንድ አይነት ባሕሪ የላቸውም፡፡ አብዛኛዎች ጉዳዮች ቀላል ሲሆን ጥቂት ጉዳዮች ወስብስብ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በተለይ ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መስፋፋት ጋር ተያይዞ በርካታ የግንባታ፣ የኢንዱስትሪና ሌሎች አገልግሎቶች መስፋፋት ውስብስብ የሆኑ ውዝግቦች እየፈጠረ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ለረጅም ጊዜ ከተለመዱ ጉዳዮች ወጣ ያሉና ፈታኝ ጉዳዮች እያጋጠሙ ይገኛሉ፡፡

የሚከተሉትን ቀላል ጉዳይን ከውስብስ ጉዳይ ለመለየት እንደመመዘኛ ልንጠቀምባቸው እንችላለን፡-

1. የጉዳዮ አይነት (ለምሳሌ በፍርድ ቤቶች ልምድ የኮንስትራክሽን ክርክሮች፣ ቴክኒካዊ እውቀት የሚፈልጉ ክርክሮች፣ የአካባቢ ብክለት ክርክሮች፣ ከህክምና ጋር ተያይዘው የሚነሱ የውል ውጭ ሃላፊነት ክርክሮች፣ ከፍተኛ መጠን ያለው የጉዳት ካሳ ክርክር፣ ወዘተ)
2. የተከራካሪዎች ብዛት (በአንድ ጉዳይ ከአምስት በላይ ተከሳሾች ካሉ መጥሪያ አደራረስ፣ በዝግጅት፣ በሙግት መስማት ሂደት ውስብስ የሆነ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ)
3. የማስረጃ ብዛት (በሺዎች የሚቆጠሩ ሰነዶች፣ በመቶዎች የሚቆጠሩ ምስክሮች)
4. ውስብስብ የህግ ጥያቄ የሚያስነሱ ጉዳዮች (ለምሳሌ የህገ-መንግስት ትርጉም የሚያስነሳ ጉዳይ ስልጣኑ ወዳለው አካል መመራት ሊኖርበት ይችላል)

ውስብስብ ጉዳዮችን ለመምራት መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች፡-

- ውስብስብ ጉዳዮችን አስቀድሞ መለየት ለምሳሌ በአይነት
- ከፍተኛ ዝግጅት፡፡ ዳኞች ጉዳዮ ውስጥ ቀደም ብሎው በመግባት ዝግጀት ሊያደርጉ ይገባል፡፡
- አስቀድሞ ማቀድ፡፡ በተለይ የፍርድ ቤቱን ሃብት (የዳኛውን ጊዜ፣ ችሎት አጠቃቀም፣ ቀጠሮ አሰጣጥ፣ ወዘተ) ጉዳዮን ለመፍታት በሚያስችል መልኩ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡
- ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈተናዎችንና ችግሮችን አስቀድሞ መተንበተይና ማስተካከያ ስልቶችንና መንገዶችን ማዘጋጀት
- ተከራካሪዎችን ማትጋት

## ክፍል 4

# የይግባኝ ጉዳዮችን መምራት

**የክፍሉ ግቦች**

**ይህ ክፍል ከተጠናቀቀ በኃላ ሰልጣኞች**

- ✓ የፍትሃብሄር ይግባኝ ሥነ-ሥርዓት ሂደቶችን ይለያሉ፡፡
- ✓ የይግባኝ ክርክርን ለመስማት መደረግ ያለበትን ዝግጅት ይለያሉ፡፡
- ✓ ይግባኝ ይሰማሉ፡፡

## የይግባኝ ሂደቶች

የይግባኝ ክርክር ሂደት በሁለት ደረጃ ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፡-

- ወደ ዋናው ክርክር ለመግባት ይግባኙን መቀበል
- ይግባኙ ተቀባይነት ካገኘ ይግባኝ ባይና መልስ ሰጭን ጠርቶ ማከራከር ናቸው፡፡

**ይግባኙን ስለመቀበል**

ሀ/ ፍ/ቤቱ የይግባኝ ማመልከቻውንና ይግባኝ ባይ ወይም ጠበቃው በቃል የሚያቀርቡትን ክርክር ከሰማ በኋላ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠበትን የመዝገብ ግልባጭ መርምሮ ፍርዱ ጉድለት የሌለበት መሆኑን ከተረዳው መልስ ሰጪውን ሳይጠራ ይግባኙን ዘግቶ አቤት ባዩን ሊያሰናብት ይችላል (ቁ 337 )፡፡

ለ/ በቁ 337 መሠረት ይግባኙን ለመዝጋት የሚሰጠው ትዕዛዝ ዝርዝር ጉዳዩች ውስጥ ሳይገባ ይግባኙ ውድቅ መሆኑን ብቻ በአጭሩ የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

ሐ/ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ውድቅ ካላደረገው (ከተቀበለው ) ይግባኙ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ወስኖ መልስ ሰጪው እንዲቀርብ መጥሪያውንና የይግባኝ ማመልከቻውን ይልክለታል፡፡

**ከፍትሃብሄር መርሃ ችሎት**

የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት አንድ የይግባኝ አቤቱታ ሲቀርብለት ይግባኙን በሁለቱም ደረጃዎች ለመስማት ዝግጅት ሊያደርግ ይገባል፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በስር ፍርድ ቤት የቀረበውንና የተደረገውን ክርክር በአግባቡ መመርመር አለበት፡፡ የይግባኝ ቅሬታ ነጥብን ከስር ፍርድ ቤት መዝገብ ጋር አገናዝቦ ዝግጅት ማድረግ ይገባል፡፡

## ይግባኙን ስለመስማት

ሀ/ ይግባኙ በሚሰማበት ጊዜ ይግባኝ ባዩ አስቀድሞ የቃል ክርክሩን ይጀምራል (ቁ.339 (1))፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በተለይ ካልፈቀደ በቀር ይግባኝ ባዩ በይግባኝ ማመልከቻው ላይ ዘርዝሮ ያልገለፀውን አዲስ ነገር በማንሳት የቃል ክርክሩን ማቅረብ አይችልም (ቁ.328 (2 )፡፡

ለ/ ይግባኝ ባዩ የቃል ክርክሩን ካሰማ በኋላ ቅሬታው መሠረት የሌለው መሆኑን ፍ/ቤቱ ከተረዳ የመልስ ሰጪውን ክርክር መስማት ሳያስፈልግ ፍ/ቤቱ ይግባኙን ወዲያው ሊሰርዘው ይችላል (ቁ 339 (2)፡፡

ሐ/ ይግባኙ ወዲያው ካልተሠረዘ መልስ ሰጪው የመከላከያ መልሱን በቃል ያሰማል፡፡ ቀጥሎም ይግባኝ ባዩ የመልስ መልሱን በቃል ክርክር ያቀርባል(ቁ.339(3) )፡፡

መ/ በመሠረቱ መልስ ሰጪው መልሱን በቃል ክርክር ማቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም ፍ/ቤቱ አስፈላጊ መስሎ ከታየው የመከላከያ መልሱ በፅሑፍ እንዲቀርብ ማዘዝ ይችላል (ቁ 339 (3) )፡፡

ሠ/ ይግባኝ ባዩ ባቀረበው የይግባኝ መዝገብ ላይ መልስ ሰጪው የራሱ የይግባኝ ቅሬታ (Cross-appeal ) ማቅረብ ይችላል(340)፡፡

ረ/ የይግባኝ ክርክሩ ካለቀ በኋላ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**ከፍትሃብሄር መርሃ ችሎት**

<u>የተግባር ልምምድ</u>

ከዚህ ሞጁል ጋር 6 የሰበር መዝገቦች ተያይዘዋል፡፡ የሰበርና የይግባኝ አሰማም ሂደት ልዩነት የላቸውም፡፡ በመሆኑም በቡድን ተከፋፍላችሁ እያንዳንዱን መዝገብ በይግባኝ ሙግት አሰማም ሂደት በልምምድ ለክፍሉ አሳዩ፡፡

# አባሪ 1

ሰኔ 20 ቀን 1999 ዓ/ም

## ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

## አዲስ አበባ

ከሣሽ ዶ/ር አህመድ አብዲ

አድራሻ፡-ክልል አዲስ አበባ ክፍለከተማ ቂርቆስ ቀበሌ 12 የቤት ቁ. 312

ተከሣሽ አድአ የእንስሳት መድሃኒት ፋብሪካ

አድራሻ፡-ክልል አዲስ አበባ ክፍለከተማ ቂርቆስ ቀበሌ 14/16 የቤት ቁ. 1009

<u>በብድር የተሰጠ ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበ ክስ፡፡</u>

1. ፍርድ ቤቱ ይህንን ጉዳይ ተቀብሎ የማየት ሥልጣን አለው፡፡
2. ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ብር 1,500,000 ነው፡፡
3. ከሳሽ በጉዳዩ በጠበቃ አማካይነት ይከራከራል፡፡
4. ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ በህግ ችሎታ አላቸው፡፡
5. <u>የክሱ ፍሬ ነገር</u>

5.1. ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ/ም በአዲስ አበባ ከተማ ከሳሽ እና ተከሳሽ ባደረጉት ስምምነት/ውል ከሳሽ ለተከሳሽ ብር 1,500,000 (አንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺ.ህ) አበድሮታል፡፡

5.2.ገንዘቡም እስከ ጥር 30 ቀን 1997 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተከሳሽ ገንዘቡን ለመመለስ የተስማማ መሆኑን ሰነዱ ያሳያል፡፡

5.3.ተከሳሹ ብር 1,100,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ.ህ) በተለያየ ጊዜ በባንክ በኩል የተረከበ ሲሆን ቀሪው ብር 400,000 (አራት መቶ ሺ.ህ) በኮሚሽንነት የሚታሰብ ሆኖ ብር 1,500,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ.ሕ) በብድር ተረክቦ በውሉ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አልመለሰም፡፡

6. ስለዚህ፡-

1.ተከሣሽ በውል በገባው ግዴታ መሠረት የሚፈለግበትን ብር ባለመክፈሉ ከሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ 9 በመቶ ወለድ ጋር

2.ከሳሽ ይህንን ክርክር ለማካሄድ ያወጣቸውን ወጪዎች ተከሣሽ እንዲከፍል እንዲወሰንልኝ ለፍርድ ቤቱ አመለክታለሁ፡፡

ከዚህ በላይ የተገለፀው ነገር ሁሉ እኔ እስከማውቀው እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ከሣሽ

ሰኔ 20 ቀን 1998 ዓ/ም

## ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

## አዲስ አበባ

ከሣሽ ዶ/ር አህመድ አብዲ

አድራሻ፡-ክልል አዲስ አበባ ክፍለከተማ ቂርቆስ ቀበሌ 12 የቤት ቁ. 312

ተከሣሽ አድአ የእንስሳት መድሃኒት ፋብሪካ

አድራሻ፡-ክልል አዲስ አበባ ክፍለከተማ ቂርቆስ ቀበሌ 14/16 የቤት ቁ. 1009

**<u>በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 223 መሠረት የቀረበ የማስረጃ ዝርዝር</u>**

1. <u>የሰው ማስረጃ</u>

1.1.በከሣሽ እና በተከሣሽ መካከል የብድር ውል የተደረገ ስለመሆኑ የሚያስረዱ

1.1.1. አቶ ሐጎስ ገ/ሕይወት አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 456

1.1.2. አቶ እንዳለ መስፍን አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 456

1.2. ለተከሣሽ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ከሣሽ ሲሰጥ/ሲሰጥ ሲሞክር የነበሩ ምስክሮች፡-

1.2.1 ወ/ሮ አልማዝ አልማው_አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 9 የቤት ቁጥር 232

1.2.2 አቶ ገሰሰ ሀይሉ  አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 9 የቤት ቁጥር 232

2. የጽሑፍ ማስረጃ

2.1.በከሳሽ እና በተከሳሽ መካከል ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ/ም  የተደረገ የብድር ውል 2 ገጽ ፎቶ ኮፒ (ዋናው እኔ ጋር ይገኛል)፣

2.2.የብድር ገንዘቡ ለከሳሽ የተሰጡበት የባንክ ደረሰኞች 10 ገፅ ፎቶ ፎቶ ኮፒ (ዋናው እኔ ጋር ይገኛል)፣

2.3.ግንቦት 7 ቀን 1998 ዓ/ም ለተከሣሽ የተሰጠ የተሞከረ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ 1 ገጽ ፎቶ ኮፒ (ዋናው ከተከሳሽ ጋር ይገኛል)፣

.

የክሱ ጭብጥ ካልተለወጠ በቀር ከዚህ በላይ ከቀረበው ውጭ ሌላ አስረጅ ወይም ማስረጃ የሌለኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ከሣሽ

ሐምሌ 20 ቀን 1999 ዓ/ም

**ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት**

**አዲስ አበባ**

ከሣሽ ዶ/ር አህመድ አብዲ

አድራሻ፡-ክልል አዲስ አበባ ክፍለከተማ ቂርቆስ ቀበሌ 12 የቤት ቁ. 312

ተከሣሽ  አድአ የእንስሳት መድሃኒት ፋብሪካ

አድራሻ፡-ክልል አዲስ አበባ ክፍለከተማ ቂርቆስ ቀበሌ 14/16 የቤት ቁ. 1009

<u>ከሳሽ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ/ም ላቀረበው ክስ የተሰጠ መልስ፡፡</u>

ከሳሽ ሰኔ 30 ቀን 1998 ዓ/ም በተፃፈ ላቀረበው ክስ ተከሳሽ የሚከተለውን መልስ ይሰጣል፡፡

1. የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

1.1. ይህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ለሽምግልና ቀርቦ የተወሰነ በመሆኑ ከሳሽ ክስ ሊያቀርብበት የማይችል ስለሆነ በፍትሃብሄር ስነስርአት ህግ ቁጥር 244 (2) ረ መሰረት የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.2. ገንዘቡ መመለስ ነበረበት ተብሎ በክሱ ላይ የቀረበው ጥር 30 ቀን 1997 ዓ/ም ሲሆን ክሱ የቀረበው ሰኔ 20 ቀን 1999 ዓ/ም ሁለት አመት ካፈለው በኃላ ነው፡፡ በፍትሃብሄር ህግ ቀጥር 2024 (ረ) ላይ በብድር የተሰጠ ገንዘብ በሁለት አመት ጊዜ ውስጥ እንዲመለስ ካልተጠየቀ ወይም የዚህ ሁለት አመት የጊዜ ገደብ ካለፈ ሊጠየቅ እንደማይችል የሚደነግግ በመሆኑ የቀረበው ክስ የፍተሃብሄር ስነስርአት ህግ ቁጥር 244(2) ሠ መሰረት ታግዷል፡፡

1.3. ተከሳሽ ገንዘብ ለማበደሩ በምስክሮች የተረጋገጠ ማስረጃ ያላቀረበብኝ ስለሆነ የቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡

1.4. ተከሳሹ ያቀረበው ክስ ከላይ በተመለከቱት ምክንቶች ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያዎችን ተቀብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 245 መሰረት እንዲያሰናብተን እንጠይቃለን፡፡ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያዎችንን የማይቀበለን ቢሆን የሚከለተውን የተሟላ መልስ እንሰጣለን፡፡

2. መልስ

2.1. የተከሳሽ ፋብሪካ በሚቋቋምበት ጊዜ ከሳሽ ኢንቬስተር ነኝ ገንዘብ አለኝ፣ ከተከሳሹ ድርጅት ጋር እሰራለሁ በሚል ግንኙነት ያደርጉ ነበር፡፡ ሆኖም ከሳሹ በቃላቸው ሳይፀኑ ተከሳሽ ድርጅትን በአቋራጭ ለመቆጣር የሞከሩ ሲሆን ከዚህ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ፋይሎች አሉን፡፡ አሁን ከሳሹ ያቀረቡት ክስ ከዚህ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይህንን ተገንዝቦ ውድቅ እንዲያደርግልን እንጠይቃለን፡ ፡

2.2. አንድ በፁሁፍ የተደረገ ውል የፍትሃብሄር ህጉ በሚያዘው መሰረት በምስክሮች ካልቀረጋገጠ ዋጋ የለውም፡፡ ከሳሽ በማስረጃነት ያቀረበው የብድር ውሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1727(2) በሚያዘው መሰረት በምስክሮች ያልተረጋገጠ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣

2.3. ከሳሽ ብር 1,100,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ) ለተከሳሽ ገቢ አላደረጉም፣ ገቢ ተደርጎባቸዋል የተባሉት ሰነዶች ለብድሩ የተሰጡ መሆኑን አያሳዩም፣

2.4. በኮሚሲዮን ታስቦልኛል የሚሉት ብር 400,000 (አራት መቶ ሺህ) ባለ አክሲዮኖች ያፀደቁት አይደለም፣ አገልግሎት ሳይሰጥም ኮሚሽን ሊሰጥ ስለማይችል ተቀባይነት የለውም፣

2.5. የብድር ውል በተባለው ላይ ወለድ እንዲከፈል ስምምነት ያልተደረገ በመሆኑ ውለድ እንዲከፈል የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡

ከዚህ በላይ የተገለፀው ነገር ሁሉ እኔ እስከማውቀው እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ተከሳሽ

ሰኔ 20 ቀን 1999 ዓ/ም

## ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

## አዲስ አበባ

ከሣሽ    ዶ/ር አህመድ አብዲ

አድራሻ፡-ክልል አዲስ አበባ ክፍለከተማ ቂርቆስ ቀበሌ 12 የቤት ቁ. 312

ተከሣሽ  አድአ የእንስሳት መድሃኒት ፋብሪካ

አድራሻ፡-ክልል አዲስ አበባ ክፍለከተማ ቂርቆስ ቀበሌ 14/16 የቤት ቁ. 1009

**በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 መሠረት የቀረበ የማስረጃ ዝርዝር**

1. የሰው ማስረጃ
   - 1.1. በከሣሽ እና በተከሣሽ መካከል የብድር ውል አለመደረጉን የሚያስረዱ
     - 1.1.1. አቶ አበበ ይመኑ    አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 456
2. የጽሑፍ ማስረጃ

2.1. የተከሳሽ ድርጅት የመመስረቻ ጹሁፍ 12 ገጽ ፎቶ ኮፒ (ዋናው እኔ ጋር ይገኛል)፣

2.2. የተከሳሽ ፋብሪካ ግንባታ ሰነዶች 10 ገፅ ፎቶ ፎቶ ኮፒ (ዋናው እኔ ጋር ይገኛል)፣

የክሱ ጭብጥ ካልተለወጠ በቀር ከዚህ በላይ ከቀረበው ውጭ ሌላ አስረጅ ወይም ማስረጃ የሌለኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

የክሱ ጭብጥ ካልተለወጠ በቀር ከዚህ በላይ ከቀረበው ውጭ ሌላ አስረጅ ወይም ማስረጃ የሌለኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ተከሣሽ

ጥር 22 ቀን 2000 ዓ/ም

ዳኛ፡-

ከሳሽ፡- ዶ/ር አህመድ አብዲ

ጠበቃ፡- አቶ አብደላ አሊ ቀረቡ

ተከሳሽ፡- አድአ የእንስሳት መድሃኒት ፋብሪካ

ጠበቃ፡- አቶ አበበ ወርቄ ቀረቡ

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ተመልክቶ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል።

## ፍርድ

ጉዳዩ ለዚህ ፍርድ ቤት ሊቀርብ የቻለው ከሳሽ ተከሳሹ ያበደርኩትን ገንዘብ አልመለሰልኝም በሚል ሚያዚያ 15 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ ክስ በማቅረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ ፍሬ ነገር ባጭሩ የሚከተለው ነው፡-

ተከሳሽ ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ/ም በተፈረመ ከከሳሽ ብር 1,500,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺሕ) ለመበደር ተስማምቷል፡፡ ገንዘቡም እስከ ሰኔ 30 ቀን 1997 ዓ/ም ባለው ጊዜ ውስጥ ተከሳሽ ገንዘቡን ለመመለስ የተስማማ መሆኑን ሰነዱ ያሳያል፡፡

ከሳሽ ባቀረበው ክስ ላይ ተከሳሹ ብር 1,100,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ.ህ) በተለያየ ጊዜ በባንክ በኩል የተረከበ ሲሆን ቀሪው ብር 400,000 (አራት መቶ ሺ.ህ) በኮሚሽንነት የሚታሰብ ሆኖ ብር 1,500,000 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ.ሕ) በብድር ተረክቦ በውሉ ላይ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ያልመለሰ ስለሆነ መመለስ ከነበረበት ቀን ጀምሮ ከ9% ወለድ ጋር ገንዘቡን ይመልስልኝ ሲል ክስ አቅርቧል፡፡

ተከሳሽ ሰኔ 4 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ በሰጠው መልስ ላይ፡- የብድር ውሉ የፍ/ብ/ህ/ቁ/1727(2) በሚያዘው መሰረት በምስክሮች ያልተረጋገጠ በመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣ ከሳሽ ብር 1,100,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ.ህ) ለተከሳሽ ገቢ አላደረጉም፣ ገቢ ተደርጎባቸዋል የተባሉት ሰነዶች ለብድሩ የተሰጡ መሆኑን አያሳዩም፣ በኮሚሲዮን ታስቦልኛል የሚሉት ብር 400,000 (አራት መቶ ሺ.ህ) ባለ አክሲዮኖች ያፀደቁት አይደለም፣ አገልግሎት ሳይሰጥም ኮሚሽን ሊሰጥ ስለማይችል ተቀባይነት የለውም፣ የብድር ውል በተባለው ላይ ወለድ እንዲከፈል ስምምነት ያልተደረገ በመሆኑ ውለድ እንዲከፈል የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በሚል ተከራክሯል፡፡

ከሳሽ ከክስ ማመልከቻቸው ጋር የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው ያቀረቡ ሲሆን ምስክሮቹንም አቅርቦ አሰምቷል፡፡

ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የሚከተሉትን አራት ጭብጦች መስርቷል፡-

1. የብድር ውሉ በተገቢው ፎርም ተደርጓልን?
2. በብድር ውሉ መሰረት ለተከሳሽ ገንዘብ ተሰጥቷልን?
3. የኮሚሽን የተባለው ለከሳሽ ሊከፈል ይገባልን?
4. ወለድ ሊከፈል ይገባልን?

**1. የብድር ውል ፎርምን በተመለከተ**

ተከሳሽ ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ/ም ብድር ውል መፈረሙን አይክድም፡፡ የተከራከረው ውሉ በሁለት ምስክሮች ያልተረጋገጠ ስለሆነ አይፀናም በሚል ነው፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1721 ውሎች የተለየ ፎርምን እንዲከተሉ ህጉ በሚያዝበት ጊዜ ወይም ተዋዋይ ወገኖች በተስማሙ ጊዜ በህጉ ላይ በተቀመጠው በስምምነቱ ፎርም መሰረት ካልተደረጉ ፋራሽ እንደሚሆኑ ይደነግጋል፡፡ የብድር ውል በተለየ ፎርም እንዲፃፍ የሚያዝ የህግ ድንጋጌ የለም፡፡ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2472 የተመለከትን እንደሆነ ብድርን ውልን ማስረዳት የሚቻለው በፁሁፍ እንደሆነ ከመደንገጉ ውጭ ውሉ በፁሁፍ መሆን አለበት የሚል ድንጋጌ አያስቀምጥም፡፡ በመሆኑም የብድር ውል በማንናቸውም የጹሁፍ አይነት ማስረዳት እንደሚቻል መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም ተዋዋይ ወገኖች ውሉ በተለየ ፎርም እንዲሆን የተስማሙ ለመሆኑ ለፍርድ ቤቱ የቀረበለት ማስረጃ የለም፡፡ ውሉን በፁሁፍ ማድረጋቸው በህጉ ላይ የተመለከተውን የፁሁፍ ፎርም ለመከተል መስማማታቸውን የሚያሳይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ/ም የተፈረመው የብድር ውል በህጉ ፊት የማይፀናበትን ምክንያት ፍርድ ቤቱ አልተመለከተም፡፡

## 2. በውሉ መሰረት ለተከሳሽ ገንዘብ ስለመሰጠቱ

ተከሳሽ በውሉ መሰረት ገንዘብ አልተቀበልኩም ሲል ተከራክሯል፡፡ ከሳሽ በባንክ በኩል ገንዘብ ገቢ ያደረኩበት ነው ሲሉ ለተከሳሽ በተለያየ ጊዜ ገንዘብ ገቢ የተደረገባቸውን የባንክ ደረሰኞችን አቅርበዋል፡፡ ገንዘቦቹ በከሳሽና በሌሎች ሰዎች ገቢ የተደረጉ መሆኑን ያሳያሉ፡፡ ከሳሽ ሁለት ምስክሮችን አቅርበው ያሰሙ ሲሆን ምስክሮቹ በግራ ቀኙ መካከል በነበረው የብድር ውል መሰረት ከሳሽ በተለያየ ጊዜ በባንክ በኩል ገንዘብ ገቢ ያደረጉ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ ተከሳሽ በበኩሉ የባንኩ ደረሰኝ ገንዘቡ ገቢ የተደረገበትን ምክንያት የማይጠቅስ ስለሆነ ገንዘቡ ገቢ የተደረገው በሌላ ምክንያት እንጂ ለብድር ውሉ አይደለም ሲል ተከራክሯል፡፡ ተከሳሽ እንዳነሳው የገንዘቡን አከፋፈል በተመለከተ ጥርጣሬን የሚጭር ሁኔታ ያለ ቢሆንም ይህ ክርክር የፍትሃብሄር በመሆኑ መረጃዎች መመዘን ያለባቸው ማን በተሻለ ሁኔታ አስረድቷል (preponderance of evidence) የሚለውን በመሆኑ፣ ከሳሽ ገንዘቡ በባንክ ስለመከፈሉ በተሻለ ያስረዱ በመሆኑ ከሳሽ ለተከሳሽ በብድር ውሉ መሰረት ብር 1,100,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺህ) አስረክበዋል የሚለው ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

## 3. የኮሚሽን ክፍያን በተመለከተ

የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2471 የብድር ውል አንድ አንድ ሰው ለሌላ ሰው ወደፊት ገንዘቡ ይመለስልኛል በሚል ገንዘብ የሚሰጥበት የውል አይነት እንደሆነ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ ውሉ ደግሞ በወለድ ወይም ያለ ወለድ በነፃ ሊሰጥ እንሚችል በህጉ የተለያዩ ክፍሎች ተቀምጧል፡፡ በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ከሳሽ ለተከሳሽ ብር 1,500,000 (አንድ ሚሊዩን አምስት መቶ ሺ.ህ) ለማበደር መስማማታቸውን ከሚገልፅ በቀር ብር 400,000 (አራት መቶ ሺ.ህ) ኮሚሽን ይከፈላቸዋል የሚል ስምምነትን አልያዘም፡፡ ይህ ክፍያ ወለድ ይሁን ወይም ሌላ ክፍያ በውሉ ላይ በግልፅ የተመለከተ አይደለም፡፡ በፍ/ብ/ህጉ ላይ በአንድ የብድር ውል ላይ ወለድ እንጂ ሌላ ክፍያ ሊፈፀም እንደሚችል በግልፅ አያስቀምጥም፡፡ ይልቅ በህጉ ላይ በግልፅ የተቀመጠው የብድር ውሉ ወለድ የሚያስከፍል ቢሆን ከ12% (አስራ ሁለት በመቶ) በላይ መብለጥ እንደሌለበት ነው፡፡ ባጠቃላይ በውሉ ላይ ወለድ ይከፈላል በሚል በግልፅ የተቀመጠ ባለመሆኑ እንዲሁም ኮምሽን የተባለው የሚከፈልበት ምክንያት የሌለ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ አልተቀበለውም፡፡

4. **የወለድ ክፍያን በተመለከተ**

ፍርድ ቤቱ በጭብጥ ሶስት ላይ ውሉ ያለ ወለድ የተደረገው የሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ሆኖም በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2489 ላይ ብድር በውሉ ላይ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ካልተመለሰ ካሳ ሊከፈል እንደሚችልና ካሳውም በህጉ ላይ የተቀመጠው የወለድ መጠን መሆኑን የሚደነግግ በመሆኑ ተከሳሽ በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 1751 ላይ የተቀመጠው የ9% (ዘጠኝ በመቶ) ወለድ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ሊከፍል ይገባል፡፡

ለማጠቃለል ተከሳሽ በብድር ውሉ ላይ የተመለከተውን ገንዘብ የተቀበለ በመሆኑ ገንዘቡን ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከነወለዱ እንዲከፍል ተፈርዶበታል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 1,100,000 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሺ.ህ) ወለድ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠበት ከ ቀን 19 ቀን ጀምሮ ዕዳው ሙሉ በሙሉ ተከፍሎ እስካበቃበት ጊዜ ድረስ 9% (ዘጠኝ በመቶ) እንዲፈከፍል ተወስኗል፡፡

ከሳሽ ወጭና ኪሳራ የመጠየቅ መብቱ ተጠብቋል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

# አባሪ 2

ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ/ም

## ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

## አዲስ አበባ

ከሣሽ ሸዋ ቆዳ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር

አድራሻ፡-ኦሮሚያ ክልል ሞጆ ከተማ

ተከሣሽ አቶ ሲሣይ ረታ አደግህልኝ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 12

## <u>በትርፍ የተከፈለ ገንዘብ ለማስመለስ የቀረበ ክስ፡፡</u>

1. ፍርድ ቤቱ ይህንን ጉዳይ ተቀብሎ የማየት ሥልጣን አለው፡፡

2. ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ብር ብር 542,128.25 (አምስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ስምንት ከሃያ አምስት ሳንቲም) ነው፡፡

3. ከሳሽ በጉዳዩ በጠበቃ አማካይነት ይከራከራል፡፡

4. ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ በህግ ችሎታ አላቸው፡፡

5. <u>የክሱ ፍሬ ነገር</u>

በከሳሽና በተከሳሽ መካከል በነበረው የንግድ ግንኙነት ተከሳሹ የተለያዩ የፍየልና የበግ ሌጦ ለከሳሽ ሲያስረክቡ የቆዩ ሲሆን በዚህ ግንኙነት ከሳሽ የፍየልና የበግ ሌጦ ዋጋ ሲከፍል ቆይቷል። ከዚህ ግንኙነታቸው በመነጨም ከሳሽ 65,521 የፍየልና 47,449 የበግ ሌጦ ለከሳሽ ለማስረከብና ከሳሽም በቀረቡለት ሌጦዎች ውጤት ደረጃው ተለይቶ የሌጠውን ዋጋ ለመክፈል በግንቦት ወር 1995 ዓ/ም ስምምነት አድርገዋል። በዚህም መሰረት የቀረቡት ሌጦዎች ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ የተመደቡ ሲሆን 1ኛና 2ኛ የሆኑት ደረጃቸውን የጠበቁ ሲሆን በ3ኛ የተመደቡት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ናቸው። ተከሳሽ ካስረከቧቸው ውስጥ፡-

- 48.07% የሚሆኑት ደረጃውን የጠበቁ የበግ ሌጦዎች
- 51.93% የሚሆኑት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የበግ ሌጦዎች
- 39.32% የሚሆኑት ደረጃቸውን የጠበቁ የፍየል ሌጦዎች
- 60.60% የሚሆኑት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የፍየል ሌጦዎች ሲሆኑ ከሳሽ ለሁሉም ሌጦዎች ብር 2,265,000 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ) ከፍሏል።

- እንዲሁም ተከሳሹ በዚሁ ፍርድ ቤት የሌጦ ሽያጭ አልተከፈለኝም በሚል በመ/ቁ/ 48876 ክስ አቅርበው ብር 542,128.25 (አምስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ስምንት ከሃያ አምስት ሳንቲም) እንዲከፈላቸው ተፈርዷል።

ከተከፈለውና ከተፈረደው ጠቅላላ ገንዘብ ብር 2,807,128.25 (ሁለት ሚሊዩን ስምንት መቶ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ስምንት ከሃያ አምስት ሳንቲም) ውስጥ 51.93% የሚሆኑት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የበግ ሌጦዎችና 60.60% የሚሆኑት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የፍየል ሌጦዎች ዋጋ ብር 542,128.25 (አምስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ስምንት ከሃያ አምስት ሳንቲም) ሊመልሱ ወይም ደረጃውን የጠበቁ ሌጦዎችን ሊያስረክቡ የሚገባ ስለሆነ ተከሳሹ ይህንን እንዲፈፅሙ እንዲወሰንልን እንዲሁም ወጭና ኪሳራችንን እንዲተኩልን ይወሰንልን።

ከዚህ በላይ የተገለፀው ነገር ሁሉ እኔ እስከማውቀው እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ከሣሽ

ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ/ም

## ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

## አዲስ አበባ

ከሣሽ    ሸዋ ቆዳ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር

አድራሻ፡-ኦሮሚያ ክልል ሞጆ ከተማ

ተከሣሽ  አቶ ሲሣይ ረታ አደግህልኝ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 12

<u>በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 223 መሠረት የቀረበ የማስረጃ ዝርዝር</u>

1. <u>የሰው ማስረጃ</u>

1.1. የቆዳ ጥራትን በተመለከተ የሚያስረዱ እንዲሁም ከሳሽ የተረከበውን ቆዳ ጥራት የሚስረዱ

1.1.1. አቶ አስረሰ ማሞ     አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15 የቤት ቁጥር 456

2. የጽሑፍ ማስረጃ

2.1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የመዝገብ ቁጥር 48876 በፍትሃብሄር ስነስርአት ህግ ቁጥር 145 መሰረት ቀርቦ እንዲታይልኝ።

የክሱ ጭብጥ ካልተለወጠ በቀር ከዚህ በላይ ከቀረበው ውጭ ሌላ አስረጅ ወይም ማስረጃ የሌለኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ከሣሽ

ጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ/ም

# ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

# አዲስ አበባ

ከሣሽ     ሸዋ ቆዳ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር

አድራሻ፡-ኦሮሚያ ክልል ሞጆ ከተማ

ተከሣሽ  አቶ ሲሣይ ረታ አደግህልኝ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 12

<u>ከሳሽ ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ/ም ላቀረበው ክስ የተሰጠ መልስ፡፡</u>

ከሳሽ ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ ላቀረበው ክስ ተከሳሽ የሚከተለውን መልስ ይሰጣል፡፡

1. የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ

1.1. ከሳሽ ለተከሳሽ ያቀረበው ቆዳ ዋጋ ባለመክፈሉ በዚሁ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48876 ክስ ቀርቦ የተወሰነ በመሆኑ ከሳሽ ክስ ሊያቀርብበት የማይችል ስለሆነ በፍትሃብሄር ስነስርአት ህግ ቁጥር 244 (2) ለ መሰረት የቀረበው ክስ ውድቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.2. ከሳሽ ያቀረበው ክስ መልስ ለመስጠት ግልፅ ስላልሆነ ውድቅ ሊደረግ ይገባዋል፡፡

1.3. ተከሳሹ ያቀረበው ክስ ከላይ በተመለከቱት ምክንቶች ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያዎችን ተቀብሎ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ/ 245 መሰረት እንዲያሰናብተን እንጠይቃለን፡፡ ፍርድ ቤቱ መቃወሚያዎችንን የማይቀበለን ቢሆን የሚከለተውን የተሟላ መልስ እንሰጣለን፡፡

2. መልስ

2.1. በግራ ቀኞችን መካከል የበግና የሌጦ በዱቤ ላይ የተመሰረተ የግብይት ውል መኖሩ የማይካድ ሲሆን ከሳሹ የሌጦዎቹን ብቁነት መርምሮ ቆዳዎቹን ተረክቧል፡፡

2.2. ከሳሹ በውሉ መሰረት የሌጦዎቹን ዋጋ ባለመክፈሉ በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 48876 ተከሶ ገንዘቡን እንዲከፍል ተፈርዶታል።

2.3. ከሳሹ ቆዳውን ከአምስት አመት በፊት በ1995 ዓ/ም የተረከበ ሲሆን በወቅቱ ጉድለት አለበት ሲል ያላስታወቀ ስለሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2291ና 2292 መሰረት ወዲያውኑ ያላሳወቀ ስለሆነ በፍ/ህ/ቁ 2293/1/ መሰረት ሻጭ ግዴታ የለበትም

2.4. ከሳሽ ለቆዳዎቹ የቅድሚያ ክፍያ ከፍሎ አያውቅም። ከሳሹ ሊከፈለኝ ይገባል የሚለውን ገንዘብም ተከሳሹ አልተቀበለም።

2.5. ከሳሹ ክስ ያቀረበው በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 48876 በተረታበትና እንዲከፍል በተወሰነበት ገንዘብ መጠን በመሆኑ ክሱ የቀረበው በክፉ ልቦና

ከዚህ በላይ የተገለፀው ነገር ሁሉ እኔ እስከማውቀው እውነት መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ተከሳሽ

ጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ/ም

## ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

## አዲስ አበባ

ከሣሽ ሸዋ ቆዳ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር

አድራሻ፡-ኦሮሚያ ክልል ሞጆ ከተማ

ተከሣሽ አቶ ሲሣይ ረታ አደግህልኝ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ፣ ቦሌ ክፍለ ከተማ፣ ቀበሌ 12

<u>በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 234 መሠረት የቀረበ የማስረጃ ዝርዝር</u>

1. <u>የሰው ማስረጃ</u>

1.1.ከሳሽ ቆዳውን መርምሮ በአግባቡ መረከቡን የሚያስረዱ

1.1.1. አቶ ሐይሉ ክፈሌ አድራሻ፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ

1.1.2. አቶ ሙደሲር ሰማን አድራሻ፡- አዲስ አበባ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ

1.1.3. አቶ ሻውል እንግዳ አድራሻ፡- አዲስ አበባ፣ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ

1.2. የቆዳ ጥራት ደረጃንና ዋጋውን በተመለከተ የሚያስረዱ ባለሙያዎች

1.2.1. ተመስገን ሃይሉ አድራሻ፡- አዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ

1.2.2. አቶ ገብረስላሴ ወልዱ አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ

የክሱ ጭብጥ ካልተለወጠ በቀር ከዚህ በላይ ከቀረበው ውጭ ሌላ አስረጅ ወይም ማስረጃ የሌለኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

የክሱ ጭብጥ ካልተለወጠ በቀር ከዚህ በላይ ከቀረበው ውጭ ሌላ አስረጅ ወይም ማስረጃ የሌለኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ተከሣሽ

ግንቦት 22 ቀን 2000 ዓ/ም

ዳኞ፡-

ከሳሽ፡- ሸዋ ቆዳ ፋብሪካ ኃ/የተ/የግል ማህበር

ጠበቃ፡- አቶ መስፍን ጌታቸው

ተከሳሽ፡- አቶ ሲሣይ ረታ አደግህልኝ

ጠበቃ፡- አቶ ገብረ እግዚአብሄር ተስፋዬ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል።

# ፍርድ

## 1. ክስ

ከሳሽ ሀምሌ 26 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ አሻሽሎ ያቀረበው ክስ ባጭሩ፡-

በከሳሽና በተከሳሽ መካከል በነበረው የንግድ ግንኙነት ተከሳሹ የተለያዩ የፍየልና የበግ ሌጦ ለከሳሽ ሲያስረክቡ የቆዩ ሲሆን በዚህ ግንኙነት ከሳሽ የፍየልና የበግ ሌጦ ዋጋ ሲከፍል

ቆይቷል። ከዚህ ግንኙነታቸው በመነጨም ከሳሽ 65,521 የፍየልና 47,449 የበግ ሌጦ ለከሳሽ ለማስረከብና ከሳሽም በቀረቡለት ሌጦዎች ውጤት ደረጃው ተለይቶ የሌጦውን ዋጋ ለመክፈል በግንቦት ወር 1995 ዓ/ም ስምምነት አድርገዋል። በዚህም መሰረት የቀረቡት ሌጦዎች ከ1ኛ-3ኛ ደረጃ የተመደቡ ሲሆን 1ኛና 2ኛ የሆኑት ደረጃቸውን የጠበቁ ሲሆን በ3ኛ የተመደቡት ደረጃቸውን ያልጠበቁ ናቸው። ተከሳሽ ካስረከቧቸው ውስጥ፡-

- 48.07% የሚሆኑት ደረጃውን የጠበቁ የበግ ሌጦዎች
- 51.93% የሚሆኑት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የበግ ሌጦዎች
- 39.32% የሚሆኑት ደረጃቸውን የጠበቁ የፍየል ሌጦዎች
- 60.60% የሚሆኑት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የፍየል ሌጦዎች ሲሆኑ ከሳሽ ለሁሉም ሌጦዎች ብር 2,265,000 (ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ አምስት ሺህ) ከፍሏል።
- እንዲሁም ተከሳሹ በዚሁ ፍርድ ቤት የሌጦ ሽያጭ አልተከፈለኝም በሚል በመ/ቁ/ 48876 ክስ አቅርበው ብር 542,128.25 (አምስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ስምንት ከሃያ አምስት ሳንቲም) እንዲከፈላቸው ተፈርዷል።

ከተከፈለውና ከተፈረደው ጠቅላላ ገንዘብ ብር 2,807,128.25 (ሁለት ሚሊዩን ስምንት መቶ ሰባት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ስምንት ከሃያ አምስት ሳንቲም) ውስጥ 51.93% የሚሆኑት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የበግ ሌጦዎችና 60.60% የሚሆኑት ደረጃቸውን ያልጠበቁ የፍየል ሌጦዎች ዋጋ ብር 542,128.25 (አምስት መቶ አርባ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ሃያ ስምንት ከሃያ አምስት ሳንቲም) ሊመልሱ ወይም ደረጃውን የጠበቁ ሌጦዎችን ሊያስረክቡ የሚገባ ስለሆነ ተከሳሹ ይህንን እንዲፈፅሙ ይወሰንልን የሚል ነው።

## 2. <u>መልስ</u>

ተከሳሹ ጥቅምት 7 ቀን 2000 ዓ/ም በተፃፈ የሰጡት መልስ ባጭሩ፡-

- በግራ ቀኛችን መካከል የበግና የሌጦ በጹቤ ላይ የተመሰረተ የግብይት ውል መኖሩ የማይካድ ሲሆን ከሳሹ የሌጦዎቹን ብቁነት መርምሮ ቆዳዎቹን ተረክቧል።
- ከሳሹ በውሉ መሰረት የሌጦዎቹን ዋጋ ባለመክፈሉ በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 48876 ተከሶ ገንዘቡን እንዲከፍል ተፈርዶታል።

- ከሳሹ ቆዳውን ከአምስት አመት በፊት በ1995 ዓ/ም የተረከበ ሲሆን በወቅቱ ጉድለት አለበት ሲል ያላስታወቀ ስለሆነ በፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2291ና 2292 መሰረት ወዲያውኑ ያላሳወቀ ስለሆነ በፍ/ህ/ቁ 2293/1/ መሰረት ሻጭ ግዴታ የለበትም
- ከሳሽ ለቆዳዎቹ የቅድሚያ ክፍያ ከፍሎ አያውቅም። ከሳሹ ሊከፈለኝ ይገባል የሚለውን ገንዘብም ተከሳሹ አልተቀበለም።
- ከሳሹ ክስ ያቀረበው በዚሁ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 48876 በተረታበትና እንዲከፍል በተወሰነበት ገንዘብ መጠን በመሆኑ ክሱ የቀረበው በክፉ ልቦና ነው የሚል ነው።

## 3. የግራ ቀኙ ማስረጃዎች

ከሳሽ አንድ ምስክር አቅርቦ ያሰማ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የመ/ቁ/ 48876 እንዲታይለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በበኩላቸው 5 ምስክሮችን ያሰሙ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የመ/ቁ/ 48876 እንዲታይላቸው ጠይቀዋል፡፡

## 4. ጭብጥ

ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ፍርድ ቤቱ ሁለት ጭብጦችን የመሰረተ ሲሆን እነሱም፡-

1. የቆዳ ዋጋ የሚወሰነው ከሳሹ ቆዳውን ከተረከበ በሃላ ደረጃውን መድቦ ነውን ወይስ ቀደም ብሎ ደረጃውን መድቦ የሚረከብበትን ዋጋ ወስኖ ነውን?
2. ደረጃው የሚወሰነው ከርክክብ በሃላ ነው የሚባል ቢሆን ከሳሹ እላፊ ገንዘብ ከፍሏልን? ምን ያህልስ ከፍሏልን? የሚሉ ናቸው

## 5. የቆዳ ዋጋን በተመለከተ

ከሳሽ አቅርበው ያሰሟቸው ምስክር የከሳሽ ድርጅት ሰራተኛ ሲሆኑ በግራ ቀኙ መካከል የፍየልና የበግ ሌጦ አቅርቦት የንግድ ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ከሳሹ ሌጦዎችን ተረክቦ በፋብሪካው በማየት ደረጃ አይቶ ክፍያ እንደሚፈጽም ከሳሽ ካቀረቧቸው ሌጦዎች መካከል ከደረጃቸው የወረዱ እንደነበርና ከዚህ ውስጥ እላፊ ክፍያ መፈፀሙን አስረድተዋል፡፡ ሆኖም ምን ያህል እላፊ ክፍያ እንደተፈጸመ ማስረዳት አልቻሉም፡፡

ተከሳሽ አቅርበው ያሰሟቸው አምስት ምስክሮች ከፊሎቹ በተከሳሹ ድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ሲሆን ሌሎቹ በከሳሽ ድርጅት ውስጥ እየሰሩ ያሉ ወይም የሰሩ ሲሆኑ የሌጦ ዋጋ የሚወሰነው ቀደም ብሎ ተከሳሹ ቆዳውን ከመረከቡ በፊት በደረጃ ተከፋፍሎ መሆኑን፣ ከሳሹ ቆዳ ከተረከበ በሃላ ዋጋ እንደማይወጣለት በዚህ አሰራርም ደረጃቸውን የጠበቁ ቆዳዎችን የከሳሹ ሰራተኞች በተከሳሽ መጋዘን በመገኘት መርጦ ዋጋ እየተተመነላቸው መረከቡን፣ የበግ ሌጦ ከደረጃ 1-3 ያሉት ብር 34 እንዲሁም የፍየል ሌጦ ከደረጃ 1-3 ያሉት ብር 18.50 እርጥቡ ብር 17.50 ደረቁ በሆነ ዋጋ የተረከበ መሆኑን፣ ከሳሹ ቆዳዎችን የሚረከበው በዱቤ መሆኑን ከሞላ ጎደል በተመሳሳይ ቃል አስረድተዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች የመዘነ ሲሆን ተከሳሽ አቅርበው ያሰሟቸው ምስክሮች በከሳሽና በተከሳሽ መካከል የነበረውን የውል ግንኙነት፣ የዋጋ አወሳሰኑን እንዲሁም የቆዳ ንግድ ስራ ልምድን በተመለከተ ለፍርድ ቤቱ አሳማኝ በሆኑ መንገድ አስረድተዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር የምስክሮቹ ተዋፅኦ ከግራ ቀኙ መ/ቤቶች የተውጣጡ፣ በቆዳ ስራ ላይም ቆየት ያለ ልምድ ያላቸው ከመሆኑ አንፃር የምስክርነት ቃላቸውን አሳማኝ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በሌላ በኩል የከሳሹ ብቸኛ ምስክር የመ/ቤቱ ሰራተኛ ሲሆኑ የቆዳ ዋጋ አወሳሰንን በተመለከተ ፍርድ ቤቱን ሊያሳምን በሚችል መልኩ ለማስረዳት አልቻሉም፡፡

ባጠቃላይ ከሳሹ ከተከሳሹ ቆዳዎቹን በደረጃ ደረጃ ከፋፍሎና መርጦ እንዲሁም ዋጋውን ቀደም ብሎ የተረከበ መሆኑ ተከሳሹ ካቀረቧቸው ማስረጃዎች የተረጋገጠ በመሆኑ የስምምነቱን ዋጋ ሊከፍል የሚገባ በመሆኑ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛውን ጭብጥ መመልከት አላስፈለገለም፡፡

ከሳሹ ያቀረበው ክስ ተቀባይነት የለውም ተብሎ ተፈዷል፡፡

ተከሳሹ ወጭና ኪሳራ የመጠየቅ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

መዝገቡ የተዘጋ ስለሆነ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

# አባሪ 3

ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ/ም

## ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

## አዲስ አበባ

ከሣሽ     አቶ ባዩ በላይነህ ዘወልደማርያም አድራሻ፦ አዲስ አበባ

ተከሣሽ  አቶ ሰለሞን ጥላሁን አድራሻ፦ አሜሪካን አገር፣ ሲያትል

የጋራ እዳን ለማስቀነስ የቀረበ ክስ፡፡

2. ፍርድ ቤቱ ይህንን ጉዳይ ተቀብሎ የማየት ሥልጣን አለው፡፡

3. ክስ የቀረበበት የገንዘብ መጠን ብር 575,000 (አምስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ) ነው፡፡

4. ከሳሽ በጉዳዩ በጠበቃ አማካይነት ይከራከራል፡፡

5. ከሳሽም ሆነ ተከሳሽ በህግ ችሎታ አላቸው፡፡

6. **የክሱ ፍሬነገር**

ከሳሽና ተከሳሽ መስከረም 21 ቀን 1985 ዓ/ም በተደረገ የንግድ ስራዎች የሽርክና ውል የአግሮ እንዱስትሪ ልዩ ልዩ የንግድ ስራዎችን ለማካሄድና በመቋቋም ላይ ከሚገኘው ከትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበር አክስዮን ገዝተን ከማህበሩ የሚገኘውን ጥቅም እኩል በጋራ ለመካፈል እዳም ቢኖር በጋራ ለመክፈል ተስማምተናል። ተከሳሽ ከኢትዮጵያ ውጪ ነዋሪ በመሆናቸውና በአገር ውስጥ ያለውን የስራ እንቅስቃሴ መቆጣጠር ስለማይችሉ መስከረም 21 ቀን 1985 ዓ/ም የተደረገውን የሽርክና ውል ቁጥር 4ና 8ን ማሻሻል አስፈላጊ ነበር። በዚህም መሰረት ተከሳሹ ውክልና በሰጧቸው አቶ ተሰማ ደምሴ በተባሉ ግለሰብ አማካይነት የትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህር አክስዮን በተከሳሽ ስም እንዲሆን ጥቅምት 10 ቀን 1987 ዓ/ም ተዋውለናል። በዚህም መሰረት በአክሲዮን ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ፈርሜያለሁ እንዲሁም ቁጥር 002 የሆነ አክሲዮን ተሰጥቶኛል። ለአክሲዮን ማህበሩም አክሲዮን ከተከሳሽ ጋር የጋራ መሆኑን አሳውቄያለሁ። ትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበር ለስራው ለሚያስገልገው ብድር በብድር ውሉ ላይ እንድፈርምና ተከሳሽም ብድሩ የሚያስከትለውን ባለዕዳነት በሙሉ ሃላፊነት እንደሚቀበሉት በመግለፅ በፋክስ አሳውቀውኛል። በዚህም መሰረት ማህበሩ ከልማት ባንክ ለወሰደው ብድር ፈርሚያለሁ። ትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበር ከባንኩ የወሰደው ብድር ብር 15,144,543.26 (አስራ አምስት ሚሊዮን አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ አምስት መቶ አርባ ሶስት ከሃያ ስድስት ሳንቲም) ለመክፈል ባለመቻሉ በፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 21924 ተከሶ ከሚያዚያ 23 ቀን 1995 ዓ/ም ከሚታሰብ ወለድ ጋር የፈርሚያለሁ። ትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበር ባለአክሲዮኖች እንድንከፍል ተፈርዶብናል። በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት የከሳሽና የተከሳሽ እዳ ብር 1,150,000.00 (አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ

ሃምሳ ሺ.ህ) ሊ.ዘ.ህም ዕዳ በላፍቶ ክ/ከተማ ቀበሌ 04 የቤት ቁጥሩ 409 የሆነ ቤቱ በመያዣነት ተይዟል። ከዕዳው ላይ የተከሳሹ ድርሻ ብር 575,000 (አምስት መቶ ሰባ አምስት ሺ.ህ) ነው። በመሆኑም ተከሳሹ ድርሻቸውን ከሚያዚያ 23 ቀን 1995 ዓ/ም ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው።

ታህሳስ 24 ቀን 2000 ዓ/ም

## ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት

## አዲስ አበባ

ከሣሽ    አቶ ባዩ በላይነህ ዘወልደማርያም አድራሻ፡- አዲስ አበባ

ተከሣሽ  አቶ ሰለሞን ጥላሁን አድራሻ፡- አሜሪካን አገር፣ ሲያትል

<u>ከሳሽ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ/ም ላቀረበው ክስ የተሰጠ መልስ፡፡</u>

ከሳሽ ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ ላቀረበው ክስ ተከሳሽ የሚከተለውን መልስ ይሰጣል፡፡

1. ከከሳሽ የተደረጉት ውሎች በተንኮል የተደረጉ ስለሆነ ጉድለት ያለባቸው ናቸው
2. ተከሳሽ ለከሳሽ መስከረም 18 ቀን 1985 ዓ/ም የሰጡት የውክልና ስልጣን እንዲሁም መስከረም 21 ቀን 1985 ዓ/ም የተደረገው የሽርክና ውል ከሳሽ በተከሳሹ ስም አክሲዮን እንዲገዙ፣ የአክሲዮን የምስክር ወረቀት በእያንዳንዳቸው ስም እንዲጻፍ፣ መብታቸው እኩል እንዲጠበቅ፣ በስማቸው የሚከፈለው ገንዘብ ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) እንዲከፈል የነበረ ሲሆን ተከሳሹ ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) ወዲያውኑ ከፍለዋል ሆኖም ከሳሹ በተከሳሹ ስም አክሲዮን አልገዙም፣ ስማቸውንም አላስመዘገቡም፣ ማረጋገጫውም የተሰጠው በከሳሹ ስም ነው። በመሆኑም ውሉ ተንኮል ያለበት ነው፡
3. አቶ ተሰማ ደምሴ ለዚህ ጉዳይ ውክልና ሳይኖራቸው አስፈርመዋቸዋል
4. ተከሳሹ ስለ ውሉ መሻሻል የሚያውቁት የለም፣ ስለሆነም ውሉ በተንኮል የተዘጋጀ ነው
5. ተከሳሹ ስለ እኔ ሆነህ ለምትፈርመው ብድር ሙሉ ሃላፊነቱን እወስዳለሁ በማለት መፃፋቸውን አይክዱም ሆኖም በተከሳሽ ስም ብድር አልተወሰደም
6. ተከሳሹ የጋራ ባለዕዳ ናቸው የሚባል ቢሆን ከሳሽ አያይዘው ያቀረቡት የፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚሳያው ለብድሩ ተጠያቂዎች 21 ሰዎች ሲሆኑ ተጠያቂነታቸው በአንድነት ስለሆነ የከሳሹ እዳ ብር 721,168 (ሰባት መቶ ሃያ አንድ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ) በመሆኑ የተከሳሹ ድርሻ ብር 360,584 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ አራት ሳንቲም)። በመሆኑም ፍርድ ቤቱ ከቀረበብን ክስ በነፃ እንዲያሰናብተን እንጠይቃለን።

ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ/ም

ዳኛ፡-

ከሳሽ፡- አቶ ባዩ በላይነህ ዘወልደማርያም

ጠበቃ፡- አቶ

ተከሳሽ፡- አቶ ሰለሞን ጥላሁን

ጠበቃ፡-

ፍርድ ቤቱ መዝገቡን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

# ፍርድ

## 1. ክስ

ከሳሽ ግንቦት 21 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- ከሳሽና ተከሳሽ መስከረም 21 ቀን 1985 ዓ/ም በተደረገ የንግድ ስራዎች የሽርክና ውል የአግሮ እንዱስትሪ ልዩ ልዩ የንግድ ስራዎችን ለማካሄድና በመቋቋም ላይ ከሚገኘው ከትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዩን ማህበር አክስዩን ገዝተን ከማህበሩ የሚገኘውን ጥቅም እኩል በጋራ ለመካፈል እዳም ቢኖር በጋራ ለመክፈል ተስማምተናል፡፡ ተከሳሽ ከኢትዮጵያ ውጪ ነዋሪ በመሆናቸውና በአገር ውስጥ ያለውን የስራ እንቅስቃሴ መቆጣጠር ስለማይችሉ መስከረም 21 ቀን 1985 ዓ/ም የተደረገውን የሽርክና ውል ቁጥር 4ና 8ን ማሻሻል አስፈላጊ ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ተከሳሹ ውክልና በሰጧቸው አቶ ተሰማ ደምሴ በተባሉ ግለሰብ አማካይነት የትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዩን ማህር አክስዩን በተከሳሽ ስም እንዲሆን ጥቅምት 10 ቀን 1987 ዓ/ም ተዋውለናል፡፡ በዚህም መሰረት በአክሲዩን ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ፈርሜያለሁ እንዲሁም ቁጥር 002 የሆነ አክሲዩን ተሰጥቶኛል፡፡ ለአክሲዩን ማህበሩም አክሲዩን ከተከሳሽ ጋር የጋራ መሆኑን አሳውቄያለሁ፡፡ ትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዩን ማህበር ለስራው ለሚያስገልገው ብድር በብድር ውሉ ላይ እንድፈርምና ተከሳሽም ብድሩ የሚያስከትለውን ባለዕዳነት በሙሉ ሃላፊነት እንደሚቀበሉት በመግለፅ በፋክስ አሳውቀውኛል፡፡ በዚህም መሰረት ማህበሩ ከልማት ባንክ ለወሰደው ብድር ፈርሚያለሁ፡

፡ ትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበር ከባንኩ የወሰደው ብድር ብር 15,144,543.26 (አስራ አምስት ሚሊዩን አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ አምስት መቶ አርባ ሶስት ከሃያ ስድስት ሳንቲም) ለመክፈል ባለመቻሉ በፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 21924 ተከሶ ከሚያዚያ 23 ቀን 1995 ዓ/ም ከሚታሰብ ወለድ ጋር የፈርሚያለሁ። ትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበር ባለአክሲዩኖች እንድንከፍል ተፈርዶብናል። በፍርድ ቤቱ ውሳኔ መሰረት የከሳሽና የተከሳሽ እዳ ብር 1,150,000.00 (አንድ ሚሊዩን አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ) ሊዚህም ዕዳ በላፍቶ ክ/ከተማ ቀበሌ 04 የቤት ቁጥሩ 409 የሆነ ቤቴ በመያዣነት ተይዟል። ከዕዳው ላይ የተከሳሹ ድርሻ ብር 575,000 (አምስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ) ነው። በመሆኑም ተከሳሹ ድርሻቸውን ከሚያዚያ 23 ቀን 1995 ዓ/ም ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ የሚል ነው።

ከሳሽ ከክስ ማመልከቻቸው ጋር የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው አቅርበዋል። በሙግቱም ምስክሮችም አቅርበው አሰምተዋል።

## 2. መልስ

ተከሳሽ ታህሳስ 24 ቀን 2000 ዓ/ም በተፃፈ የሰጡት መልስ ይዘት ባጭሩ፡-

- ከከሳሽ የተደረጉት ውሎች በተንኮል የተደረጉ ስለሆነ ጉድለት ያለባቸው ናቸው
- ተከሳሽ ለከሳሽ መስከረም 18 ቀን 1985 ዓ/ም የሰጡት የውክልና ስልጣን እንዲሁም መስከረም 21 ቀን 1985 ዓ/ም የተደረገው የሽርክና ውል ከሳሽ በተከሳሹ ስም አክሲዩን እንዲገዙ፣ የአክሲዩን የምስክር ወረቀት በእያንዳንዳቸው ስም እንዲጻፍ፣ መብታቸው እኩል እንዲጠበቅ፣ በስማቸው የሚከፈለው ገንዘብ ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) እንዲከፈል የነበረ ሲሆን ተከሳሹ ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) ወዲያውኑ ከፍለዋል ሆኖም ከሳሹ በተከሳሹ ስም አክሲዩን አልገዙም፣ ስማቸውንም አላስመዘገቡም፣ ማረጋገጫውም የተሰጠው በከሳሹ ስም ነው። በመሆኑም ውሉ ተንኮል ያለበት ነው፡
- አቶ ተሰማ ደምሴ ለዚህ ጉዳይ ውክልና ሳይኖራቸው አስፈርመዋቸዋል
- ተከሳሹ ስለ ውሉ መሻሻል የሚያውቁት የለም፣ ስለሆነም ውሉ በተንኮል የተዘጋጀ ነው
- ተከሳሹ ስለ እኔ ሆነህ ለምትፈርመው ብድር ሙሉ ሃላፊነቱን እወስዳለሁ በማለት መፃፋቸውን አይክዱም ሆኖም በተከሳሽ ስም ብድር አልተወሰደም
- ተከሳሹ የጋራ ባለዕዳ ናቸው የሚባል ቢሆን ከሳሽ አያይዘው ያቀረቡት የፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሚሳየው ለብድሩ ተጠያቂዎች 21 ሰዎች ሲሆኑ ተጠያቂነታቸው በአንድነት ስለሆነ የከሳሹ እዳ ብር 721,168 (ሰባት መቶ ሃያ አንድ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ስምንት ሺህ) በመሆኑ

የተከሳሹ ድርሻ ብር 360,584 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ አራት ሳንቲም) ብቻ ነው የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ከመልሳቸው ጋር የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው አቅርበዋል፡፡ በሙግቱም ምስክሮችን አቅርበው አሰምተዋል፡፡

## 3. ጭብጥ

ፍርድ ቤቱ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት የሚከተሉትን ሁለት ጭብጦች መስርቷል፡-

1. ተከሳሽ ከሳሽ ለገቡት ግዴታ በጋራ ሃላፊነት አለባቸውን?
2. ሃላፊነት አለባቸው የሚባል ቢሆን ከከሳሽ ጋር በጋራ ሊከፍሉት የሚገባ ዕዳ ምን ያህል ነው? ድርሻቸውስ ምን ያህን ነው? የሚል ነው፡፡

## 3.1. የተከሳሹን ሃላፊነት በተመለከተ

በግራ ቀኙ መካከል መስከረም 21 ቀን 2000 ዓ/ም የተፈረመ የሽርክና ውል ስለመኖሩ ግራ ቀኙ አይካካዱም፡፡ ተከሳሹ አጥብቀው የሚከራከሩት ከሳሽ "ከትዊንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበር" በስማቸውን የገዟቸውን አክሲዮኖች በስሜ እንዲያዛውሩ ተስማምተን እያለ ከሳሹ አክሲዮኖቹን በሙሉ በስማቸው ይዘዋል፣ በስሜም ያላዛወሩ ስለሆነ ተንኮል ተፈጽሞብኛል በመሆኑም ከሳሹ ገባሁ የሚሉት ግዴታ የሚመለከተኝ አይደለም በሚል ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል የሽርክና ውል ከመደረጉ በፊት ተከሳሽ መስከረም 18 ቀን 1985 ዓ/ም በስማቸው የንግድ ማህበራትን እንዲያቋቁሙ፣ አክሲዮን እንዲገዙ፣ በማህበራት ስብሰባዎች ላይ እንዲገኙ፣ ወዘተ ለከሳሽ የውክልና ስልጣን ሰጥተዋል፡፡ ይህም በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ እንዲሁም በግራ ቀኙ መካከል የተፈረመ የሽርክና ውል በተለየ ሁኔታ በወቅቱ በመቋቋም ላይ ስለነበረው ትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበር የሚገልፅ ሲሆን ከሳሽ ቀደም ብለው የማህበሩን 500 አክሲዮን መግዛታቸውንና እነዚህን አክሲዮኖች ግራ ቀኙ ባደረጉት የመዋጮ ስምምነት እኩል መካፈላቸውን የሚያሳይ ሲሆን ይህንን ተከትሎ አክሲዮን ማህበሩን በተመለከተ በሁለቱም መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገዛ ነው፡፡ በዚህ መሰረት አክሲዮኖቹ በሁለቱም ስም ተለያይቶ ተፅፎ እንዲሰጣቸው በአንቀፅ 4 ላይ ተስማምተዋል፡፡

ሆኖም በ1987 ዓ/ም ሌላ ማሻሻያ ውል ተደርጓል የተባለ ሲሆን በዚህ ውል መሰረት አንቀፅ 4 ተሻሽሎ አክሲዮኖቹ በከሳሹ ስም ተመዝግበው እንዲቆዩ ሆኖም በውስጥ የሽርክና ውል መሰረት በእኩል ድርሻ

የጋራ እንዲሆን የተስማሙ መሆኑን ያሳያል፡፡ ተከሳሹ ለሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ውል አላውቀውም፣ ውክልና ባልሰጠኋቸው ሰውም የተፈረመና በተንኮልም የተደረገ ነው ባይ ናቸው፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከሳሹ አቶ ተሰማ ደምሴ ለተባሉ ግለሰብ መስከረም 14 ቀን 1985 ዓ/ም በተፃፈ የሰጡትን ውክልና ተመልክቶታል፡፡ ውክልናው ግለሰቡ ትዌንቲ ትዌንቲ ዲቨሎፐርስ አክሲዮን ማህበርን በተመለከተ በተለየ ሁኔታ እንዲፈርሙ ውክልና የተሰጣቸው መሆኑን አያመለክትም፡፡ ሆኖም የውክልናው ቁጥር 8 "በጠቅላላው እኔን በማናቸውም ጉዳይ እንዲወክሉኝ፣ ማናቸውም አስፈላጊ ነገሮች ሁሉ እኔን መስለውና በእኔ ስም በማናቸውም ስፍራ በኢትዮጵያ ውስጥ ለማነጋገር ጉዳዮችን ለማስፈፀም…" ጠቅላላ ውክልና የተሰጣቸው መሆኑን ያሳያል፡፡ ወኪሉም በምስክርነት ቀርበው ተከሳሹ ከሳሹ የሚያስፈርምህ ወረቀት ስላለ ፈርምለት ስላሉኝ ፈርሚለታለሁ ሲሉ ለፍርድ ቤቱ አስረድተዋል፡፡

በ1995 ዓ/ም ከሳሽ ለተከሳሽ በላኩላቸው የፍክስ መልዕክት መሰረት ተከሳሹ በፋክስ ያስተላለፉት መልዕክት "…በድጋሚ የላከው ፋክስ በትክክል ደርሰዋል፡፡ በእኔ በኩል ለብድሩ በተርፍም ጥሩ ነው ብዩ አምናለሁ፡፡ ስለ እኔ ሆነህም ለምትፈርመው ሙሉ ሃላፊነቱን እንደምወስድና እንደምቀበል በዚህ ማስታወሻ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ…" የሚል ነው፡፡ የማሻሻያ ውሉ የተፈረመው በ1987 ዓ/ም ሲሆን ተከሳሹ ይህንን መልዕክት ያስተላለፉት ከ8 ዓመት በሃላ በ1995 ዓ/ም ነው፡፡ ተከሳሹ በዚህ ጊዜ ውስጥ አክሲዮኖቹ በስማቸው አለመመዝገባቸውን ወይም በ1987 ዓ/ም የተደረገውን ውል አያውቁም ነበር ለማለት የሚያስቸግር ነው፡፡ በዚህ ግዜ ውስጥ ተከሳሹ አክሲዮኖቹ በስማቸው ባለመመዝገቡ ቅሬታ ስለማቅረባቸው የሚያመላክቱ ማስረጃዎችን አላቀረቡም፡፡ ይልቁንም ከሳሽ በማስረጃነት ያቀረቡት የፍክስ መልእክት የ1987 ስምምነት በትክክል መፈጸሙን የሚያሳይ ነው፡፡ በተከሳሹ ጠቅላላ ውክልና የተሰጣቸውም ግለሰብ በተከሳሹ ትዕዛዝ መሰረት ውሉ ላይ መፈረማቸውን አስረድተዋል፡፡ ይህም ተከሳሹ ስምምነቱን መቀበላቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም ተከሳሹ ተንኮል ተፈፅሞብኝ ነበር የሚሉትን አሳማኝ በሆነ ማስረጃ ለማስረዳት አልቻሉም፡፡ ፍርድ ቤቱ ጭብጡን ተከሳሹ ከሳሹ ለገቡት ግዴታ የጋራ ሃላፊነት አለባቸው የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡

## 3.2. የሃላፊነት መጠንን በተመለከተ

የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ/ 21924 በ21 ሰዎች ላይ ውሳኔ የሰጠው ብር 15,144,543.26 (አስራ አምስት ሚሊዩን አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ አምስት መቶ አርባ ሶስት ከሃያ ስድስት ሳንቲም) በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ነው፡፡ ብዛታቸው ከሁለት በላይ የሆኑ ባለእዳዎች ግዴታ የአንድነትና በነጠላ በሆነ ግዜ የእያንዳንዱ የእዳ ድርሻ እኩል ነው ተብሎ ይገመታል (የፍ/ህ/ቁ/ 1907)፡፡ በመሆኑም ፍርድ ቤቱ በሰጠው ውሳኔ መሰረት የከሳሹ ድርሻ ብር 721,168.73 (ሰባት መቶ ሃያ አንድ ሺህ አንድ መቶ ስልሳ ስምንት ከሰባ ሶስት ሳንቲም) በመሆኑ የተከሳሹ ድርሻ ብር 360,584.36 (ሶስት መቶ ስልሳ ሺህ አምስት መቶ ሰማንያ አራት ከሰላሳ ስድስት ሳንቲም) ነው፡፡

## ውሳኔ

ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 360,584.36 ወለድ ከሚያዚያ 23 ቀን 1995 ዓ/ም ጀምሮ 9% እንዲከፍሉ ተወስኗል፡፡

ከሳሽ ወጭና ኪሳራ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

# አባሪ 4

## ክስ

ከሳሽ ሰኔ 5 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- ተከሳሹ ፒተር ወርቅ ደስት የሚል ድርጅትና ያላቸውና የወርቅ ነጋዴ መሆናቸውን ገልጸውልኝ ከጥቅምት 18 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ በኢሚል ስለ ወርቅ ሽያጭ ግንኙነት ያደረግን ሲሆን እኔ እዚህ አዲስ አበባ ድረስ በአካል መጥቼ እንዲሁም ልጄ ኢንጂነር መሀመድ ኢል ሁሴን አብደል ጋዋድ ወደ አዲስ አበባ ልኬው ግንኙነት እንዲያደርግና ናሙና እንዲልክ አድርጌያለሁ፡፡ ተከሳሹ የግዥ ስምምነትና ክፍያ በኤሊሲ ወይም በካሽ ሊደረግ እንደሚችል፣ የውጭ ምንዛሪም ከውጭ ይገቬ መምጣት የምችል መሆኑን ገልጾልኝ በመጨረሻ፡-

- ግንቦት 20 ቀን 1999 ዓ/ም አዲስ አበባ የገባሁ ሲሆን በማግስቱ ከተከሳሹና ምክትሌ ነው ካሉን ከአቶ መንገሻ ጋር የተገናኘን ሲሆን በማግስቱ የግዥ ስምምነቱን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ ሰነዶችን እንዲያዘጋጁ ስምምነት ላይ የደረሰን ሲሆን
- ተከሳሹ ግንቦት 23 ቀን 1999 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ወስደውኝ በማጠራቀሚያ ሳጥኖች ውስጥ የተቀመጡ ወርቆችን አሳይተውኛል፡፡
- ግንቦት 23 ቀን 1999 ዓ/ም ተከሳሹና ምክትሌ የሚሏቸው ▪አቶ መንገሻ ከምሽቱ 12፡30 ላይ ያረፍኩበት ኢማድ ፈርኒሽድ አፓርትመንት መጥተው ሰነዶቹ የተዘጋጁ መሆኑንና ሰነዶቹን የሚያሳዩኝ ክፍያ ስፈፅም ብቻ እንደሆነ ገልፀውልኝ ሆኖም ቆይተው ከለሌቱ 6 ሰዓት መጥተው ሰነዱን እንዳልያዙ ነግረውኝ በነጋታው ጠዋት እንደሚያመጡ ነገሩኝ
- ግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ/ም ከጠዋቱ 1፡30 እኔጋ መጥተው ሰነዱን ከመስጠታቸው በፊት ገንዘቡን መቁጠር እንደሚፈልጉ ነግረውኝ ኢማድ ፈርኒሽድ አፓርትመንት ድረስ

ሄደን የአሜሪካን ዶላር 179,000 (አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ) ወስደዋል፡፡ በወቅቱ ሁለት ሰነድ ብቻ ያቀረቡ ሲሆን ሌሎቹን ሰነዶች ኤርፖርት 2፡30 ላይ እንደሚያመጡ ተስማምተው ተለያየን፡፡ ተከሳሹ ኤርፖርት ሳይመጡ ቀሩ በረራውም ተሰረዘ፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ስልክ ደውለው ስህተቱ የሳቸው መሆኑን በማመን ሰነዶቹን በበረራ ሰአት ከምሽቱ 4፡30 ላይ እንደሚያመጡ ነገሩን፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ባለመምጣታቸው ከኤርፖርት ወጣን፡፡

- የተከሳሹ ምክትል ናቸው የተባሉት ግለሰብ ግንቦት 25 ቀን 1999 ዓ/ም 4፡30 ላይ ቀጠሮ የሰጡን ቢሆኑም ተከሳሹ ሊገኙ አልቻሉም፡፡

በመሆኑም ተከሳሹ የሚሸጥ ወርቅ አለ በሚል አላግባብ ለመበልጸግ የወሰዱትን የአሜሪካን ዶላር 179,000 (አንድ መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺህ) ወይም ክሱ በቀረበት ጊዜ በነበረው ምንዛሬ ብር 1,598,470.00 (አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አራት መቶ ሰባ) ከግንቦት 24 ቀን 1999 ዓ/ም ከሚታሰብ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

## መልስ

ተከሳሽ ከክስ ማመልከቻቸው ጋር የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው አቅርበዋል፡፡

ተከሳሹ ሰኔ 25 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ የሰጡት መልስ ባጭሩ፡-

- ተከሳሽ የወርቅ ኤክስፖርት ንግድ ፈቃድ ያለኝ ቢሆንም ፒተር ወርቅ ደስት የሚባል ኩባንያ የለኝም
- ከከሳሻ ጋር ወርቅ የመሸጥ ውል አላደረግኩም በኢሜልም ግንኙነት አላደረግኩም፣ ናሙናዎችም አላሳየሁም፣ ገንዘብ አልተቀበልኩም
- ከሳሽ በክስ ማመልከቻቸው ላይ የጠቀሱት የወርቅ ግብይት ስርአት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ የጣሱ ህገ ወጥ ድርጊቶች ናቸው
- የቀረበው ክስ በአላግባብ መበልጸግ ድንጋጌ ውስጥ የሚወድቅ አይደለም
- ከሳሽ ያቀረቡት ክስ በሀሰት የቀረበ ነው የሚል ነው፡፡

# አባሪ 5

ከሳሽ ሰኔ 28 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- ከሳሽና ወ/ሮ ሰልማ ድረስ ሳሌም (ታረቀኝ ተክሉ) በባልና ሚስትነት ተጋብተን ለረጅም ጊዜ አብረን የኖርን ሲሆን ቀደም ሲል የጋብቻ ውል ስላልነበረን በኩዌት መንግስት በኢትዮጵያ አቆጣጠር ነሀሴ 24 ቀን 1984 ዓ/ም የተፃፈ ቁጥር 1333 የሆነ የጋብቻ ማስረጃ ተሰጥቶናል። እንዲሁም በሃይማኖታችን መሰረት ከሸሪዓ ፍርድ ቤት ነሀሴ 29 ቀን 1983 ዓ/ም ባልና ሚስት መሆናቸውን ተረጋግጧል። ይህ በእንዲህ እንዳለ በጋብቻ ላይ እያለን በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 04/06/07 የቤት ቁጥሩ 459 የሆነ መኖሪያ ቤት በጋር የሰራን ሲሆን ባለቤቴ ባደረባት ህመም ከዚህ አለም በሞት የተለየች ስለሆነ ይህ ቤት በተከሳሹ አላግባብ የተያዘ ስለሆነና ለማካፈልም ፈቃደኛ ስላልሆነ ቤቱን እንዲያካፍለኝ ወይም የቤቱ ግምት ብር 6,000,000 (ስድስት ሚሊዩን) ስለሆነ ግማሹ ብር 3,000,000 (ሶስት ሚሊዩን) እንዲከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው።

ከሳሽ ከክስ ማመልከቻቸው ጋር የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዘው አቅርበዋል። እንዲሁም የምስክሮችን ዝርዝር አያይዞ አቅርቧል።

ተከሳሽ ጥር 5 ቀን 2000 ዓ/ም በተፃፈ መልስ የሰጡ ሲሆን የመልሱ ይዘት ባጭሩ፡-

- ወ/ሮ ሰልማ ድረስ ሳሌም (ታረቀኝ ተክሉ) የተከሳሽ ወላጅ እናት ስትሆን ከሳሽ ከእናቴ ጋር ጋብቻ ነበረኝ ሲል ያቀረበው ሃሰት ነው
- ከሳሽ ያቀረባቸው የሰነድ ማስረጃዎች ሃሰተኛ ሰነዶች ናቸው
    - በኩዌት መንግስት የተሰጠ ማስረጃ ነው የተባለው ሀሰተኛ ነው፣ ፎቶግራፍም የለበትም፣ በኤምባሲና በውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተረጋገጠ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም

- በኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ መስተዳደር የናኢባው ወረዳ ፍርድ ቤት ተሰጠ የተባለው ማስረጃ ሀሰተኛ ነው፣ ፎቶግራፍ የለበትም፣ ከኩዌት ተሰጠ ከተባለው ማስረጃ ጋር የሚጋጭ ነው

- ከሳሹ ከናቴ ጋር በባልና ሚስትነት ክርክር በቀረበበት ቤት አልኖረም
- ማች እናቴ ውጭ አገር ተመላላሽ ነጋዴ ስለነበረች ከሳሹ አንዳንድ ጉዳዩችን እንዲፈፅምላት ውክልና ሰጠችው እንጁ በባልና ሚስትነት አብረው አልኖሩም
- ከሳሹ በነበረው የውክልና ዘመኑ የተሰጠውን እምነት በመተው ግምቱ ብር 150,000 (አንድ መቶ ሺህ) የሆነ ወርቅ በመሸጡ ማች እናቴ በስርቆት ወንጀል በመክሰስ አሳስራዋለች
- ክስ የቀረበበት ቤት የእናቴ የግል ቤት እንጂ ከሳሹ በጋራ ያፈራው ንብረት አይደለም፣ ከሳሹ በቤቱም ኖሮ አያውቅም
- የጋራ ሃብት ነው የተባለው ቤት ግምት ተቀባይነት ያለው አይደለም የሚል ነው።

ተከሳሹ ከመልሳቸው ጋር የተለያዩ የሰነድ ማሰረጃዎችን አያይዘው አቅርበዋል። እንዲሁም የምስክሮችን ዝርዝር አቅርበዋል።

# አባሪ 6

## 1. ክስ

ከሳሽ ሰኔ 14 ቀን 2000 ዓ/ም በተፃፈ ያቀረበው ክስ ባጭሩ፡- ከሳሽ ተከሳሹ በቃሊቲ የሚያሰራውን የምግብ ፋብሪካ ህንፃ ለመገንባት ጥቅምት 7 ቀን 1998 ዓ/ም በተፈረመ ውል ተስማምቷል፡፡ በዚህም መሰረት ለሲቪል ስራ የፕሮጀክት ግንባታ በወጡት መደበኛ የውል ደንቦች መሰረት ውሉን ለማስፈፀም ለተመደበው አማካሪ መሀንዲስ በግንባታ ስራው የውል ስምምነት በተሰጠው ስልጣን መሰረት በከሳሽ በቁጥር 1 እና 2 የተቀመጡ ክፍያዎችን ተከሳሽ ለከሳሽ ብር 1,434,817.67 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሰባት ከስልሳ ሰባት ሳንቲም) እንዲከፈል አፅድቋል፡፡ ሰነዱም ለተከሳሹ ደርሷል፡፡ ሆኖም ተከሳሹ ክፍያውን ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆነ ስለሆነ ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍሉ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ከሳሽ ከክስ ማመልከቻው ጋር የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዞ አቅርቧል፡፡

## 2. መልስ

ተከሳሽ ህዳር 5 ቀን 2000 ዓ/ም በተፃፈ የሰጠው መልስ ይዘት ባጭሩ፡-

- ከሳሽ ብር 1,434,817.67 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰላሳ አራት ሺህ ስምንት መቶ አስራ ሰባት ከስልሳ ሰባት ሳንቲም) ሊከፈለው የሚችለው ውሉ ሳይቋረጥ ቀጣይነት ሲኖረው ብቻ ሲሆን ውሉ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት ቢቋረጥ ሂሳብ ተሰርቶ መወራረድ ያለበት ነው

- ተከሳሽ በግንባታ ውሉ መሰረት በቅድሚያ ብር 493,387.39 (አራት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) የከፈለ ሲሆን ሂሳብ በሚታሰብበት ጊዜ ይህ ሊወራረድ ይገባል

- በስፍር የምስክር ወረቀት ቁጥር 1 ላይ ከተመለከተው ክፍያ ውሥጥ ብር 450,220.87 (አራት መቶ ሃምሳ ሺህ ሁለት መቶ ሃያ ከሰማንያ ሰባት ሳንቲም) ያህሉ ለግንባታ የቀረበ የአርማታ ብረት የተገዛበትን የሚመለከት ሲሆን ኮንትራክተሩ ካስገባው ብረት ውስጥ ጥቅም ላይ ያዋለው የተወሰነ ሲሆን ቀሪውን ጭኖ የወሰደ ስለሆነ የምስክር ወረቀቱ የክፍያ ወረቀት ሊሆን የሚችል አይደለም

- በስፍር የምስክር ወረቀት ቁጥር 1ና 2 ላይ የቁፋሮ ስራን እንዲሁም ተጓጓዘ የተባለውን አፈር በተመለከተ ተሰራ የተባለውና በተግባር የተሰራው የተለያየ በመሆኑ ወረቀቶቹ ለክፍያ የሚበቁ አይደለም

- አብላጫ ክፍያ በተግባራዊ የስራ እንቅስቃሴ አልፎ አልፎ የሚያጋጥም ሲሆን የሚደረገውም አማካሪ መሀንዲሱ ኮንትራክተሩ ያለበትን የገንዘብ ችግር ያቃልልለታል ብሎ ሲያምንና ስራው መሰራቱ አይቀርም በሚል በመሆኑ ሂሳብ መወራረዱ የግድ ነው

- በዚህም መሰረት አጠቃላይ የተሰራው ስር ብር 1,208,504.42 (አንድ ሚሊዩን ሁለት መቶ ስምንት ሺህ አምስት መቶ አራት ከአርባ ሁለት ሳንቲም) ሲሆን ቅድሚያ ክፍያ ብር 493,387.39 (አራት መቶ ዘጠና ሶስት ሺህ ሶስት መቶ ሰማንያ ሰባት ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም) ሲቀነስ ተከፋይ የሚሆነው ብር 715,117.03 (ሰባት መቶ አስራ አምስት ሺህ አንድ መቶ አስራ ሰባት ከዜሮ ሶስት ሳንቲም) ሲሆን ወለዱም መታሰብ ያለበት ክስ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ነው የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ከመልሱ ጋር የተለያዩ የሰነድ ማስረጃዎችን አያይዞ ያቀረበ ሲሆን ምስክሮቹንም አቅርቦ አሰምቷል፡፡

# አባሪ 7

## 1. ክስ

ከሳሽ ሀምሌ 9 ቀን 1999 ዓ/ም በተፃፈ ያቀረቡት ክስ ባጭሩ፡- በቀድሞ ወረዳ 17 ቀበሌ 23 የቤት ቁጥሩ 0188 የሆነ መኖሪያ ቤት ከባለቤቶቹ ከአቶ ታደሰ የሺጥላና ከወ/ሮ ሰናይት ጥበበ በጊዜው በመንደር በተደረገ ውል በብር 900,000 (ዘጠኝ መቶ ሺ.ህ) የገዛሁት ሲሆን የሽያጩን ገንዘብ በቅድሚያ ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺ.ህ) ከፍዩ ቤቱን የተረከብኩ ሲሆን ቀጥሎ ብር 200,000 (ሁለት መቶ ሺ.ህ) ለሻጮች በወኪሌ በአቶ ያሬድ ማሞ አማካይነት ከፍያለሁ፡፡ ከሳሽ ቤቱን በምገዛበት ወቅት የኤች አይ ቪ ታማሚ የነበርኩ ሲሆን ባለቤቴም በዚህ በሽታ ሞቷል፡፡ ቤቱን ከገዛሁ በኃላ ህመሙ ስለፀናብኝ በአልጋ ላይ እንዳለሁ ከአስታማሚዎች አንዷ ተከሳሽ እህቴ ስትሆን በተጨማሪም ለእሷ እናት ለእኔ የእንጀራ እናት ከሆነችው ጋር በመሆን ሟች ባለቤቴ ከሌላ የወለደው ልጅ ወራሽነቱን አስረድቶ የመጣ መሆኑንና በእኔ ላይ ክስ በፍርድ ቤት ያቀረበ ጠበቃ ነው በማለት አንድ ሰው አምጥተው በማሳየትና እሱም ክሱ የቀረበ መሆኑን በሃሰት በማረጋገጥ የቤቱ ውል በተከሳሽ ካልሆነ በቤቱ ላይ የሚኖረኝን መብት የማጣና ልጄም ያለቅርስ የሚቀር መሆኑን በመግለፅ በማታለልና ተፅዕኖ በማድረግ እሷ እኔን ወክላ ውሉን እንድታደረግ ቤቱን ለሸጡልኝ ሰዎች ነግሬ ከእነሱ ጋር ያደረግሁት ውል እንድቀድ አድርገውናል፡፡ ከህመሜ ትንሽ ተሸሎኝ በማገገም ላይ ሳለሁ ተከሳሽ የቤቱን ሽያጭ ውል ከሻጮች ጋር ማድረጓን፣ የባለቤቴ ወራሽም በኔ ላይ ክስ መስርቷል የተባለውም እውነት አለመሆኑን፣ ተከሳሽዋ የተጫነችኝና ያታለለችኝ መሆኑን ስለተረዳሁ ውሉ በስሜ እንዲደረግ ስጠይቅ ተከሳሽ ፈቃደኛ አልሆነችም እንዲሁም የተሰወረችብኝ ስለሆነ የቤቱ ባለቤትነት በኔ ስም እንዲሆን ወይም በአማራጭ አላግባብ የበለፀገችበት ስለሆነ በአሁኑ የገበያ ዋጋ ቤቱ ብር 2,000,000 (ሁለት ሚሊዩን) እንድትከፍለኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ከሳሽ ከክስ ማመልከቻቸዋ ጋር አንድ የሰነድ ማስረጃ አያይዘው ያቀረቡ ሲሆን በክስ ማመልከቻቸው ላይ የዘረዘሯቸውን ምስክሮች አሰምተዋል፡፡

## 2. መልስ

ተከሳሽ ጥር 6 ቀን 2000 ዓ/ም በተፃፈ የሰጡት መልስ ይዘት ባጭሩ፡-

- ክስ የቀረበበትን ቤት በራሴ ገንዘብ የገዛሁት እኔ እንጂ ተከሳሽ አይደለችም
- የባለቤትሽ ወራሽ እንዳይመጣብሽ በስሜ ልዋዋል በሚል የማታለል ድርጊት አልፈፀምኩም
- ቤቱን በተመለከተ በስሟ እንድዋዋል አልተስማማንም፣ አልወከለችኝም፣ ማስረጃም አልቀረበም
- የሽያጭ ውሉን ከሳሽ የፍ/ብ/ህ/ቁ/ 2005 በሚያዘው መሰረት በሰው ማስረጃ ማስተባባል አትችልም የሚል ነው፡፡

ተከሳሽ ከመልሳቸው ጋር አንድ የሰነድ ማስረጃ አያይዘው ያቀረቡ ሲሆን በመልሳቸው ላይ የዘረዘሯቸውን ምስክሮች አቅርበው አሰምተዋል፡፡

# የስልጠና ማንዋል፡፡

| ኮርስ | የስልጠና ቀናት | ስልጠና የሚሰጥበት ንኡስ አርእስት | የስልጠና ስልት |
|---|---|---|---|
| የፍትሃብሄር ቅድመ ሙግት ሂደትን መምራት (pre-trial management) | ቀን 1 | • በፍትሃብሄር ስነስርአት አካሄድና አመራር መሰረታዊ መርሆች<br>• በፍትሃብሄር ጉዳዮች ቀደም ብሎ የመግባት ዘዴ<br>• ጉዳዮችን ለያይቶ የመምራት ዘዴ<br>• ውጤታማ የሆነ የቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴ | • አጭር ገለፃ<br>• በሞጁሉ ላይ የተመለከተውን የማሰቢያ ጥያቄ 1ና 2 እንዲሰሩ ማድረግ፣ በጋራ መወያየት<br>• የቡድን መወያያ ጥያቄዎች 1ና 2ን ሰልጣኞች በቡድን እንዲወያዩና ማጠቃለያ የጋራ ውይይት ማድረግ |
| | ቀን 2 | • ክስ ለመስማት መደረግ ስላለባቸው ቅድመ ዝግጅቶች<br>• ክስን የመስማት ዘዴ<br>• በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ላይ ብይን የመስጠት ዘዴ | • አጭር ገለፃ<br>• የቡድን መወያያ ጥያቄዎች 3ና 4ን ሰልጣኞች በቡድን እንዲወያዩና ማጠቃለያ የጋራ ውይይት ማድረግ<br>• ከአባሪ 1-7 ያሉትን ጉዳዮች በተመለከተ ጭብጥ መመስረት ልምምድ<br>• ከአባሪ 1ና 2ን በተመለከተ የክስ መስማትና ለመጀመሪያ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | • ጭብጥ የመመስረት ዘዴ | ደረጃ መቃወሚያ ብይን መስጠት ልምምድ ማድረግ |
| | ቀን 3 | • ከቀን 2 የቀጠለ | • ከአባሪ 1ና 2ን በተመለከተ የክስ መስማትና ለመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ብይን መስጠት ልምምድ ማድረግ |
| የፍትሃብሄር የሙግት ሂደትን መምራት (trial management) | ቀን 1 | • ሰብሰብ ያለ የፍትሃብሄር ሙግት አሰማም ዘዴ<br>• የሙግት ቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴዎች<br>• የራሳቸውን ጉዳይ ይዘው የሚከራከሩ ተሟጋቾች ጉዳይን መምራት<br>• የውስብስብ ጉዳዮች ሙግት አሰማም ዘዴ | • አጭር ገለፃ<br>• አባሪ 1-3 ላይ የተቀመጡትን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የሙግት ልምምድ ያድርጉ |
| | ቀን 2 | • የቀጠለ | • አጭር ገለፃ<br>• አባሪ 1-3 ላይ የተቀመጡትን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የሙግት አመራር ልምምድ ያድርጉ |
| | ቀን 3 | • የቀጠለ | • አጭር ገለፃ<br>• አባሪ 1-3 ላይ የተቀመጡትን ጉዳዮች መሰረት በማድረግ የሙግት አመራር ልምምድ ያድርጉ |
| የይግባኝ ሙግት ሂደትን | ቀን 1 | • የይግባኝ ቀጠሮ አሰጣጥ ዘዴ | • አጭር ገለፃ<br>• ከሞጁሉ ጋር የተያያዙ 6 |

| | | | |
|---|---|---|---|
| መምራት | | • ይግባኝን ለመስማት መደረግ ስላለባቸው ዝግጅቶች<br><br>• የይግባኝ አሰማም ዘዴ | የሰበር መዝገቦችን መሰረት በማድረግ የይግባኝ አሰማም ልምምድ ያድርጉ |
| | ቀን 2 | • የቀጠለ | • አጭር ገለፃ<br>• ከሞጁሉ ጋር የተያያዙ 6 የሰበር መዝገቦችን መሰረት በማድረግ የይግባኝ አሰማም ልምምድ ያድርጉ |